



# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ
## የመምህሩ መምሪያ



## 6ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ እና
በዲላ መምህራን ት/ኮሌጅ የተስማማ

# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የመምህሩ መምሪያ

## 6ኛ ክፍል

አስማምቶ አዘጋጆች፡- -አሸናፊ ደጉ

-በቀለ ሙዳ

-ስናፍቅሽ አስፋው

# የይዘት ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምዕራፍ አንድ ........ 1
ባህላዊ አለባበስ ........ 1
ምዕራፍ ሁለት ........ 14
ታዋቂ አትሌቶች ........ 14
ምዕራፍ ሶስት ........ 28
ቃላዊ ግጥም ........ 28
ምዕራፍ አራት ........ 38
ዘመናዊ እርሻ ........ 38
ምዕራፍ አምስት ........ 55
ቱሪዝም ........ 55
ምዕራፍ ስድስት ........ 69
አደንዛዥእጾች ........ 69
ምዕራፍ ሰባት ........ 78
የጥላቻ ንግግር ........ 78
ምዕራፍ ስምንት ........ 96
ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ በኢትዮጵያ ........ 96
ምዕራፍ ዘጠኝ ........ 112
ባህላዊ ክንዋኔዎች ........ 112
ምዕራፍ አስር ........ 133
ሴቶችን ማብቃት ........ 133
ዋቢ መፃሕፍት ........ 148

# መግቢያ

ይህ የመምህር መምሪያና ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄደው የ6ኛ ክፍል የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ አማርኛን በመጀመሪያ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ፤ በተጨማሪም የቃላትና የሰዋስው እውቀት እንዲገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት አካል ነው።

የመምህር መምሪያው በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ በመመሥረት በአዳዲሶቹ የመማሪያ-ማስተማሪያ መሣሪያዎች ውስጥ በጥቅም ላይ ስለዋሉት የማስተማር አቀራረቦችና ስለአዲሱ መርሃ ትምህርት(ሥርዓተትምህርት) መነሻ ሀሳቦች መሠረታዊ መረጃ ይሰጣል።በአንድ ምዕራፍ ሥርም ለቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ግልጽ መመሪያ ያቀርባል።በተጨማሪም ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ለመከታተልና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ተገቢውን ድጋፍና ማጠናከሪያ ለመስጠት ተከታታይ ምዘናን መተግበር የሚቻልበትን መርሕ ይዟል።በትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታንና የአካቶ ትምህርትን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚገባ ድጋፍ ይሰጣል።

በመጨረሻ ላይም ለ6ኛ ክፍል የተዘጋጀው አማርኛ ቋንቋ (የመጀመሪያ) መርሃት ምህርት ተያይዟል።ይኽ መርሃ ትምህርትም በየደረጃው በእያንዳንዱ ወሰነ ትምህርት ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ስለሚገቡ የቋንቋ ብቃቶች ያሳያል።

## ❖ የማስተማር መርሆዎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በሁሉም ክሂሎች(ማዳመጥ፣መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) እንዲሁም ቃላትና ሰዋስው የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች የማንበብንና የመጻፍን ችሎታዎች በሚያዳብሩበት መልክ ተደራጅተዋል፡፡

አዳምጦ/አንብቦ መረዳት የሚዳብረው በቅድመ ማዳመጥ/ማንበብ፣ በማዳመጥ/በማንበብ ሂደትና በድኅረ ማዳመጥ/ማንበብ ተግባራት ነው፡፡ተማሪዎች ስለጽሑፉ (በቅድመ ማዳመጥ/ማንበብና በማዳመጥ/በማንበብ ሂደት ወቅት) እንዴት መገመት እንደሚችሉ፣መረዳታቸውን በራሳቸው እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉና ያዳመጡትን ወይም ያነበቡትን እንዴት መገምገም እንደሚችሉ መማር አለባቸው፡፡

መናገርና መጻፍ በተገቢ ሁኔታ ራስን መግለጽን ይመለከታል፡፡ ይኸውም ቋንቋውን በትክክል መጠቀምንና ሀሳብን ለሌላ አካል በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በግልጽ ማስተላለፍን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም የንግግርና የጽሑፍ ክሂል የሚዳብረው ተማሪዎች በተቻለ መጠን ራሳቸውን እንዲገልጹ በርካታ ዕድሎች ሲመቻቹላቸውና ወቅታዊ ግብረ-መልሶችም ሲያገኙ ነው፡፡

የቃላት ዕውቀት፣ቃላትን የመለየት/የመረዳትና ፍቻቸውን የመገንዘብ ችሎታ ነው፡፡የተገደበ የቃላት ዕውቀትያላቸው ተማሪዎች የሚያነቡትንም ሆነ የሚያዳምጡትን ጽሁፍ መልእክት ለመረዳት የቃላት እውቀት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡የቃላት ዕውቀት የሚዳብረው አዳዲስ ቃላትን ከነፍቻቸው በማስተማር፣ተማሪዎች እነዚህን ቃላት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ እንዲጠቀሙባቸው በማበረታታትና ከሚያነቡት ወይም ከሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ የቃላትን ፍቺ የሚያገኙበትን ብልሃት (ስትራተጂ) በማስተማር ነው፡፡

ሰዋስው፡-በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተመሥርቶ ለደረጃው በተዘጋጀው የትምህርት ወሰንና ተለጣጥቆ መሠረት የተለያዩ ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በመማርና በትክክል በመጠቀም ላይ ያተኩራል፡፡ በአጠቃ ላይ ከላይ የዘረዘርናቸው የትምህርት ይዘቶች ማዕከል ያደረጉት በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ዓላማዎች ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## ባህላዊ አለባበስ

ክፍለ ጊዜ (18)

**የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-**

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡-** ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-

- ✓ በተገቢው ፍጥነትና በትክክለኛ ድምጸት ያነባሉ፡፡
- ✓ የቃላትን አገባባዊ ሥርዓት ተከትለው አረፍተ-ነገር ይመሰርታሉ፡፡
- ✓ ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ ቃላት ፍቺ ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ቃላትን እያጣመሩ ያነባሉ፡፡
- ✓ በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ስርዓተ-ነጥቦችን በተገቢው መንገድ ይጠቀማሉ፡፡

**የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች**

- ➢ አድምጦ ሀሳብ መግለፅ
- ➢ አቀላጥፎ ማንበብ
- ➢ አዳዲስ ቃላት
- ➢ አንቀጽ መፃፍ

# ❖ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## የሀገር ባህል ቀሚስ

## ❖ የትምርቱ አቀራረብ

- መምህር ወደ ተግባር ከመግባትዎ በፊት መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ካሉ ወደፊት እንዲቀመጡ በማድረግ የአካል እንቅስቃሴዎን በመከታተል እንዲሳተፉ ያድርጉ፡፡
- ለማዳመጥ የቀረበውን ምንባብ ከማንበብዎ በፊት በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን የምዕራፍ ዓላማዎች እንዲረዱ ያብራሩላቸው፡፡
- ወደ ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በመሻገር ለማዳመጥ ትምህርት የቀረበውን ስዕል ተመልክተው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- በውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲገልፁ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠልም በጥሞና እያዳመጡ ጭብጡን ለማወቅ ማስታወሻ እንዲጽፉ በመግለጽ ለማዳመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡

ኢትዮጰያውያን በየአካባቢያቸው፣ በየአጥቢያቸው ከትውፊታቸው ከሚቀዳው አለባበስ አንዱ ሀገረኛው ቀሚሳቸው ነው፡፡ ከሀምሳ አመታት በፊት ታትሞ በወጣው የአለቃ ደስታ ተክለ ወልድ ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት›› ባህላዊ ቀሚስን በየፈርጅ በየፈርጁ ይበይነዋል፡፡ በሐር የተጠለፈና የተዘመዘመውን ጥልፍ ቀሚስ ሲለው፤ ጥበብ ያለበትን ደግሞ ጥበብ ቀሚስ ይለዋል፡፡ ባህላዊ አለባበስ አንድን ግለሰብ ወይ ምማህበረሰብ በቀላሉ የት አካባቢ እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል፡፡ ለአብነት ያህልም በጎጃም ማህበረስብ የልጃገረዶችና የሴቶች አለባበስን ከአጊያጌጥ ጋር እንደሚከተለው ገልፆታል፡፡ ቀደም ባሉት

ጊዜያት የጎጃም ልጃገረዶች ባህላዊ አለባበስ በተለይም በዓል ሲሆን ለብሰውት የሚወጡት ልብስ ሙሉ በሙሉ የሀበሻ ቀሚስ ነበር፡፡የሀበሻ ቀሚስ ጉንፍ፣ ሽብሽቦና ጥልፍ ቀሚስ እንዲሁም ፍቅር ቁርጥ የተባለ ነበር፡፡፡

አሁን ላይ ግን በተለያዩ አጋጣሚዎች ይህንን አለባበስ ሳይሸራርፍ ሙሉውን ለብሳ የምትወጣ ልጃገረድ ማግኘት ባይቻልም በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ልጃገረዶች ባህላዊ አለባበሳቸውን ያዘወትራሉ፡፡ በእለት ከእለት እንቅስቃሲያቸው የሀበሻ ቀሚሱ ቀስ በቀስ ዘመን አመጣሽ በሆኑ ከብትን ጨርቆች በሚዘጋጁ ልብሶች ቢተካም በበዓላት፣በቤተ-እምነት ሲገኙና በሌሎች ማህበራዊ አጋጣሚዎች (በሰርግ፣ ዘመድ ጥየቃ፣ዘመን መለወጫና ህዝባዊ ስብሰባዎች…)ላይ አሁንም ድረስ ባህላዊ የሀበሻ ቀሚስ መልበስ የተለመደ ነው፡፡ ባህላዊ ቀሚሶች በአይነታቸውና በቅርፃቸው የተለያዩ ናቸው፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ ?
2. ምንባቡ ምን ምን የቀሚስ አይነቶችን የሚጠቅስ ይመስላችኋል?

ለአብነት ያህልም፡-

1. ሽብሽቦ ቀሚስ

ሽብሽቦ ቀሚስ የተለያዩ ቀለማት ካላቸው ጥለቶች ከክር፣ ከማግና ከዝሃ የሚዘጋጁ ባላገሩ ወጣት ሴቶችና በእናቶች ሊለበስ የሚችል የልብስ አይነት ነው፡፡ ሽብሽቦ የተባለበት ምክንያት እንደጉንፍ ቀሚስ ልቅ ባለመሆኑና ወገቡ ላይ ገመድ በማስገባት የሚሰፋ ስለሆነ እና ቀሚሱ ከወገቡ ጀምሮ እስከታች እስከጥለቱ ድረስ የሚሸበሸብበ መሆኑ ነው፡፡

## 2. ጉርድ ቀሚስ

ጉርድ ቀሚስ ከጊዜ በኋላ ነባሩን የማህበረሰቡን ባህል በማሻሻል የተገኘ እንደሆነ ይገመታል፡፡ የተለያዩ ቀለም ካላቸው ጥለቶች ከማግና ከዝሃ የሚዘጋጅ ሲሆን ጉርድ የተባለበትም ምክንያት እስከወገቡ ድረስ ባዶ ሆኖ ከወገቡ በታች ልቅ ስለሆነ ነው፡፡ ቀሚሱ ከወገቡ ጀምሮ እስከ ጥለቱ ድረስ የሚሸበሸብ መሆኑ ከሸብሸቦ ቀሚስ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ያላገቡ ልጃገረዶች፣ እናቶች እናህፃናት ይለብሱታል፡፡

## 3. ጉንፍ ቀሚስ

የጎጃም ማህበረሰብን ከሚወክሉና ባህሉን ከሚያንፀባርቁ ሀገረሰባዊ አለባበሶች መካከል አንዱ ጉንፍ በመባል የሚታወቀው የቀሚስ አይነት ነው፡፡ ጉንፍ ከጥጥ የሚዘጋጅና በአካባቢው ሸማሰሪዎች የሚሰራ የሴቶች ባህላዊ ልብስ ሲሆን በአብዛኛው በተለያዩ በዓላትና ክብረ በዓላት ላይ ይለበሳል፡፡

ምንጭ፡-ከሪፖርተር ጋዜጣሚ ያዚያ11/2009ዓ/ም ለስድስተኛ ክፍል እንዲሆን ተሸሽሎ የቀረበ

- የቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥና ድህረ ማዳመጥ ሂደቶችን በተግባር ላይ በማዋል ተማሪዎቹ የአዳምጦ መናገር ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያግዟቸው፡፡
- በተግባር አንድ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- ለቃላት እውዳዊ ፍቺ እየሰጡ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- በመጨረሻም ስለአንድ ባህላዊ ልብስ ከሰዎች ጠይቀው በክፍለ ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ ይግለጹላቸው፡፡

- ጠይቀው የመጡትን በክፍል በንገግገር እንዲያቀርቡ ጊዜውን ያመቻቹላቸው፡፡
- ባቀረቡት ሀሳብ እርስ በርስ እንዲወያዩና አስተያየት እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎቹ ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክት በትክክል መረዳት መቻላቸውን በድህረ ማዳመጥ ተግባራት ስር ላሉት ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ያረጋግጡ፡፡
- በሌላ ጊዜ ሬዲዮ፣ቴሌቪዥን እያዳመጡ ያዳመጡትን ለጓደኞቻቸው በመተረክ የማዳመጥ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያስረዷቸው፡፡

## ❖ክፍል ሁለት፡- ንባብ

### ባህላዊ አለባበስ

- የማንበብ ተግባር ከመጀመሩ በፊት የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎችን በርዕሱና በምስሉ መካከል ያለውን ዝምድና፣ርዕሱን አይተው ምንባቡ ስለምን ሊገልጽ እንደሚችል እንዲገምቱ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ግምታቸውን ይቀበሏቸውና ወደቀጣዩ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር ንባብ ያምሩ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ውስብስብ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ያሉ በመሆናቸው በአንብቦ መረዳት ላይ እንቅፋት እንዳይሆንባቸው በትክክል እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም ተማሪዎቹ በለሆሳስ እንዲያነቡና በንባብ ሂደት የሚያጋጥማቸውን ግልጽ ያልሆነ ሀሳብ በማስታወሻ እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- የንባብ ሂደቱን ገታ በመድረግ የንባብ ጊዜ ጥያቄን እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡

- የማንበብ ሂደቱን ሲያጠንቅቁ ሲያነቡ ያጋጠማቸው ግልጽ ያልሆነ ሀሳብ ካለ እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፡፡
- ላቀረቡት ጥያቄ በራሳቸው መልስ መስጠት እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ በተማሪዎቹ ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ እርስዎ ይስጧቸው፡፡
- በመልመጃ ሶስት የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት በጽሁፍ እንዲመልሱና ለሚሰጡት መልስ ምክንያት እንዲያቀርቡ ይግለጹላቸው፡፡
- የሰጡትን መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በተጨማሪም ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት ፍች በጽሁፍ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡
- የቀረቡትን ጥያቄዎች በትክክል መመለስ መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በትክክል ያልሰሩት ጥያቄካለትክከለኛውን መልስይግለፁላቸውና እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- መምህር የአንብቦ መረዳት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ ለአቀላጥፎ ንባብ ባህላዊ አለባበስ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ተቀንጭቦ የተወሰደ ምንባብ ቀርቧል፡፡
- በጥንድ በጥንድ ሆነው ደቂቃ እየያዙ በተገቢው ፍጥነት እንዲያነቡ ያዘጋጇቸው፡፡
- እያንዳንዱ ተማሪ ንባቡን ያጠናቀቀበትን ደቂቃ እንዲመዘግቡላቸው ንባቡን ሲጨርሱ እንዲያሳውቅዎት ያስረዷቸው፡፡
- ምን ያህሉ ተማሪ በተሰጠው ደቂቃ አጠናቆ እንዳነበበና ምን ያህሉ ደግሞ ማንበብ እንዳለቻለ ይለዩ፡፡

- ማንበብ ያልቻሉትን ተማሪዎች በድጋሚ ለብቻ ለብቻ ደቂቃ ይዘው ያስነብቧቸው፡፡
- በዚህም ያሳዩትን መሻሻል ይመዝግቡና መሻሻል ያላሳዩ ተማሪዎችን ለይተው ይመዝግቡ፡፡
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ተጨማሪ ተግባር በመስጠት ንባብን ያለማምዷቸው፡፡
- በመጨረሻም ተማሪዎቹ የንባብ ክሂላቸውን ለማሳደግ ይረዳቸው ዘንድ የተለያዩ ጽሁፎችን እንዲያነቡ በመግለጽ ትምህርቱን ያጠናቁ፡፡

## ❖ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### መነጠልና ማጣመር

- የቃላት አውዳዊ ፍች ቃላት በዓረፍተ-ነገር ውስጥ የሚኖረውን ፍች የሚመለከት መሆኑን በማስረዳት እንዴት መረዳት እንደሚችሉ ከቀጥተኛ ፍች እንደሚለይ በምሳሌ በማስደገፍ አጭር ገለፃ ይስጧቸው፡፡
- ለምሳሌ አሻራ የሚለውን ቃል ወስደን በቀጥተኛ ፍች ብንመለከት ምልክት የሚል ፍች ይሰጠናል፡፡
- ይህንኑ ቃል በአውዳዊ ፍች ብንመከተው ኢትዮጵያውያን በአባይ ግድብ ላይ አሻራቸውን አስቀምጠዋል፡፡ብንል አውዳዊ ፍች የድርሻውን አበርክቷል የሚል ይሆናል፡፡
- በተሰጠው ገለፃ መሰረት በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተ-ነገር እንዲሰሩባቸው ያድርጓቸው፡፡
- በማዛመድ የቀረበውን የቃላት ተመሳሳይ ፍች ጨምረው ያሰሯቸው፡፡
- ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ ለቃላቱ ትክክለኛ መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

- የፈጸሙት ስህተት ካለ እርማት በመስጠት እንዲያስተካክሉ ያበረታቷቸው፡፡

❖ **ለናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**መልመጃ አንድ**

ከዚህ በታች በ‹‹ሀ››ስር ለቀረቡት ቃላትእና ሐረጋትበ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት በፍች ተመሳሳይ የሆኑትን እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡

1. ረ
2. ሰ
3. መ
4. ሐ
5. ሠ
6. ሀ

**መልመጃ ሶስት**

ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት በፍች ልዩ የሆነውን አውጡ፡፡

1. ሀ
2. መ
3. ሐ
4. ለ
5. መ

# ❖ክፍል አራት፡- ጽህፈት

## አንቀጽ

❖ **ማስተዋሻ፡-**

➢ **የቢጋር (የአስተዋፅኦ) ምንነትና አዘገጃጀት**

ቢጋር (አስተዋፅኦ) አንድን አንቀጽ ለማዘጋጀት፣ከተዘጋጀም በኋላ በተፈለገው መንገድ ሀሳቡ በትክክል መስፈሩን የሚያሳይ ንድፍ ነው፡፡ቢጋር አብዛኛውን ጊዜ አንቀጽ ከመፃፋችን በፊት የሚዘጋጅ ሲሆን ጸሀፊው ከዋናው ሀሳብ ሳያፈነግጥ፣በቅደም ተከተል እንዲቀመጥ ያግዛል፡፡

ቢጋር ለጀማሪም ሆነ ልምድ ላላቸው ጸሀፊዎች ወሳኝ ነው፡፡ቢጋር (አስተዋፅኦ) ለማንኛውም ጸሀፊ የፅሁፉን መነሻና መድረሻ በመጠቆም ትልቅ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ እንዲህ አይነቱ ድጋፍ በፅሁፍ ውስጥ የሀሳብ ቅደም ተከተል መፋለስ እንዳይኖር በእጅጉ ያግዛል፡፡ቢጋር በዝርዝር(ፍሬሀሳቡን) በአጭሩ በሚጠቁም መልኩ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ ይሁን እንጅ የአንቀጹን መነሻና መድረሻ ቅደም-ተከተል ይዞ እንዲቀርብ በዝርዝር ቢቀርብ የተሻለ ይሆናል፡፡በተመረጠው እርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከርእሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሃሳቦች በወረቀት በአጭር በአጭሩ ማስፈር ስራውን የበለጠ ያቀለዋል፡፡ቢጋርን በሁለት አይነት መንገድ ልናዋቅር እንችላለን፡፡እነሱም በርዕስ መልክና በአረፍተ-ነገር መልክ ሊሆን ይችላል፡፡

**ሀ. ቢጋር በርዕስ መልክ ሲዋቀር**

ለምሳሌ፡-አንቀጽ ለመፃፍ ያሰብነው የአየር ብክለትና መንስኤዎቹ በሚል ርዕስ ቢሆን ርዕሱን አስመልክቶ ከዚህ የሚከተሉትን መሰል ሀሳቦች በወረቀት ላይ ማስፈር ይቻላል፡፡

የአየር ብክለትና መንስኤዎቹ

1. የኢንዱስትሪዎች ጭስ
    1.1. የቀላል ኢንዱስትሪዎች ጭስ
    1.2. የከባድ ኢንዱስትሪዎች ጭስ
2. ጦርነት
    2.1. የከባድ ፈንጂዎች ጭስ
    2.2. የኑክሌር ፍንዳታ
    2.3. የቀላል መሳሪያዎች ጭስ
3. የተሽከርካሪዎች፣የአውሮፕላኖችና የሮኬቶች ጭስ
    3.1. የቀላልና የከባድ አውሮፕላኖች ጭስ
    3.2. የቀላልና የከባድ ተሽከርካሪዎች ጭስ
    3.3. የሮኬቶች ጭስ
4. የተፈጥሮ አደጋዎች የሚፈጥሩት ከፍተኛ ጭስ
    4.1. የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ
    4.2. ከፍተኛ የደን ቃጠሎ

ሰ. ቢጋር በዓረፍ-ተነገር መልክ ሲዋቀር

ምሳሌ፡-ክረምት ሲጠባ

አካባቢው በሙሉ ይጨልማል፡፡

1.1. ፀሀይ በደመናት ጋረዳለች፡፡

1.2. ጨረቃና ከዋከብት ይጋረዳሉ፡፡

1.3. ጋራ ሸንተረሩ በጉም ይሸፈናል፡፡

1.4. ሰማዩ ይጠቁራል፤ በደመና ይሸፈናል፡፡

ሰዎች በስራ ይጠመዳሉ

2.1. ገበሬው በእርሻ ስራ ይጠመዳል፡፡

2.2. የገበሬ ሚስቶች በጉልጓሎ ስራ ይጠመዳሉ፡፡

2.3. ሰዎች ከመዝናናት ይታቀባሉ፡፡

የእርሻ ስራ ግብዓቶች በጣም ተፈላጊ ይሆናሉ፡፡

3.1. የዘር እህል ፍላጎትና ዋጋ ይጨምራል፡፡

3.2. የማዳበሪያ ፍላጎት ይጨምራል፡፡

3.3. የእርሻ ስራ መሳሪያዎች ዋጋ ይጨምራል፡፡

መዝናናት መደሰትና መፈንጠዝ ቀዝቀዝ ይላል፡፡

4.1. ሰርግና ድግስ ጎልቶ አይታይም፡፡

4.2. ደምቆ የሚከበር በዓል አይኖርም፡፡

4.3. ጭፈራ፣ሆታና እልልታ እምብዛም አይታይም፡፡

- በጽህፈት ተግባር ላይ የቀረበውን የአንቀጽ አጻጻፍ ክሂል ከማሰራትዎ በፊት በአምስተኛ ክፍል ስለአንቀጽ ምንነትና የአንቀጽ አጻጻፍ ስልቶች በተመለከተ የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል በመምህሩ መምሪያ የቀረበውን የቢጋር አፃፃፍ ምንነትና የቢጋር ንድፍ ማስታወሻ እንዲፅፉ ያድርጓቸው፡፡

- ከዚያም አንቀጽ ለመጻፍ በተሰጣቸው ርዕስ ቢጋር እንዲያዘጋጁ ምሳሌውን በአግባቡ ያስረዷቸው፡፡
- በምሳሌው የቀረበውን ጅምር ቢጋር አጠናቀው እንዲጽፉ ይደግፏቸው፡፡
- በመጨረሻም አንቀጽ ለመፃፍ የሚያስችል ቢጋር ማዘጋጀታቸውን ያረጋግጡላቸው፡፡
- ከዚያም አንቀጽ ጽፈው እንዲመጡ ይግለፁላቸው፡፡በሚቀጥለው ክፍለ-ጊዜ የጻፉትን አንቀጽ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲቀያየሩ በማድረግ የጽሁፍን ስህተት እንዲለዩ ያግዟቸው፡፡
- ለይተው ያወጡትን ችግር እንዲያቀርቡ በማድረግ በራሳቸው ለማስተካከል እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡
- በመጨረሻም የተስተካከለውን አንቀጽ በመውሰድ በአርያነት እንዲያቀርቡ ያግዟቸው፡፡

### መርጃ መሳሪያ

ተስተካክሎ የተዘጋጀ ቢጋር በቻርት

## ❖ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### የተጸውዖና የወል ስም

- ❖ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የተጸውዖና የወል ስሞችን ማስተዋሻ በደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ በጥያቄና መልስ በምሳሌ በማስደገፍ አጭር ገለፃ ያቅርቡላቸው፡፡
- ❖ ከዚያም በመማሪያ መጽሐፉ ተደበላልቀው የቀረቡትን ስሞች የተጸውዖና የወል ስም በማለት በሰንጠረዡ ውስጥ እንዲመድቡ ያድርጉ፡፡
- ❖ የሰሩትን እንዲናገሩ በማድረግ ስህተት ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት ትክክለኛውን መልስ እንዲይዙ ያድርጉ፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ የተጸውዖ እና የወል ስሞችን በትክክል መለየታቸውን ከሰጡት መልስ በመነሳት እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

- መደገፍ የሚያስፈልጋቸው፣ልዩ ፍላጎት ያላቸውንና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ካሉ በመለየት ተጨማሪ ተግባር በመስጠት እንዲለማመዱ ያግዟቸው፡፡
- ትምህርቱን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ተጨማሪ ተግባር ይስጧቸው፡፡

**መርጃ መሳሪያ**

**የተዘጋጀ የተፀውዖና የወል ስም የያዘ ሰንጠረዥ በቻርት**

# ምዕራፍ ሁለት

## ታዋቂ አትሌቶች

**ክፍለ ጊዜ 18**

**አጠቃላይ የምዕራፉ ዓላማዎች:-**

- ✓ ከቅጥያዎች ውስጥ ዋና ቃል ይለያሉ
- ✓ ቅጥያዎችን በማጣመር ቃላት ይመሰርታሉ፡፡
- ✓ የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የስርዓተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድተው የንባብ ድምፀቱን ጠብቀው ያነባሉ፡፡

**አጠቃላይ የምዕራፉ ይዘቶች:-**

- ➢ አዳምጦ ማስታወሻ መያዝ
- ➢ ቃላትን ማጣመርና መነጠል
- ➢ አንቀፅ ማዋቀር
- ➢ ተመሳሳይ ቃላት
- ➢ የወል ስሞች

## ❖ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ‹‹ ኦሎፒክን በባዶ እግር ››

## ❖ የትምህርቱ አቀራረብ

- ተማሪዎቹ ወደማዳመጥ ተግባር ከመሄዳቸው በፊት ለማዳመጥ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው በተማሪው መፅሀፍ ላይ የሰፈሩትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ሁለት ሁለት እየሆኑ እንዲወያዩና ስዕሉን ተመልክተው እንዲገምቱ ያድርጓቸው፡፡ከውይይቱ የተረዱትን እንዲናገሩ እድል ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን ደጋግመው እንዲያነቧቸውበማድረግ በቀላሉ አዳምጠው እንዲመልሱ የሚችሉበትን መንገድ ይግለፁላቸው፡፡
- በተጨማሪም የሚነበበውን ታሪክ ሲያዳምጡ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታዎሻ እንዲይዙበማስረዳት ምንባቡን በርጋታ ሁለት ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡

አበበ ቢቂላ ነሐሴ 30 1925 ዓ/ም በሰሜን ሸዋ አውራጃ ደነባ ልዩ ስሟ ጀቶ ከምትባል ስፍራ ተወለደ፡፡ ብላቴናው አበበ እንደ አካባቢው ልምድ በእረኝነትና በቄስ ትምህርት ተሰማርቶ በአስራ ሁለት አመቱ ትምህርቱን አጠናቀቀ፡፡ በዚህ በጨቅላ እድሜው ስመጥር የገና ጨዋታ ተጨዋች እንደነበረ ይነገርለታል፡፡ በ1934ዓ.ም አዲስ አበባ መጥቶ በክብር ዘበኛ በወታደርነት ይቀጠርና በገና ጨዋታ እና በስፖርት እራሱን እያዳበረ ቆዬ፡፡ወዲያው በ1936ዓ.ም የአራት ልጆች እናት የሆነችለትን ወ/ሪት የውብዳር ወለደ ጊዮርጊስን አገባ፡፡

በህዳር ወር 1938ዓ.ም በአስራ ስድስተኛው በሜልቡርን ኦሎምፒክ ላይ የተሳተፉ መለያ ስም የተፃፈበትን ልብሳቸውን ለብሰው ሀገራቸውን ወክለው የተወዳደሩትን ወጣቶች ባየ ጊዜ ምን ያህል ስሜት እንዳላቸው ተገረመ፡፡እሱም እንደነሱ ለመሆን እንደወሰነ ይጠቅሳል፡፡ በዚሁ ዓመት በብሄራዊ ሰራዊት የእርስ በእርስ ውድድር ላይ ተሳትፎ በአምስት ሺ ሜትር እና በአስር ሺ ሜትር ሩጫ የብሄራዊውን ክብረ ወሰን የያዘው የጊዜው የስፖርት ጀግና ዋሚ ቢራቱ እና አበበ በማራቶን ውድድሩ ሲገጥሙ ተመልካቹ ዋሚ ያሸንፋል ብሎ ነበር የሚጠብቀው፡፡ ነገር ግን አበበ ይህን ውድድር በቀላሉ ማሸነፍ ስለቻለ ተይዞ የነበረውን ክብረ ወሰን የራሱ ማድረግ ችሏል፡፡ በዚህ ድሉም ለ1942ዓ.ም ለሮም ኦሎምፒክ በተወዳዳሪነት ለመመረጥ በቅቷል፡፡

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ?
2. ሻምበል አበበ ቢቂላ ኦሎምፒክን በባዶ እግር ለምን የተባለ ይመስላችኋል?

ሀገራቸውን ወክለው በዚህ ውድድር ላይ ለመሳተፍ ከአሰልጣኙ ጋር ወደ ሮም ካመሩት የኢትዮጵያ ተወዳዳሪዎች መካከል ለማራቶን እሩጫ የተመረጡት አበበ ቢቀላና አበበ ዋቅጅራ ነበሩ፡፡ አሰልጣኙም በዚያን ወቅት የጊዜውን ምርጥ የማራቶን ተወዳዳሪዎች የነበሩትን ኮከቦች አንድ ባንድ ካስተዋወቃቸው በኋላ በደንብ እንዲዘጋጁ አደረጋቸው፡፡ በውድድሩ ወቅትም አበበ ቢቂላ በሁለት ሰዓት ከአስራ አምስት ደቂቃ ከአስራ ስድስት ነጥብ ሁለት ሴኮንድ/2፡15፡16.2/ በማጠናቀቅ የአለምን ክብረ ወሰን ሰብሮ የወርቅ ሚዲያን ማግኘት ቻለ፡፡

አበበ ቢቂላ በተከታታይ ውድድሮችን እያሸነፈ ክብረ ወሰኖችን በእጁ እያስገባ ብቃቱንና ተደናቂነቱን ከፍ ማድረግ ቻለ፡፡ ለአብነትም ጥቅምት አስራ አንድ ቀን 1957ዓ.ም የጃፓን ቶኪዮ ኦሎምፒክ ላይ ሁለት ሰዓት ከአስራ ሁለት ደቂቃ ከአስራ አንድ ነጥብ ሁለ /2፡12፡11.2/ በመግባት የራሱን ክብረ ወሰን

ማሻሻል ችሏል፡፡ በዚህም ወደ ሀገሩ ሲመለስ ከንጉሰ ነገስቱ የሻምበልነት ማዕረግንና አዲስ ቮልስዋገን ቢትል መኪና መቀበል ችሏል፡፡

ሻንበል አበበ ቢቂላ ሮምን የወረረው ብቸኛው ወታደር ከተወዳደረባቸው አስራ አምስት ውድድሮች አስራ ሁለቱን በአንደኝነት ማጠናቀቅ ችሏል፡፡ ኢትዮጵያዊ ጀግና በተወለደ በስልሳ አንድ አመቱ የሜክሲኮውን ሩጫ አቋርጦ መንገድ ዳር በወደቀ በስድስት አመቱ ጥቅምት 1966 ዓ.ም የህይወት ትግሉን ጨርሶ ከዚህ አለም በሞት ተለየ፡፡ የቀብር ስነ ስርአቱም ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃ/ስላሴ፣ ዘመድ ወዳጆቹና አድናቂዎቹ በተገኙበት በቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ተከናውኗል፡፡

ምንጭ፡-አበበ ቢቂላ የተወለደው መቼ ነው በሚል ጋዜጠኛ ሄኖክ ያሬድ በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ነሀሴ አምስት 2005ዓ.ም ከቀረበው ፅሁፍ ለማስተማሪያነት በሚያመች መንገድ ተሸሽሎ የተወሰደ፡፡

- ያዳመጡትን ታሪክ በቃላቸው በድርጊት ቅደም ተከተል እንዲተርኩ ያበረታቷቸው፡፡ በመቀጠል ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎችን በማሰራትተማሪዎች ያዳመጡትን ምንባብ በትክክል ሀሳቡን ተረድተው መግለፅ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡ ያዳመጡትን ምንባብ መልዕክት ያልተረዱት ከሆነ በድጋሜ በማንበብ መልዕክቱን እንዲጨብጡት ለማስቻል ጥርት ያድርጉላቸው፡፡

## ❖ክፍል ሁለት፡- ንባብ

- አንብቦ መረዳት በሚለው ክፍል የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በቡድን ሆነው ውይይት እንዲደርጉ ይግለጹላቸው፡፡በውይይቱ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡የተወያዩትን ሀሳብ እንዲገልፁ ካደረጉ በኋላ ምንባቡን በግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡ በንባብ ወቅት በፅሁፉ ውስጥ ያሉ ስርዓተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድተው ድምፀቱትን ጠብቀው እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡
- ተማሪዎች በግላቸው በሚያነቡበት ጊዜ ለማንበብ የሚቸገሩ(ማየት የተሳናቸው) ተማሪዎች ካሉ የሚያግዟቸውን ተማሪዎች መመደብ አይዘንጉ፡፡
- ከንባብ በኋላ የስርዓተ ነጥብ አነባበብ ድምፀት ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን ለማረጋገጥ አንድ ወንድ አንዲት ሴት ተማሪዎች በተራ ድምፅ አውጥተው እንዲያነቡ በማድረግ ድምፀቱን ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን ይፈትሹ፡፡
- ተማሪዎቹ በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ካረጋገጡ በኋላ ወደ ቀጣይ ተግባር ይሸጋገሩ፡፡ ስህተቶች ካሉ ግን እርስዎ በአርአያነት ያንብቡላቸው እና የእርስዎን አነባበብ ተከትለው በድጋሜ እንዲያነቡ በማድረግ ትምህርቱን ያጠናክሩ፡፡
- ከምንባቡ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ማብራሪያ እንዲሰጡ፣ ለተዘረዘሩት ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሰርት ተመሳሳይ እና አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያግዟቸው፡፡ ተማሪዎቹ ምንባቡን ካነበቡ በኋላ በጥያቄዎች ላይ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸውንና በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡ በሰጡት ምላሽ ላይ ስህተቶች ካሉ ተገቢውን እርማት በቡድን በቡድን ሆነው እንዲያስተካክሉ ያድርጉ፡፡

## በናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### መልመጃ አንድ፡-

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ሀሴት፣ፍስሃ

ለ. ጥንካሬ

ሐ. የበለጠ

መ. ምሳሌ

ሠ. በግብርና የሚተዳደር

ረ. ሁልጊዜ

ሰ. ስኬታማ

ሸ. ተቃርኖ

ቀ. ደስታ

### መልመጃ ሶስት፡-

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. የካበተ ዕውቀት፣ችሎታ

ለ. ታዋቂ፣በበጎ ስራ የሚታወቅ

ሐ. የተሻሻለ ድል

መ. ተወዳጅነት፣ተከባሪነት

ሠ. መሪ፣ ዋና

ረ. ተደጋጋሚ ስኬት

ሰ. የክብር ሽልማት

ሸ. ቦታ

# ❖ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ

- በክፍል ሶስት የቀረበው ይዘት ቃላት ሲሆን ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ፣ከቀረበላቸው ቃላት ውስጥ ዋና ቃልና ቅጥያ ለይተው እንዲፅፉ እና ከተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ ተመሳሳይ ቃላትን ለይተው እንዲመርጡ የሚያግዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡
- በመጀመሪያ ተማሪዎቹ የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ ምንነት እንዲያስታውሱ በጥያቄ ያነቃቋቸው፡፡ ከዚያም በተማሪው መማሪ መጽሐፍ ውስጥ በተግባር አንድ ስር ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን እየመረጡ እንዲያዛምዱ ይግለጹላቸው፡፡
- በተግባር ሁለት ስር የቀረቡትን ቃላት ዋና ቃሉንና ጥገኛ ምእላዱን እየነጠሉ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- ተግባራት ሶስት ስር ለቀረቡት ቃላት ደግሞ ይበልጥ በፍቺ የሚመስለውን መርጠው እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- በመጨረሻም ዋና ቃሉንና ቅጥያውን እያጣመሩ ቃላት እንዲመሰርቱ ያስረዷቸው፡፡ በአንድ እንዲተገብሩ ይግለፁላቸው፡፡
- የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መመለሳቸውን ያረጋግጡ፡፡ ያልመለሱት ጥያቄ ካለ ማስተካከያ መልስ ይስጧቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

## በናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### መልመጃ አንድ

በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡትን ቃላት በ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት በፍች የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ

| | |
|---|---|
| 1. መ | 6. ሀ |
| 2. ረ | 7. ሽ |
| 3. በ | 8. ሠ |
| 4. ሐ | 9. ሰ |
| 5. ቀ | 10. ለ |

### መልመጃ ሁለት፡-

የሚከተሉትን ቃላት በቀረበው ምሳሌ መሰረት ዋና ቃሉን እና ቅጥያውን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

1. ከ - ተ - ወዳዳሪ - ዎች - ኡ
2. መረጥ - ኣችሁ
3. ጓደኛ - ኦች - ኣቸው - ን
4. ውጤት- ኣማ - ነት - ኣችን
5. ስኬት - ኣማ - ነት
6. ሀገር-ኣችን
7. ወታደር- ኦች-ኣችን
8. ቤት -ኣቸው- ን
9. ሰው -ኦች-ኡ

## መልመጃ ሶስት፡-

ከዚህ ቀጥሎ ከ ተራ ቁጥር ከ1- 6 ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ መልሱ፡፡

1. መ
2. ሐ.
3. መ
4. መ
5. ሀ
6. ለ

## መልመጃ አራት

ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ቅጥያዎች በማገጣጠም ቃላት መስርቱ፡፡

ሀ. ዘመናዊነት

ለ. ክብርት

ሐ. ወጣቱ

መ. ሴትዮዋ

ሠ. ሸጡት

ረ. በጥልቀት

ሰ. በአደገችበት

# ❖ክፍል አራት፡- ጽህፈት

## አንቀፅ መፃፍ

- በዚህ ክፍል የቀረበው አንቀጽ የማዋቀር ይዘት ነው፡፡ ይህንን ይዘት በምዕራፍ አንድ የአምስተኛ ክፍል የቀደመ እውቀታቸውን ተጠቅመው አንቀጽ ለመፃፍ የሚያስችላቸውን ቢጋር በማዘጋጀት አንቀጽ ለመፃፍ ሙከራ ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡በምዕራፍ አንድ ላይ የሞከሩትን የአንቀጽ አፃፃፍ ልምምድ በምእራፍ ሁለት አጠናክረው የአንቀጽ ምንነትንና ክፍሎችን ለይተው እንዲገነዘቡ ይጠበቃል፡፡
- ስለዚህ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን የአንቀጽ ማስታዋሻ እስኪረዱ ድረስ በደብተራቸው እንዲጽፉ በማድረግ እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡ በተጨማሪም በጥያቄና መልስ ያንቀጽ ምንነትንና ክፍልን በሚገባ እንዲገልፁ የማጠናከሪያ አጭር ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚህ ቀድም ስለአንቀጽ ያላቸውን እውቀት እና አሁን የተሰጣቸውን ማብራሪያ ተጠቅመው ከተሰጣቸው ርዕስ አንዱን በመምረጥ ቢጋር አዘጋጅተው አንቀጽ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- የፃፉትን አንቀጽ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተቀያይረው እንዲያነቡና ትችት እንዲሰጣጡ ይግለፁላቸው፡፡ ያቀረቡትን ትችት ትክክለኝነት ካረጋገጡ በኋላ በናሙናነት የተመረጠ አንቀጽ ከተማሪዎቹ በመምረጥ ያስቅርቡላቸው፡፡ በተሰጣቸው ማስተካከያ የፃፉትን አንቀጽ ደግመው አሻሽለው እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች አሻሽለው የፃፉትን በመሰብሰብ በአንቀጽ ውስጥ መካተት ያለበትን ሀሳብ ተካቶ መቅረቡን፣ በተገቢው ቦታ ስርዓተ ነጥብ መጠቀማቸውን፣ የአንቀጽ ክፍሎችን በትክክል ማዋቀር መቻላቸውን ይፈትሹ፡፡ የመፃፍ ክሂል በድግግሞሽ የሚገኝ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ተደጋጋሚ ተግባር በመስጠት ልምምድ እንዲያደርጉ ይርዱአቸው፡፡

**መርጃ መሳሪያ**

**የተዘጋጀ የአንቀጽ ክፍሎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

## ❖ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### የወል ስሞች

- በምዕራፍ አንድ ክፍል አምስት ላይ የተጸውዖና የወል ስም መማራቸው ይታወሳል፡፡በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎቹ ቅድመ እውቀታቸውን ተጠቅመው ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የወል ስም የሆኑትን ለይተው እንዲያሳዩ፣ በራሳቸው የወል ስሞችን ፈልገው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ፣ ከተዘረዘሩት ስሞች ውስጥ የወል ስሞችን ለይተው እንዲያሳዩ የሚለማመዱበት ተግባር ቀርቧል፡፡
- በመጀመሪያ የወል ስምን እንዲያስታዉሱ በጥያቄና መልስ የከልሱላቸው፡፡ ከዚያም ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች የወል ስም የሆኑትን ለይተው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠል የወል ስም የሆኑ ቃላትን ፈልገው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያስረዷቸው፡፡
- ተዘርዝረው ከቀረቡት የተለያዩ ስሞች ውስጥ የወል ስም የሆኑትን ብቻ ለይተው እንዲያሳዩ ያበረታቷቸው፡፡ የሰጡትን መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ የወል ስሞችን በትክክል መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በመጨረሻም ከዚህ በታች የቀረበውን የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት በተመለከተ ተማሪዎች ማስታወሻ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡ ከዚያም በምሳሌው መሰረት የተለያዩ የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎቶችን በተመከለተ የተለያዩ መልመጃዎችን በመስጠት ያሰሯቸው፡፡

## የጥገኛ ምዕላድ አገልግሎት

ጥገኛ ምዕላድ የተለያ ሰዋስዋዊ አገልግሎት ያላቸው ሲሆን የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

1. ባለንብረትነትን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

ገንዘብ-ኤ- ገንዘቤ - የእኔ

ገንዘብ-ኣችን-ገንዘባችን- የእኛ

ገንዘብ-ሽ ገንዘብሽ -ያንቺ

2. ብዙ ቁጥርን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

| ነጠላ ቁጥር | ጥገኛ ምዕላድ | ብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| በሬ | ዎች | በሬዎች |
| ፈረስ | ኦች | ፈረሶች |
| ከበደ | እነ | እነከበደ |

3. ወገንን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ኬንያ | -ኣዊ | ኬንያዊ |
| አፍሪካ | -ኣዊ | አፍሪካዊ |
| ኢትዮጵያ | - ኣዊ | ኢትዮጵያዊ |

4. እምርነትን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

| ስም | ጥገኛ ምዕላድ | እምር ስም |
|---|---|---|
| ልጅ | -ኡ | ልጁ |
| በግ | -ኡ | በጉ |

5. ጾታን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ቆንጆ | -ኢት | ቆንጂት |
| ሙሽራ | -ው | ሙሽራው |
| ልጅ | -ኢት | ልጂት |

6. የአይነት ገላጭን ያመለክታሉ

ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| አሸዋ | -ኣማ | አሸዋማ |
| ተራራ | -ኣማ | ተራራማ |
| ድንጋይ | -ኣማ | ድንጋያማ |

## ለናሙናነት ለተመረጡ መልመጃዎች የቀረበ መልስ

### መልመጃ አንድ፡-

በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የወል ስሞች ለይታችሁ አውጡ።

ሀ. ተማሪዎች፣ ክፍል

ለ. እድር፣ሰዎች፣አካባቢ

ሐ. መኪና፣ እንስሳት፣ሰዎች

መ. ቅርሶች

ሠ፣ እፅዋት

### መልመጃ ሶስት

በምዕራፍ አንድ በተማራችሁት መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የስም አይነቶች የወል ስሞችን ብቻ ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ዓሳ ቅርስ

ልጅ ወንበር

ሰው

### መርጃ መሳሪያ

ለወል ስሞች የተዘጋጀ ሰንጠረዥ

# ምዕራፍ ሶስት

## ቃላዊ ግጥም

ክፍለ ጊዜ 18

❖ የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች፡-

✓ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ በመስጠት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡

✓ ግጥም ጽፈው በትክክል ያነባሉ፡፡

✓ ቅንፍንና እዝባርን በአረፍተ ነገር ውስጥ ይጠቀማሉ፡፡

✓ አዳዲስ ያወቁትን ቃላት በመጠቀም ገላጭ ፣ተራኪና ቃላዊ ግጥም በመጻፍ በጮክታ ያነባሉ፡፡

❖ የምዕራፉ ይዘቶች

- ማድመጥና ግጥም መግጠም
- ግጥም አስመስሎ ማንበብ
- የግጥም ጭብጥ መጻፍ
- ቅንፍና እዝባር
- ተቃራኒ ቃል

# ❖ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## የእርሻ ጊዜ ቃላዊ ግጥም

### ✓ የትምህርቱ አቀራረብ

➢ መምህር ወደእለቱ ትምህርት ከመሄድዎ በፊት የሚከተለውን ቃላዊ ግጥም በማንበብ ተማሪዎቹን ያነቃቁ፡፡

እቴሜቴ የሎሚ ሽታ፣
ያሰውዬ ምን አለሽ ማታ፣
ምንም ምንም ምንም አላለኝ፣
ትዳሩን ፊቶ ልውሰድሽ አለኝ፣
አይወስድሽም ትዳሩን ፈትቶ፣
ምሎልሻል ጋሻ ጦር ደፍቶ፣
ማላ ማላ የጎበዝ ማላ፣
ፉት ይላታል እንደጉሽ ጠላ፡፡

➢ ያነበቡላቸው ግጥም ምን አይነት ግጥም እንደሆነ እንዲለዩ ይጠይቋቸው፡፡ የሰጡት መልስ ትክክል ይሁንም አይሁንም ማስተካከያ ሳይሰጡ ከቀጣዩ ትምህርት በኋላ ሊያውቁት እንደሚችሉ በመንገር ወደቀጣዩ ስራ ይሂዱ፡፡

➢ በመቀጠል በመምህሩ መምሪያ ላይ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም ከማስደመጥዎ በፊት በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በቃል እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡

➢ በመጀመሪያ የቃላዊ ግጥም ምንነት እንዲገልጹ ይጠይቋቸው፡፡ ተማሪዎቹ የሚሰጡትን መልስ ተቀብለው ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ ሳይሰጡ

ወደቀጣዩ ጥያቄ ይለፉና በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ስዕል ተመልክተው የተረዱትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

- በመቀጠልም ቀድሞ እርስዎ እንዳቀረቡላቸው አይነት ግጥም የሚያውቁት ካለ ለወንዶቹም ለሴቶቹም ዕድል በመስጠት ሙከራ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡
- ከዚያም በማዳመጥ ጊዜ ለመመለስ እንዲያግዛቸው ያዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ቀድመው ደጋግመው እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡
- ተማሪዎቹ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡና ሲዳምጡ አዳዲስ ቃላትን እንዲጽፉ በመንገር የሚደመጠውን ቃላዊ ግጥም በዝግታ አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡

## በእርሻ ጊዜ የሚገጠም ቃላዊ ግጥም

የበሮቹ ቁስ የበሬው መምህር
አቆላላፊ ክምር በክምር፡፡
ሐምሌ ነሐሴ ያልተራበ ሰው
ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው፡፡
ጀርጃራው ፈንዛ ባንተ አልደረስኩም
ያሸኮበኩባል ጮሌው እንደርኩም፡፡
ሚያዚያ ግው ሲል ግንቦት ሲያገሳ
አከናናቢ ጎድጓዳ ማሳ፡፡
ሆ ይላል ገበሬ
ሆ ይላል ገበሬ
ዲብ እያፈረሰ በሽልማ በሬ፡፡
በርዬ በርዬ
አንተን የቻለ ሰው
ቶሎ ቶሎ ብለህ

አንጆቴን አርሰው
እረኛህ ያለቅሳል
ምሳ እያነሰው፡፡
በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጅ
እንዲያ ስተትብሎ ይጠመዳል እንጂ
እረስ ሽልም እረስ መጋል
እንድን በላ ገብስ እንድንለሰልስ፡፡

- ሲያዳምጡ የጻፏቸው አዳዲስ ቃላት ካለ ይጠይቋቸውና በረሳቸው መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡በራሳቸው መመለስ ካልቻሉ እርስዎ መልሱን ይግለጹላቸው፡፡
- በመቀጠል ባዳመጡት ግጥም መሰረት ያልተሟሉ ስንኞችን እያስታወሱ አሟልተው እንዲጽሁ ያበረታቷቸው፡፡
- በትክክል ያላሟሉት ስንኝ ካለ ለሁለተኛ ጊዜ ግጥሙን በማንበብ እያዳመጡ እንዲያሟሉ ያድርጉ፡፡
- ለሶስተኛ ጊዜ ያላሟሉት ካለ እያስታወሱ እንዲጽፉ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም እርስ በርስ እንዲተራረሙ በማድረግ በትክክል መስራታቸውን ለማረጋገጥ በቃል እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪ ተግባሩን በትክክል መስራቱን ይፈትሹ፡፡
- ካዳመጡት ግጥም ውስጥ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ሰጥተው ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- በቀረቡት አዳዲስ ቃላት አረፍተ ነገር መመስረት መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡
- በመጨረሻም በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም ያዳመጡትን አነባበብ ስልት ተከትለው በማንበብ የግጥሙን ጭብጥ እንዲናገሩ ያግዟቸው፡፡

## ❖ክፍል ሁለት፡- ንባብ

- ወደማንበብ ተግባረር ከመግባታቸው በፊት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ከተወያዩ በኂላ የሚያውቁትን የፍቅር ቃላዊ ግጥም ካለ በቃላቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- የቃላዊ ግጥሞች ማህበራዊ ፋይዳ ምን ሊሆን እንደሚችል በውይይቱ ያገኙትን ሀሳብ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- የሙሾ እና የሰርግ ቃላዊ ግጥሞች የሚኖራቸውን ልዩነት ምን እንደሆነ እንዲያብራሩ ይግለጹላቸው፡፡
- በመጀመሪያ ምንባቡን ለማንበብ ጥንድ ጥንድ ሆነው ለማንበብ ያዘጋጇቸው፡፡
- አንዱ ሲያነብ ሌላው እያዳመጠ የሀረግ አከፋፈልንና ዜማን ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን እያረጋገጡ እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡
- በዚህ ጊዜ በምንባቡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች በክፍል አንድ ማዳመጥ ላይ ባደረጉት የግጥም ንባብ ልምምድ ድምፀቱን ጠብቀው ማንበብ መቻላቸውን ይገምግሙ፡፡
- በተግባር አንድ የቀረበውን የእውነት ሐሰት ጥያቄ በምንባቡ መሰረት ምክንያት እየሰጡ በጽሑፍ እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡
- እንዲሁም በምርጫ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጡ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- የሰጡት ምላሽ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ እያንዳንዱን ተማሪ በመጠየቅ ይፈትሹ፡፡
- በተማሪዎች ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ እርስዎ ያስረዷቸውና ማስተካከያውን እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

- በመጨረሻም በመጽሐፋቸው ውስጥ የቀረበውን ተራኪና ገላጭ ድርሰት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው።

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች

## መልመጃ ሁለት፡-

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ለ
2. ሐ
3. ሀ
4. ሐ
5. መ
6. ለ
7. ሐ

# ❖ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## አዳዲስ ቃላት

- ከዚህ በፊት በምእራፍ አንድና ሁለት የተማሩትን የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እንዲያስታዉሱ በማድረግ በዚህ ክፍል ደግሞ ስለ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንደሚማሩ ያስተዋውቋቸው።
- ከዚያም የቃላት ተቃራኒ ፍቺ ምን እንደሆነ ይግለጹላቸው።
- ተግባር አንድ በአዛምድ መልክ ለቀረቡት በ‹‹ሀ›› ስር ላሉት ቃላት ተቃራኒ በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት እየመረጡ እንዲመልሱ ያስረዷቸው።
- በተግባር ሁለት በምርጫ ለቀረቡት ጥያቄዎች ለተሰመረባቸው ቃላት ተቃራኒ የሆኑትን እየመረጡ እንዲመልሱ ይግለጹላቸው።
- መልሳቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ።

- ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች

## መልመጃ አንድ

በ‹‹ሀ››ረድፍ ለቀረቡትቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ‹‹ለ››ረድፍ በመምረጥ በትክክል አዛምዱ፡፡

1. ሠ
2. ሰ
3. ሸ
4. ለ
5. ሀ
6. ሐ
7. መ

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ትርጉም ያላቸውን ፊደል ብቻ ምረጡ፡፡

1. ሐ
2. ለ
3. ሐ
4. መ
5. ለ

## መርጃ መሳሪያ

- የቃላት ተቃራኒ ፍቺ የያዘ ሰንጠረዥ
- የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በንጽጽር የያዘ ሰንጠረዥ

## ❖ክፍል አራት፡- ጽህፈት

### ቅንፍና እዝባር

- መመህር ስለቅንፍና እዝባር ስርአተ ነጥብ ምንነትና አገልግሎት በተማሪዉ መጽሐፍ የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ጽፈው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- አንብበው ሲያጠናቅቁ ምን እንደተረዱ በመጠየቅ፣ በሰጡት መልስ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- በተግባር አንድ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች እዝባር ተጠቅመው አሳጥረው እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- ከዚያም በተግባር ሁለት በተሰጣቸው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የቅንፍን ስርአተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ ተጠቅመው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡
- የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠታቸውን ይገምግሙ፡፡
- በትክክል መልስ ከሰጡ መልካም ካልሆነ ግን እርስዎ ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸውና እርማት እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡
- ከቀረበላቸው ርዕስ አንዱን መርጠው ግጥም እንዲጽፉና ስርአተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታ እንዲጠቀሙ ይግለጹላቸው፡፡
- የግጥም አጻጻፍና የስርአተ ነጥብ አጠቃቀማቸውን እንዲገማገሙ የጻፉትን ግጥም ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲቀያየሩ ያድርጉ፡፡
- የጓደኞቻቸውን ግጥም ገምግመው ሲያጠናቅቁ ያገኙትን ጠንካራ ጎን እና መሻሻል ያለባቸውን ሀሳቦች እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ተማሪዎቹ የሰጡትን አስተያየት መሰረት ያደረገ የማስተካከያ አስተያየት ይስጧቸው፡፡
- በመጨረሻም የትምህርቱን ማጠቃለያ ሰጥተው ያጠናቁ፡፡
- ተማሪዎች በሚፈልጉት ርእስ ዙሪያ ግጥም መጻፍ እንዲለማመዱ ይግለጹላቸው፡፡

# ❖ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## የጊዜ ተውሳከ ግስ

- በተማሪው መጽሀፍ የቀረበውን የጊዜ ተውሳከ ግስ ማስታወሻ ጽፌው እንዲያነቡ ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- ከዚያም የጊዜ ተውሰከ ግስ አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት የሚገልጽ መሆኑን ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- በማስከተል ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የጊዜ ተውሳከ ግስ ለይተው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ከተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ለይተው በቻርት ውስጥ እንዲያሰፍሩ ያድርጉ፡፡
- በቀረቡላቸው ተውሳከ ግሶች ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ የጊዜ ተውሳከ ግስን አገልግሎት በትክክል መለየታቸውን ይፈትሹ፡፡
- በዚህ ምእራፍ መጨረሻ ላይ የሙከራ ፈተና ቢሰጣቸው መልካም ነው፡፡

### ለናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች

#### መልመጃ አንድ

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

1. ባለፈው አመት
2. በጧት
3. ትናንት
4. ዛሬ ጧት
5. በሚቀጥለው አመት
6. ባለፈው ሳምንት
7. ዘወትር

## ተግባር ሶስት

**ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ለይታችሁ በቻርቱ ውስጥ ጻፉ፡፡**

**ወዲያውኑ አሁን**

**ዛሬ ያለፈው አመት**

**ነገ**

**መርጃ መሳሪያ**

**የጊዜ ተውሳከ ግስ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች የያዘ ቻርት**

# ምዕራፍ አራት

## ዘመናዊ እርሻ

ክፍለ ጊዜ 18

❖ የምዕራፉ አጠቃላይ ዓላማዎች

- ✓ አዳምጠው በቃላቸው ይመልሳሉ
- ✓ አከራካሪ አንቀፅ ይፅፋሉ
- ✓ ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም ይሰጣሉ
- ✓ የጊዜ ግስን ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር ይመሰርታሉ

❖ የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች

- ➢ አዳምጦ የቃል ዘገባ
- ➢ ቃላትን በትርጉም መመደብ
- ➢ አከራካሪ አንቀፅ
- ➢ የጊዜ ግስ

## ❖ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ‹‹ድሮና ዘንድሮ››

### የትምህርቱ አቀራረብ

- መምህር በቅድመ ማዳመጥ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በጥንድ በጥንድ እንዲወያዩበት ጊዜ ይስጧቸው፡፡ ውይይታቸውን ሲያጠናቅቁ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- የገለጹትን ሀሳብ አስደግፈው የሚደመጠውን ርዕስ ያስተዋውቋቸውና በርዕሱ ዙሪያ አንዳንድ ጥቆማ በመስጠት ይበልጥ ለማዳመጥ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያድርጉ፡፡
- ወደማንበብ ከመሄድዎ በፊት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ የቀረበውን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄ እስኪረዱት እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ከዚያም ምንባቡን እያዳመጡ ባዶ ቦታውን እንዲሞሉ ይግለጹላቸውና ምንባቡን አንድ ጊዜ በዝግታ ያንብቡላቸው፡፡

ስሜ መስታወት ተበጀ ይባላል፡፡ ተወልጄ ያደኩት እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ትምህርቴን እስከ መጨረሻው መቀጠል አልቻልኩም ነበር፡፡ እናቴ ከአከፋፋዮች አትክልትና ፍራፍሬ ተረክባ ጉልት ላይ በመቸርቸር በምታገኛት ገቢ እንተዳደር ነበር፡፡አባቴ ደግሞ በቀን ስራ ተሰማርቶ የጉልበት ስራ ይሰራ ነበር፡፡ሆኖም ከሁለቱም የሚገኘው ገቢ ከዕለት ጉርስ የሚተርፍ አልነበረም፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደሚባለው አባቴ በስራ ቦታ በደረሰበት አደጋ በህክምና ቢረዳም ሊተርፍ ባለመቻሉ እኛን ተሰናብቶን ሄደ፡፡

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እናቴን የማገዝ ሀላፊነቱ በኔ ጫንቃ ላይ ወደቀ፡፡ ለምን ተፈጠርኩ ብየ እስካማርር ድረስ ፈተናዎች ሁሉ አንድ በአንድ ይፈራረቁብኝ ጀመር፡፡ የማይተካው የልጅነት ጊዜዬን እንደ አቻዎቼ ተደስቼና ቦርቄ ሳይሆን በስቃይና በፈተና መግፋት ጀመርኩ፡፡ ላያስችል አይሰጥም እንደሚባለው በምችለው አቅም ሁሉ እናቴን በመርዳት ህይወታችንን መግፋቱን ተያያዝነው፡፡ ችግር መፍትሄን ይወልዳል እንዲሉ ከዕለታት በአንዱ ቀን የስራ እድል ፈጠራ ስልጠና ለመውሰድ ከተመዘገብኩበት መስሪያ ቤት ስልክ ተደወለልኝ፡፡ እንዴት ስበርር እንደደረስኩ አላውቅም፡፡ ብቻ ከቦታው ስደርስ ለስራ ፈጠራ ስልጠና ሊሰጠኝ መሆኑን ስሰማ ወዲያውኑ እኔና እናቴ ከችግራችን የምንወጣበት የብርሃን ጭላንችል ብሩህ ሆኖ ታየኝ፡፡ ስልጠናውም እንዴት ሰርቶ መለወጥ እንደሚቻል የሚያስተምር ስለነበር ጆሮየን የኮረኮሩኝ ያህል በንቃት ነበር ስከታተለው የነበረው፡፡ በስልጠናውም በከተማችን ከሚሰሩ የተለያዩ የስራ መስኮች መካከል አንዱ የከተማ ግብርና እንደሆነ ተረዳሁ፡፡

የከተማ ግብርና በአነስተኛ ቦታ፣አቅምና ጉልበት ብዙ ምርት ማስግኘት የሚያስችል፣በዘመናዊ አሰራር የተደገፈ ውጤታማ ስራ ነው፡፡በችግር እንድንኖር ያስገደደንን አስከፊ ድህነት ከላያችን ላይ ለማራገፍ በወሰድኩት ስልጠና እና ባገኘሁት አነስተኛ ብድር ባለን የጓሮ መሬት ላይ እንደ ጎመን፣ሰላጣ፣ካሮት፣ ቲማቲም፣ቀይስር፣ሙዝ፣ብርቱካንና ፓፓያ የመሰሳሰሉትን አትክልትና ፍራፍሬዎች ለማምረት ወደስራ ገባሁ፡፡ለማመርታቸው ምርቶች ውጤታማ ሊያደርጉኝ የሚያስችሉ የተለያዩ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ማለትም

የአፈር ማዳበሪያ፣ምርጥ ዘርና ፀረ ተባይ … ወዘተ መጠቀም ጀመርኩ፡፡በዚህም በትንሽ መሬት ላይ ብዙ ምርት ማግኘት ቻልኩ፡፡በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ገቢ ማስገኛና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የአመጋገብ ስርዓትን በማስተካከልና መሰል ችግሮችን ለማቃለል ያገኘሁትን ልምድ በመጠቀም በአቅራቢያዬ ላሉ ነዋሪዎች ማስተማር ጀመርኩ፡፡

ሰርቼ ከማገኘው ገንዘብ ከእለት ፍጆታ የሚተርፈንን በባንክ ማስቀመጥ ጀመርኩ፡፡የሚገኘው ምርት እያደገ ሲመጣ አነስተኛ ሱቅ በመክፈት እናቴ የጉሊት ስራዋን አቁማ ሱቁ ላይ እንድትሰራ ማድረግ ቻልኩ፡፡የአትክልትና ፍራፍሬው ምርት በጣም እያደገ ሲመጣና ከከፈትነው ሱቅ የምናገኘው ገቢ ሲጨምር ባለቤቴ የተሻሻሉ የወተት ምርት የሚሰጡ ላሞችን ገዝቶ መስራት ጀመረ፡፡የወተት ምርቱም በጣም ተፈላጊነቱ እየጨመረ ስለመጣ በምናገኘው ገቢ የኑሮ ዘይቤያችንም እየተሻሻለ መጣ፡፡ ከራሳችን አልፈን ለሌሎች የስራ እድልን መፍጠር ቻልን፡፡

በአሁኑ ሰዓት ከአከፋፋዮች ተረክበን ጉልት ላይ ከመቸርቸር አልፈን ባስመዘገብነው ውጤት በአካባቢያችን ላሉ አትክልትና ፍራፍሬ መደበሮች ምርታችንን በማቅረብ ቋሚ ደንበኞችን ማፍራት ቻልን፡፡ከከተማ ግብርና ሌላውና ዋነኛው የስራ ዘርፍ የእንስሳት እርባታ ሲሆን ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል አጭር ስልጠና ወስዶ ሊሰማራበት የሚችል እና የሥራ ዕድል ለመፍጠርም የሚያስችል መስክ ነው፡፡በመሆኑም እኔና ባለቤቴ በተከራየነው ትንሽ ቤት ውስጥ እየሰራን ያለነው የወተት ምርቱ መጠን እየጨመረ ሲመጣ ለሌሎች የምናከፋፍለውን ከመንግስት ብር ተበድረን በመጨመር የወተት ተዋፅዖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በመገንባት መስራት ጀመርን፡፡ በዚህም የስራ እድል የፈጠርንላቸው ግለሰቦች ቁጥር በእጅጉ ጨመረ፡፡ በአሁኑ ወቅት የተጋረጠብንን ድህነት አሸቀንጥረን በመጣል ለበርካታ ሰዎች የስራ እድል

በመፍጠር እና በከተማው የሚስተዋለውን የወተትና የአትክልት አቅርቦት ለማሻሻል የበኩላችን እየተወጣን እንገኛለን።

- በመጀመሪያ ማዳመጥ ጊዜ ምን ያህሉን ጥያቄ እንደመለሱ ይጠይቋቸው። ከዚያም ድጋሜ ማንበብ አስፈላጊ ሆኖ ከታየዎት ድጋሜ ያንብቡላቸው። በሁለት ጊዜ ማዳመጥ ሙሉ በሙሉ መመለስ ያልቻሉ ተማሪዎች ካሉ ከታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸውና ያዳመጡትን በማስታወስ ባዶ ቦታውን እንዲሞሉ ያግዟቸው።

በጠመኔ ሰሌዳ ላይ የሚጻፉት ቃላትና ሀረጋት

ጫንቃ ላይ
ከተመዘገብኩበት
የከተማ ግብርና
አቻዎቼ
የተስፋ ጭላንጭል
በባንክ ማስቀመጥ
ማቅረብ
እየጨመረ

- በመጨረሻም ካዳመጡ ምንባብ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረትዓረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። መስራታቸውን ለማረጋገጥ እያንዳዳቸው የሰሩትን እንዲናገሩ በማድረግ ይፈትሹና የዕለቱን ትምህርት ያጠናቁ።
- በመጨረሻም በተግባር አራት ስር የተገለፀውን ጥያቄ ተማሪዎች ከዝቅተኛ ገቢ እንደት ወደ ከፍተኛ የገቢ መጠን ማደግ እንደሚቻል በቡድን እንዲወያዩ ያድርጓቸው።በመቀጠልም በቡድን የተወያዩትን ሀሳብ በየተራ

እየወጡ ንግግር እንዲያደርጉ ይርዷቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ንግግር አድርገው እንደጨረሱ እርስዎ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡

## ❖ ክፍል ሁለት፡- ንባብ

- መምህር ወደዕለቱ ትምህርት ከመግባትዎ በፊት ከታች የቀረበውን ግጥም ለተማሪዎቹ በማንበብ ያነቃቋቸው፡፡መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ግጥሙን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉና እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡

እስኪ ላመስግንህ እንዲህ ልበልና፣
የሀገር ምሶሶ አለይኝታ ነህና፡፡
ደከመኝ ሰለቸኝ ፊፅሞ ማታውቀው፣
የሁሉንም ጎጆ ኩራት ያለበስከው፡፡
ሁሉም ተደስቶ ስቆ ሚቦርቀው፣
አንተነህ ገበሬ መሰረት የሆንከው፡፡

- በመቀጠል የዕለቱን የንባብ ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም በቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡
- ምንባቡን በግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡና የሚያጋጥማቸውን አዳዲስ ቃል በደብተራቸው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ንባባቸውን ሲያጠናቅቁ የጻፏቸውን አዳዲስ ቃላት ይጠይቋቸውና በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ፡፡ ለቀረቡት አዳዲስ ቃላት በራሳቸው ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ ከዚያም ከጓደኞቻቸው ጋር በጋራ እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም ለመመለስ ያዳገታቸውቃል ካለ ትክክለኛ መልስ ይስጧቸው፡፡

- ከምንባቡ የወጡ ቃላት በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ በምንባቡ ውስጥ እና ከምንባቡ ውጭ ባላቸው ፍቺ ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ይግለጹላቸው፡፡
- የቃላትን አገባባዊ እና ከአገባብ ውጪ ያለውን ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር በመጻፍ በምሳሌ አስደግፌው ያስረዷቸው፡፡

ምሳሌ1= በመዘርጋት የሚለው ቃል በምንባቡ ውስጥ ያለው ፍቺ

- ዘነበ ዘመናዊ የግብርና ዘዴ በመዘርጋት ውጤታማ መሆን ችሏል፡፡

ከምንባቡ ውጪ

- ሰናይት ገመድ በመዘርጋት ልብሷን አሰጣች፡፡

ምሳሌ 2= በማሳደግየሚለው ቃል በምንባቡውስጥያለው ፍቺ

- እያንዳንዱ ግለሰብ የከተማ ግብርናን በመጠቀም የቀን ገቢውን በማሳደግ ህይወቱን መቀየር ይችላል፡፡
- ሁሉም ማህበረሰብ ወላጅ አልባ ህጻናትን በማሳደግ ተግባር መሳተፍ አለበት፡፡

- ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ተጨማሪ ዓረፍተ ነገሮችን በመጻፍ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡
- በምርጫ መልክ የቀረበውን ጥያቄ በደብተራቸው እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የሰሩትን ተመልክተው ትክክለኛ መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡ የፈጸሙትን ስህተት ለይተው የማስተካከያ መልስ ይስጧቸው፡፡
- በግቢያቸው ወይም በአካባቢያቸው የሚካሄድ የግብርና ሥራ ካለ ምን አይነተ ግብርና እንደሆነ በመጥቀስ አመራረቱንና ያለውን ጠቀሜታ

ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀው በመምጣት በክፍል ውስጥ የቃል ዘገባ እንዲያቀርቡ ይግለጹላቸው፡፡

- የሰበሰቡትን መረጃ አለፍ አለፍ እያሉ የተማሪዎችን ስም በመጥራት በክፍል እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው፡፡ ላከናወኑት ተግባር የማበረታቻ ቃል በመጠቀም ቀጣይ ልምምድ እንዲያደርጉድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡
- የክርክር ርዕሱን በማሳወቅ በተማሪዎች ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ቡድን ይመስርቱና ዳኛ በማስመረጥ በቀጣይ ለክርክር እንዲዘጋጁ ያስረዷቸው፡፡ በዝግጅት ጊዜና በአቀራረብ ጊዜ ምን ምን ተግባር ማከናወን እንዳለባቸው ይጠቁሟቸው፡፡
- በተዘጋጁበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ክርክሩን እንዲያካሂዱ ያመቻቹላቸው፡፡ ክርክሩ ሲጠናቀቅ ሲከታተሉ የቆዩትን ታዳሚ ተማሪዎች በክርክሩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ይጋብዟቸው፡፡ በማጠቃለያ የክርክሩን ጠንካራና ደካማ ጎን በማሳወቅ ለቀጣይ የክርክር ጊዜ አሻሽለው እንዲገኙ ያስገንዝቧቸው፡፡
- የቀረበውን የክርክር ዝግጅትና አቀራረብ መነሻ አድርገው የክርክር መመሪያ እንዲያዘጋጁያበረታቷቸው፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### መልመጃ አራት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ለ
2. ሀ
3. ሐ
4. ሀ
5. ለ
6. ሐ
7. ሀ
8. ሐ
9. ለ
10. መ

# ❖ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም መስጠት

በቃላት ትምህርት ሥር የቀረቡትን ተግባራት ከመጀመርዎ በፊት ቃላት ሲመሰረቱ የፊደላት አደራደር ስርዓት መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ያስረዷቸው፡፡ ቃላት ከአደራደር ስርዓት ውጪ ፍቺ መስጠት እንደማይችሉ ከታች የቀረበውን ምሳሌ በመጥቀስ ይግለጹላቸው፡፡

ምሳሌ = ከሆሄ አደራደር ስርዓት ውጪ የተዋቀሩ በስርዓት የተዋቀሩ

| | |
|---|---|
| ሀ. ገራነት | ነገራት |
| ለ. ምዝታ | ዝምታ |
| ሐ. ትከረበ | በረከት |
| መ. ራንችስሁ | ስራችሁ |

በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ ተዘበራርቀው የተደረደሩ ሆሄያትን አስተካክለው ፍቺ የሚሰጡ ቃላትን መመስረት እንዲለማመዱ ይግለጹላቸው፡፡ የመሰረቱትን ቃል እየወጡ ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉ በማድረግ በጓደኞቻቸው እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጉ፡፡

ከቀረበላቸው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላት ለይተው እንዲያወጡ በማድረግ ለቃላቱ ፍቺ በመስጠት በቃላቸው መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡

በመልመጃ ሶስት ስር ለቀረቡት ቃላት ይበልጥ በፍቺ የሚቀርበውን በመምረጥ በደብተራቸው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡የሰጡትን መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ ትክክለኛነታቸውን ይመዝኑ፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ትርጉም የማይሰጡ ቃላት በምሳሌው መሰረት ትርጉም በሚሰጥ መንገድ አዋቅራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ዕውቀትሰ. ሳይታክት

ለ. የዶሮ ወጥሽ. ፈተና

ሐ. ብርሃንቀ. መጽሐፍ

መ. ይመለሳልበ. የተደራሲያን

ሠ. ለመቀጠልተ. ወንበር

ረ. አልማዝ ቸ. ገፀባህርያት

### መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች ባለው አንቀፅ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት አውጥታችሁ ትርጉማቸውን በቃላችሁ ተናገሩ፡፡

- ይነቀንቃሉ
- ያወልቃሉ
- ይሰረስራሉ
- ያብላሉ
- ይቆርጣሉ
- እስካልተመነጠሩ
- አሜከላ
- መጎሹ

### መልመጃ ሶስት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ይሆናሉ ተብለው ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ይበልጥ የሚስማማቸውን ምረጡ፡፡

1. ሐ
2. ለ
3. ሀ
4. መ
5. ሀ
6. ሀ
7. ሐ

## ❖ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### አመዛዛኝ ጽሑፍ

መምህር በዚህ ክሂል ስር ተማሪዎቹ በተለያየ መንገድ አንቀጽ መጻፍ እንዲችሉ የተለያዩ መለማመጃ ተግባራት ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያ የሀሳብ ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀ ዓረፍተ ነገሮችን ቅደም ተከተል አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡የዓረፍተ ነገሮቹ የሀሳብ ቅደም ተከተል በትክክል መስራታቸውን የእያንዳንዱን ተማሪ ተመልክተው እርማት ይስጧቸው፡፡

የሀሳብ ቅደም ተከተላቸው የተስተካከለውን ዓረፍተ ነገሮቹ አገጣጥመው አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አንቀጽ እንዲገነቡ ይግለጹላቸው፡፡

የጻፉትን አንቀጽ ከጓደኞቻቸው ጋር በመለዋወጥ እንዲተራረሙ ያድርጉ፡፡ ከጓደኞቻቸው የተሰጣቸውን አስተያየት መልሰው ራሳቸው እንዲገመግሙ ያድርጉና የመጨረሻውን የተስተካከለ አንቀጽ ለሁሉም ተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ከቀረቡላቸው መንደርደሪያ አረፍተ ነገሮች አንዱን መርጠው አከራካሪ አንቀጽ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

ስለአከራካሪ አንቀጽ ምንነትና አገነባብ ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻና ምሳሌ በደብተራቸው ያጽፏቸውና እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡በተጨማሪ አጭር ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

❖ ማስታዋሻ፡-

አመዛዛኝ (አከራካሪ አንቀፅ)

አመዛዛኝ ወይም አከራካሪ ፅሁፍ ብዙውን ጊዜ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ተቃራኒ ሀሳቦችን በማንሳት አንዱ ከሌላው የሚለይበትን፣የሚመረጥበትን፣የሚልቅበትንና የሚያንስበትን ወዘተ. በተጨባጭ ምክንያት በመዘርዘር አንባቢን ለማሳመን የሚሞከርበት የጽሑፍ አይነት ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ አመዛዛኝ ጽሁፍ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት እያመዛዘኑ፣እያወዳደሩ፣እያከራከሩ፣የማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡ አመዛዛኝ ጽሑፍ አሳማኝ በሆነ ምክንያት አንዱን በመደገፍ ሌላውን በመንቀፍ አንባቢን ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለማሳመን የሚቻልበት ነው፡፡ በንፅፅር የሚቀርቡ ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ እየመረመሩ አንድነትና ልዩነትን፣ጥቅምና ጉዳትን፣ ክፋትና ደግነትን እያወዳደሩ የማቅረቢያ መንገድ ነው፡፡ (አለም እሸቱ፣1999፣76)

ምሳሌ፡- የአከራካሪ አንቀጽ ምሳሌ

ፀጥታና ዝምታ በመዝገበ ቃላት ፍቻቸው ተተካኪ ቢሆኑም መጠነኛ ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል ይገመታል፡፡ፀጥታ፣ሰላም የሰፈነበትን የአዕምሮ እረፍት ያመለክታል፡፡ ሁከትን ሳይሆን ውስጣዊ እርጋታን ስለሚጠቁም ስሜትን ያዝናናል፡፡ፀጥታ አጭር ዕድሜ ያለው ብርቅዬ ስሜት ነው፡፡ዝምታ ግን እፎይታን ላያሳይ ይችላል፡፡ በዝምታ ውስጥ የገዛ ራስ ጉርምርምታ ሊኖር

ይችላል። ዝምታ የአንደበትን ስራ መፍታት እንጂ የሀሊናን እረፍት ላያመለክት ይችላል።በዝምታ ውስጥ የአቅል መበታተንና የስሜት መዶልዶም ሊኖር ስለሚችል ሁለቱን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች አድርጎ መመልከቱ ያስቸግራል። (ሰለሞን ሐለፎም፣ 1997፣196)

- በመጨረሻም ተማሪዎቹ ከላይ በቀረበላቸው ተግባር ጽሕፈትን በተለማመዱት መሰረት አሁን ደግሞ በራሳቸው አከራካሪ ጽሑፍ ለመጻፍ የሚያስችላቸው ርዕስ እንዲመርጡና አከራካሪ በሆነ መንገድ አንቀጽ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው።
- ጽፈው ያመጡትን አንቀጽ እንዲያነቡ በማድረግ የታለመውን የጽሑፍ ክሂል በትክክለል መሳካቱን ይገምግሙ።
- የጽሑፍ ተግባር ሲጠናቀቅ ተማሪዎቹ ባገኙት አጋጣሚ የጽሑፍ ክሂላቸውን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ይግለጹላቸው።

## በናሙና የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

**መልመጃ አንድ**

የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ አንድ አንቀጽ አዋቅራችሁ ጻፉ።

| | |
|---|---|
| 1. ሐ | 5. መ |
| 2. ሽ | 6. ለ |
| 3. ረ | 7. ሠ |
| 4.ሰ | 8. ሀ |

# ❖ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## የጊዜ ግስ

➢ መምህር በዚህ ክፍል የቀረቡትን ተግባራት ከማሰራትዎ በፊት የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎቹ በደብተራቸው ያጽፏቸውና ያስነብቧቸው፡፡ ካነበቡ በኋላ በጥያቄና መልስ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

**የጊዜ አይነቶች**

✓ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የጊዜ አይነቶችን በሶስት ዋና ዋና መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም የአሁን ጊዜ፣ የሀላፊ ጊዜና የትንቢት(የወደፊት) ጊዜ ናቸው፡፡

ሀ. **የአሁን ጊዜ፡-** የምንለው አንድ ድርጊት እየተከናወነ ወይም እየተፈፀመ ያለ እና ድርጊቱ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለመግለፅ የሚያገለግል ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ልጁ ምሳውን እየበላ ነው፡፡

ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እየተጓዙ ነው፡፡

ለ. **የሀላፊ ጊዜ፡-** ይህ የጊዜ አይነት አንድ ድርጊት ተከናውኖ ወይም ተሰርቶ ያለፈ መሆኑን ለመግለፅ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ባለፈው አመት ለጉብኝት ሀዋሳ ሄደው ነበር፡፡

መምህሩ ትናንት ከባህርዳር ተመልሷል፡፡

ሐ. የትንቢት(የወደፊት) ጊዜ፡- ይህ የጊዜ አይነት አንድ ነገር ወይም ድርጊት ወደ ፊት ሊሰራ ወይም ሊፈፀም መሆኑን አስቀድመን የምንተነብይበት መንገድ ነው፡፡

ምሳሌ፡- መቅደስ በሚቀጥለው ወር ዘመዶቿን ለመጠየቅ ትሄዳለች፡፡

በተያዘው አመት ሞዴል አርሶ አደሮች ሊሸለሙ ነው፡፡

- በመቀጠል በተግባር አንድ ስር የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የድርጊት ጊዜ ጽፈው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡ ስህተት ከፈጸሙ እርማት በመስጠት ማስተካከያ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡
- ከዚያም የአወቃቀር ስህተት የሚታይባቸው ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ ስህተቱን ፈልገው በማውጣት እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ከዚህ በፊት ስለ ጊዜ ተውሳከ ግስ የተማሩትን በጥያቄና መልስ ክለሳ ያድርጉላቸው፡፡ በመቀጠል በተግባር ሶስት የቀረቡትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች ዓረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ ያስረዷቸው፡፡
- በመጨረሻም ደብተራቸውን በመሰብሰብ ያርሙላቸውና የፈጸሙት ስህተት ካለ የማስተካከያ መልስ ይስጧቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በመልመጃ አራት የቀረቡትን የጊዜ አመልካች ቃላት የአሁን፣ የሀላፊና የወደፊት በማለት ለይተው በሰንጠረዡ እንዲያሰፍሩ ያግዟቸው፡፡

## በናሙነናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### መልመጃ አንድ

በሚከተሉትን ጥያቄዎች ውስጥ ያሉትን የጊዜ አይነቶች ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. የሀላፊ ጊዜ                መ. የወደፊት ጊዜ

ለ. የሀላፊ ጊዜ                ሠ. የወደፊት ጊዜ

ሐ. የአሁን ጊዜ                ረ. የሀላፊ ጊዜ

ሰ. የአሁን ጊዜ                ሸ. የወደፊት ጊዜ

### መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ሰዋስዋዊ ስህተት የሚታይባቸው ዓረፍ ነገሮች አስተካክላችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ተማሪዎቹ የክፍል ተወካያቸውን መረጡ፡፡

ለ. ጎበዝ ተማሪዎችን ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

ሐ. ማንኛውም ሰው ድህነትን ለማስወገድ ታጥቆ መነሳት አለበት፡፡

መ. ሄለን በስነ ምግባሯ የተመሰገነች ናት፡፡

ሠ. ሁሉም ሰው የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ መከላከል አለበት፡፡

ረ. ትምህርት በሳይንስና ቴክኖሎጂ መደገፍ አለበት፡፡

ሰ. ህብረተሰቡ አጥፊዎችን ለህግ ለማቅረብ መተባበር አለበት፡፤

ሸ. አረጋውያንን መንከባከብ ባህላችን ሊሆን የገባል፡፡

## መልመጃ አራት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት የአሁን ጊዜ፣የሀላፊ ጊዜና የወደፊት ጊዜ በማላት በሰንጠረዥ ውስጥ መድቡ።

| የአሁን ጊዜ | የወደፊት ጊዜ | የሀላፊ ጊዜ |
|---|---|---|
| እየተማረ ነው | ያነባል | ሰጥቷል |
| እየሰራ ነው | ሰላም ይሰፍናል | አንብቧል |
| እየመጣ ነው | ይሰጣል | ሰብሯል |
| እየሰጠ ነው | ይመጣል | ሰላም ሰፍኖ ነበር |
| ሰላም እየሰፈነ ነው | ይሰብራል | መጥቷል |

### መርጃ መሳሪያ

የጊዜ አይነቶችን የሚያሳይ ቻርት

# ምዕራፍ አምስት

## ቱሪዝም

ክፍለ ጊዜ 18

### የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ ቃላትን በምዕላድ ይከፍላሉ
- ✓ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ
- ✓ በአላፊ ጊዜ አንቀፅ ይፅፋሉ
- ✓ ራስን የመገምገሚያ ስልቶችን ተጠቅመው ሥራቸውን ይመዝናሉ
- ✓ ቅድመ ግንድ ቅጥያን ይጠቀማሉ

### የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች

- ➢ አዳምጦ ምዕላዶችን መከፋፈል
- ➢ አንብቦ የፅሁፉን መልዕክት ማብራት
- ➢ ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ
- ➢ አንቀፅ መፃፍ
- ➢ ድህረ ግንድ ቅጥያ

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### አባያና ጫሞ ሀይቆች

#### ቅድመ ማዳመጥ

### የትምህርቱ አቀራረብ

- መምህር በመጀመሪያ ደረጃ በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የምዕራፉ አላማዎች እንዲረዱ ያድርጉ፡፡
- ከዚያም በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ በጥንድ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩና ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በማበረታታት ለማዳመጥ ተግባሩ ዝግጁ እንዲሆኑ ያድርጓቸው፡፡ተማሪዎች የሚሰጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ምላሽ ተመልክተው ትክክለኛውን መልስ ከመናገርዎ በፊት የተማሪዎችን ምላሽ ያረጋግጡ፡፡
- ተማሪዎች በሰጡት ምላሽ መነሻነት የሚቀርብላቸው ምንባብ ‹‹አባያና ጫሞ ሀይቆች›› እንደሆነ በማስተዋወቅ በጥሞና እንዲያዳምጡ ያሳስቧቸው፡፡ ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላትን በደብተራቸው እንዲጽፉ ይግለጹላቸውና ምንባቡን በትክክል ያንብቡላቸው፡፡ ምንባቡን ሲያነቡ ትክክለኛውን የአነባበብ ስርዓት ተከትለው ያንብቡላቸው፡፡

በኢትዮጲያ ዉስጥ ብዙ ሀይቆች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል አባያና ጫሞ ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ በሁለቱም ሀይቆች መካከል ተመሳሳይነትና ልዩነት አሉ፡፡ ለዚህም የተፈጥሮና የሰዉ ሰራ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡

አባያና ጫሞ ሀይቆች የሚመሳሰሉበት ባህሪያት አላቸዉ፡፡ ሁለቱም ሀይቆች በደቡብ ክልል ጋሞጎፋ ዞን ዉስጥ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም አባያና ጫሞ በጣም ተቀራርበዉ በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሀይቆች ናቸዉ፡፡

ሁለቱን ሀይቆች የሚለይ በመካከላቸዉ የሚገኝ ዳገታማ ቦታ አለ፡፡ ይህ ቦታ በአካባቢዉ ነዋሪዎች ዘንድ የሚለይ በመሆኑ የእግዜር ድልድይ በመባል ይጠራል፡፡

በሁለቱ ሀይቆች ዉስጥ የተለያዩ የባህር እንስሳትና አእዋፍ ይገኛሉ፡፡በሀይቆቹ ዉስጥ ከሚገኙት የባህር እንስሳት መካከል አዞን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሁለቱ ሀይቆች ዉስጥ አዞ በብዛት ይገኛል፡፡ በተለይ በጫሞ ሀይቅ ዳርቻ የአዞ ገበያ የሚባል ቦታ አለ፡፡ ይህ ቦት አሸዋማ ስለሆነ አዞዎች እየወጡ እንቁላል ጥለዉ ተመልሰዉ ይገባሉ፡፡ ከዚህ ቦታ ሰዎች የአዞ እንቁላል እየወሰዱ ለአዞ እርባታ ይጠቀማሉ፡

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ ቀሪዉ የጽሁፍ ክፍል ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኃል

ሀይቆቹን ለቱርስት የተሻለ መስህብ ለማድረግ የተለያዩ ሰዉ ሰራሽ ነገሮች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በተለይ በአባያ ሀይቅ ዙሪያ ለቱሪስቶች ማረፊያ የሚሆኑ ሎጆች እየተሰሩ ነዉ፡፡

በተጨማሪም ሁለቱ ሀይቆች በታላቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ ዉስጥ የሚገኙ በመሆናቸዉ ይመሳሰላሉ፡፡ ሀይቆቹ በአንድ አካባቢ የሚገኙ በመሆናቸዉ በዙሪያቸዉ ያለዉ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ በአብዛኛዉ ተመሳሳይ ነዉ፡፡ በሁለቱ ሀይቆች ዙሪያ ደንና ሜዳማ የሆኑ ቦታዎች ይታያሉ፡፡

በአንጻሩ ሀይቆቹ በአንድ አካባቢ የሚገኙ ቢሆኑም የተወሰኑ ልዩነቶች አላቸዉ፡፡ ሁለቱም ሀይቆች በርዝመታቸዉና በስፋታቸዉ መጠን የለያያሉ፡፡ አባያ ሀይቅ ስድሳ ኪሎ ሜትር ርዝመትና ሀያ ኪሎ ሜትር ስፋት ሲኖረዉ ጫሞ ሀይቅ ደግሞ ሀያ ስድስት ኪሎ ሜትር ርዝመትና ሀያ ሁለት ኪሎ ሜትር ስፋት አለዉ፡፡ ሌላዉ ሁለቱ ሀይቆች ባላቸዉ

የዉሀ ገጽታም ይለያያሉ፡፡ በዚህም የአባያ ሀይቅ ደለል ያለበት ወይም ጎርፍ የሚመስል ገጽታ ሲኖረዉ ጫሞ ሀይቅ ደግሞ የንጹህ ዉሀ ገጽታ አለዉ፡፡ በመሆኑም በርቀት ሲታዩ የሁለቱ ሀይቆች ገጽታ የተለያየ ነዉ

- የቀረበላቸውን ምንባብ ሲያዳምጡ የጻፏቸው አዳዲስ ቃላት ካሉ ይጠይቋቸው፡፡ በራሳቸው ፍቺ ለመስጠት ሙከራ እንዲያደርጉ እድል ይስጧቸውና በትክክል መልስ መስጠት መቻላውን ያረጋግጡና የመለሱትንና የተሳሳቱትን እንዲያነጻጽሩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም እርስዎ ትክክለኛውን መልስ በመግለፅ እርማት ያድርጉ፡፡
- ካዳመጡት ምንባብ ውስጥ የወጡትን የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች በቃላቸው ያሰሯቸው፡፡ የሚሰጡትን ምላሽ በምክንያት እያስደገፉ እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ከምንባቡ የወጡ ቃላትን በምዕላድ ነጣጥለው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡
- በትክክል መልስ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ የቃል ጥያቄ በመጠየቅ መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በዚህም ያዳመጡትን ምንባብ መልእክት በትክክል መረዳት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- አዳምጠው ለቃላት አውዳዊ ፍች እንዲሰጡ የቀረበላቸውን ጥያቄ በትኩረት በቡድን እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ የሰጡትን ምላሽ ከትክክለኛው ምላሽ ጋር በማስተያየት ጥሩ የመለሱትን በማበረታታት የተሳሳቱትን ደግሞ በቀጣይ የተሻለ ስራ መስራት እንደሚችሉ ያበረታቷቸው፡፡
- በመጨረሻም ለተጨማሪ ተግባር በቴሌቪዥንና ሬዲዮ ስለቱሪዝም የሚቀርብ መርሀ ግብር አዳምጠው መረጃ ሰብስበው በመምጣት በክፍል ውስጥ በቃል እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡ ያቀረቡትም ንግግር ከንግግር መመሪያ አንፃር በመገምገም በቀጣይ የተሻለ ንግግር እንዲያደርጉ መንገዶችን ይጠቁሟቸው፡፡

ለናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት በምዕላድ ነጣጥላችሁ ፃፉ።

ሀ. ሎጅ--ኦች--ም

ለ . ተመሳስሎ--ዎች

ሐ. የሚመሳሰሉ-- ባቸዉ

መ. መልክአ-ምድር-- ኣዊ

ሠ. መዳረሻ--ነት--ኣቸው--ን

ረ. መስህብ--ኦች--ኣቸው

ክፍል ሁለት ንባብ

- መምህር በቅድመ ንባብ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲገልጹና በውይይቱ ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያሳስቧቸው። የገለፁትን ሀሳብ ምርምረው ትክክለኛ ምላሽ የሰጡትን በማበረታታት ለተሳሳቱት እርምት በስጠት ያስተካክሉ።
- ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው፣የአካል ጉዳተኞች፣ አይነ ስውራንና መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ካሉ ሳይዘነጉ ተማሪዎች እርስ በእርስ እንዲተጋገዙ ያድርጉ።
- ከቅድመ ንባብ ተግባር በኂላ ተማሪዎቹ በአንቀፅ በአንቀፅ ተከፋፍለው ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዲያነቡ እና ንባቡን በክንያትና ውጤት እያስተሳሰሩ እንዲያነቡ ያስረዷቸው። የንባብ ሂደታቸው የተሳካ እንዲሆን የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን በትክክል ዕንዲያጤኑ ያድርጉ። ይህ ስልት ሁሉም ተማሪ በንባቡ እንዲሳተፍ ያግዛል።

- ንባባቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በምንባቡ ውስጥ ያጋጠማቸው አዳዲስ ቃል ካለ መምህራቸውን እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፡፡
- የጠየቁት አዳዲስ ቃል ካለ እራሳቸው ተማሪዎቹ እርስ በእርስ እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ በትክክል ካልተመለሰ ግን እርስዎ ተገቢውን ፍቺው ይግለፁላቸው፡፡
- ያነበቡትን ምንባብ ዋና ሀሳብ በቃል እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡ በአንብቦ መረዳት ስር የቀረቡትን የምርጫ ጥያቄዎች በደብተራቸው ያሰሯቸው፡፡
- በምንባቡ መሰረት የቀረቡትን የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች ደግሞ በቃል እንዲመልሱ ይግለፁላቸው፡፡
- የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በደብተራችሁ ፃፉ**

| | |
|---|---|
| 1. መነ | 5. መ |
| 2. ለ | 6. ለ |
| 3. ሐ | 7. ሐ |
| 4. መ | |

## ክፍል ሶስት ቃላት

## እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

- በቃላት ትምህርት የቀረበውን የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ማስታወሻ በደብተራቸው እንዲጽፉና እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡
- የቃል እማሬያዊ ፍቺ የቀጥታ ወይም የመዝገበ ቃላዊ ፍቺ እንደሆነና ፍካሬያዊ ፍቺ ደግሞ ከእማሬያዊ ፍቺ ባሻገር ቃላት የሚኖራቸውን ሚስጥራዊ ወይም ስውር ፍቺ መሆኑን በጥያቄና መልስ በምሳሌ አስደግፈው ያስረዷቸው፡፡ በተለይም የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በዓረፍተ ነገር እያስገቡ እንዲሰሩ ያግዟቸው፡፡
- ቀጥሎ በመልመጃ አንድና ሁለት ስር ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በትክክል መለየት መቻላቸውን ይመዝኑ፡፡
- በመጨረሻም በራሳቸው አምስት ቃላትን ፈልገው እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች ሰርተው እንዲያሳዩ ይግለፁላቸው፡፡ ከመጀመሪያው ሙከራ ያሳዩትን መሻሻል ተመልክተው እርስዎ አስፈላጊውን እገዛ ያድርጉ፡፡

ለናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት እማሬያዊ ፍቻቸውን በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራቸውሁ አሳዩ፡፡**

ሀ. የአዕዋፍ ዝርያ

ለ. የሚያጣብቅ ፈሳሽ

ሐ. የበርበሬ ዝርያ

መ. በመሬት ውስጥ የሚኖሩ ነፍሳት

ሠ. ማር የምትሰራ ነፍሳት

ረ. የፍራፍሬ አይነት

ሰ. ተንቀሳቃሽ አየር

ሸ. የረጋ ወተት

**መልመጃ ሁለት**

**የሚከተሉትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ፍካሬያዊ ፍቺ በመስጠት በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ. ፈጣን

ለ. ቀልጣፋ

ሐ. ወሬ የማይቋጥር

መ. ውብ ፣ ሸጋ

ሠ. በጭፍን የሚሄድ

ረ. የማይንቀሳቀስ

## ክፍል አራት ጽሕፈት

## በሃላፊ ጊዜ አንቀፅ መፃፍ

- መምህር በተማሪው መፅሀፍ በሃላፊ ጊዜ የቀረበውን አንቀፅ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ ካነበቡ በኋላ የሃላፊ ጊዜ ጽሁፍ ምን እንደሆነ ያነበቡትን ጽሁፍ በምሳሌነት በመጥቀስ የአንድ ድርጊት በጊዜ ቅደም ተከተል ትረካ መሆኑን ያስረዷቸው፡፡
- ከዚያም በዚሁ መሰረት ባለፈው ሳምንት ያከናወኑትን ተግባር በሀላፊ ጊዜ ጽሁፍ እንዲያመጡ ይግለፁላቸው፡፡
- ጽፈው ያመጡትን በየተራ እያቀርቡ እራሳቸውን እንዲገመግሙ ያድረጉ፡፡
- በዚህም ጥንካሬና ድክመታቸውን እንዲለዩ ያሳስቧቸው፡፡ በመጨረሻም ያጋጠማቸውን ችግር፣የታየባቸውን ድክመት የሚያሻሽሉበትን ስልት ይጠቁሟቸው፡፡
- በመጨረሻም በተሰጣቸው ኃይለ ቃል መነሻነት አንቀጽ ጽፈው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡ ጽፈው የመጡትን ከጓደኞቻቸው ጋር በመቀያየር እንዲያነቡና ያገኙትን ጠንካራና ድክመት እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም የመጨረሻውን ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

## ክፍል አምስት ሰዋስው

## ቅድመ ግንድ ቅጥያ

- ❖ በዚህ ክፍል የቀረቡትን ተግባራት ለማከናወን በምዕራፍ አንድና ሁለት ላይ ስለምዕላድ የተማሩትን ያስታውሷቸው፡፡ ከዚያም በቀረበላቸው ምሳሌ መሰረት የቀረቡትን ቃላት ዋና ቃሉን ከድህረ ምዕላድ ጋር እንዲያጣምሩና ከዋና ቃሉ ቅድመ አምድ ቅጥያውን ለይተው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡
- ❖ የሰጡት ምላሽ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድርግ ይገምግሙ፡፡
- ❖ በዚያም ትክክለኛ መልስ ላልሰጡት ትክከለኛውን መልስ በመግለፅ እንዲያስተካክሉ ያግዟቸው፡፡
- ❖ ከዚህ በታች የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን የቅጥያ ተግባራት ለተማሪዎቹ ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡ ለተማሪዎቹ ማስታወሻ በሚሰጡበት ወቅት ሁሉም ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ ማስታወሻውን እየፃፉ መሆናቸውን ይከታተሏቸው፡፡
- ❖ ማስታወሻውን አፅፈው እንደጨረሱ የተወሰነ ደቂቃ ተማሪዎቹ በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ በጥንድ በጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ እርስዎም ተማሪዎች በሚወያዩበት ወቅት በትክክል እየተወያዩ ስለመሆናቸው እያንዳንዱን ተማሪ እየተዟዟሩ በማየት ያረጋግጡ፡፡
- ❖ በመቀጠልም ተማሪዎቹ የተወያዩበትን ሀሳብ በየተራ እየወጡ ፅብረቃ እንዲያደርጉ ያድርጓቸው፡፡ ከዚያም ሁሉም ተማሪዎች ፅብረቃ ማድረጋቸውን ካረጋገጡ በኋላ እርስዎ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡
- ❖ ከላይ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ተማሪዎቹ ርእሰ ጉዳዩን በትክክል መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሁለት መልመጃዎች የክፍል ስራ ይስጧቸውና እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎቹ ሰርተው እንደጨረሱ

በትክክል መስራት አለመስራታቸውን በእርግጥ ያረጋግጡ፡፡ በትክክል የሰሩትን ተማሪዎች በማበረታታት በትክክል ያልሰሩ ተማሪዎች ካሉ ትክክለኛውነ መልስ እርስዎ ይንገሯቸው፡፡

ሀ.በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚታዩትን መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች ለይተው ያመልክቱ፡፡

1. በቤታቸው
2. ለልጆቻቸው
3. እንደመጣች
4. ስለጠራኝ
5. ከየስራቸው

ለ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የገቡትን ቅጥያዎች የእርባታ ወይም የምስረታ በማላት ለይተው ያመልክቱ፡፡

1. በሰውነቴ
2. መንገደኛ
3. ወላጆቹ
4. ኮረብታማ
5. ቀልደኛ

የመልመጃዎቹ መልሶች

| ሀ. | ለ. |
| --- | --- |
| 1. በ-ቤት -ኣቸው | 1. የእርባታ |
| 2. ለ-ልጅ-ኦች-ኣቸው | 2. መስራች |
| 3. እንደ-መጣ-ች | 3. የእርባታ |
| 4. ስለ-ጠራ-ኝ | 4. መስራች |
| 5. ከ-የ-ስራ-ኣቸው | 5. መስራች |

የእርባታና የምስረታ ቅጥያዎች

ቅጥያዎች በቃል ላይ ሲታከሉ የተለያየ ሙያ ይኖራቸዋል፡፡ ይህንን ሙያቸውን መሰረት በማድረግ የእርባታ ቅጥያ እና መስራች ቅጥያ በሚል ተለይተው ይታወቃሉ፡፡

ሀ. የእርባታ ቅጥያዎች፡-

የእርባታ ቅጥያዎች በአንድ ቃል ተደርበው የሚገቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ቅጥያዎች በቃሉ ላይ ሲታከሉ የቃሉን ሰዋስዋዊ ክፍል አይለዉጡም ወይም ቃሉን ወደ ሌላ የቃል ክፍልነት አይቀይሩትም፡፡

ምሳሌ፡- በር- ኦች- በሮች ልብስ-ኦች-ልብሶች

በር-ኤ- በሬ ልብስ-ኤ--ልብሴ

በር-ኣችሁ- በራችሁ ልብስ-ኣችሁ-ልብሳችሁ

ከፍ ሲል በቀረበው ምሳሌ ላይ ታክለው የሚታዩት ቅጥያዎች የእርባታ ቅጥያዎች ናቸው፡፡ የእርባታ ቅጥያዎች ናቸው የሚባለውም በር ወይም ልብስ የሚሉትን ቃላት ሰዋስዋዊ ክፍል ባለመለወጣቸው ነው፡፡ ቅጥያዎቹ በመታከላቸው ምክንያት ስም የነበሩት በር እና ልብስ የሚሉት ቃላት ወደ ሌላ ሰዋስዋዊ ክፍል አልተቀየሩም፡፡

ለ. የምስረታ ቅጥያዎች፡-

መስራች ቅጥያዎች እንደ የእርባታ ቅጥያ ሁሉ በአንድ ቃል ላይ ተጠግተው የሚገቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ቅጥያዎች ግን በቃሉ ላይ ሲታከሉ የቃሉን ሰዋስዋዊ ክፍል ይለውጣሉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀይል- ኧኛ- ሀይለኛ

ሀብት- ኣም -ሃብታም

ተራራ-አማ- ተራራማ

ጉልበት-ኧኛ- ጉልበተኛ

ከፍ ሲል በቀረበው ምሳሌ ላይ ታክለው የሚታዩት ቅጥያዎች የምስረታ ቅጥያዎች ናቸው፡፡ መስራች ቅጥያዎች ናቸው የሚባለውም የቀላቱን ሰዋስዋዊ ክፍል ከስምነት ወደ ቅፅልነት በመለወጣቸው ነው፡፡ ከምሳሌው መረዳት እንደሚቻላው ቅጥያዎቹ በመታከላቸው ምክንያት ስም ነበሩት ጉልበት፣ሀይል፣ሀብትና ተራራ የሚሉት ቃላት ወደ ሌላ ሰዋስዋዊ ክፍል ማላትም ከስምነት ወደ ቅፅልነት ተቀይረዋል፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ላይ ምሳሌውን መሰት በማድረግ በዋና ቃሉ ላይ ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን አጣምራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ደብተራችሁ

ለ. ገበሬዎች

ሐ. መከራት

መ. ተከሰተች

ሠ. መምህሮች

ረ. ትምህርታችሁ

ሰ. መጽሐፉን

ሸ. ንብረታቸውን

**መልመጃ ሁለት**

**ከሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን በመነጠል በደብተራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ሀ. እንደ - ወረደ

ለ. ስለ - ፍቅር

ሐ. የ - መቅደስ

መ. የነ - ጀማል

ሠ. ወደ - መስኮት

ረ. በ - ህብረተሰብ

ሰ. ከ - አዲስ አበባ

**መርጃ መሳሪያ**

የቅድመ አምድና ድህረ አምድ ቅጥያዎችን የሚያሳይ የተዘጋጀ ቻርት

# ምዕራፍ ስድስት

## አደንዛዥእጾች

ክፍለ ጊዜ 18

### ❖ የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትለው ያነባሉ፡፡
- ✓ አዳምጠዉ በመረዳት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ
- ✓ መረጃ ሰጪ ፅሁፎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ አአዳዲስ ቃላትን ከአገባቡ በመነሳት ይገምታሉ፡፡
- ✓ አንድን ሀሳብ ለመግለጽ መሸጋገሪያ ቃላትን ይጠቀማሉ፡፡

የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች

- ➢ ምንባቡን መሰረት ያደረገ ውይይት
- ➢ የፅሁፍና የግል ህይወት ተዛምዶ
- ➢ የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ
- ➢ አንቀፆችን ማጠናቀቅ
- ➢ ስም፣ተውላጠ ስምና ግስን በዓረፍ ተነገር ውስጥ መተቀም

ክፍል አንድ ማዳመጥ

‹‹ሰካራሙ ተበጂ››

የትምህርቱ አቀራረብ

- ❖ መምህር ተማሪዎቹ የምዕራፉን ዓላማዎች አንብበው እንዲረዱ ያድርጉ፡፡
- ❖ በዚህ ምዕራፍ ለማዳመጥ የቀረበውን ‹‹ሰካራሙ ተበጂ›› የሚለውን ታሪክ ከማንበብዎ በፊት ከምንባቡ ለወጡ ቁልፍ ቃላት በቃላቸው

ፍቺ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የሚያነቡላቸውን ምንባብ ርዕስ አስተዋውቀው በጥሞና በማዳመጥ ጥያቄዎችን ለመስራት እንዲዘጋጁ ያሳስቧቸው፡፡

- ተማሪዎቹ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ምንባቡን ስልቱን ጠብቀው ያንብቡላቸው፡፡

በጉለሌ የነበረው የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነው ብለው ከጉለለ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቀ ‹‹ሰካራሙ ተበጀ! ዶሮ ነጋዴው ተበጀ ነው!›› ብለው ይነግሯችዋል፡፡ የህይወት ታሪኩ ፍፁም ገድል ነው፡፡ የራሱን ፀጉር ውሃና መቀስ ነክቶት አያውቅም፡፡ ከጠርሙስ ጋር ካልተገናኘ አይኑ አይገለጥም፤ሰውንም አያናግርም፡፡ በጠርሙስ የሞላውን ከጠጣ በኋላ ሲራገም ወይም ሲሳደብ ሲፎክርና ሲያቅራራ ድምፁ ከፈረንጅ ውሻ ድምጽ ይወፍራል፡፡ቢያውቅም ባያውቅም ካገኘው ጋር ሁሉ ይስቃል፣ይንከተከታል፣ መልሶ ይተክዛል፣ መልሶ ይስቃል፡፡

ቡና በተፈላ ጊዜ ጉለሌ በየምድጃው ስር የሰካራም ተረት የተጫወተው ሰው ሁሉ የተናገረው በሰካራሙ ተበጀ ላይ ነው፡፡ መልኩን አይተው የማያውቁት ባልቴቶች እንኳን ቡናውን ፉት እያሉ የሌሎቹን ስካር ፌዝና ተረት በተበጀ ላይ ነው የሚያላክኩበት፡፡ ከሚያሰክር ሁሉ ለመራቅ ብዙ ጊዜ ሞክሮ ነበር፡፡አድሮ ቃሪያ እንዳሉት አበው ከድጡ ወደ ማጡ ሆነበትና ሰክሮ ያላደረበት ሌሊት አልፎ ብርሃን በሆነ ጊዜ‹‹ከእንግዲህ መጠጥ በዞረበት አልሄድም››እያለ በየቀኑ ምሏል፡፡ የመጠጥ ጠርሙችን ከቤት አውጥቶ የማንም መሳለቂያ አልሆንም ብሎ ጥሏቸዋል፤ መልሶ ሰብስቧቸዋል፡፡ እሱ አጠገብ የተኛ እንቅልፍ አያይም፡፡ ጠርሙሱን ከከፈተ በኋላ ብርጭቆ ያስፈልገው እንደነበር

ትዝ አለው። ሶስት የሚሆን ደህና ጉንጭ ጠርሙሱን ከአፉ አስጠግቶ ጨለጠው። ብርጭቆ ሊያመጣ ሲያስበው ግማሹን ያክለ ስርጉጀዋለሁ አለና ከት ብሎ ሳቀ። የጠርሙሱ መጠጥ እስኪያልቅ ከዛፉ ስር ተቀምጦ ትንባሆውን በላዩ በላዩ ላይ ይለዋል።

ይህን መጠጥና ትንባሆህን ካልተውህ ላንተ ንስሃ አባት አልሆንህም›› ብለው የመጀመሪያ የንስሃ አባቱ ብዙ ከመከሩት በኋላ መንፈሳዊ ልጅነቱን ከርግማት ጋር አስወግደውታል። ስራተኞቹ ለእርሱ ተቀጥሮ መስራትን ከውርደት ቆጥረውት እያዋረዱት ሄደዋል።‹‹መጠጥ ካልተውክ አናገባህም›› ብለው በየጊዜው ጋብቻ ጠይቋቸው የነበሩ ሴቶች ሁሉ በቁመናው አሰናብተውታል። በሰንበቴም፣ በማህበርም፣ ማህበርተኛ ለመሆን የጠየቃቸው ነፍሱን ሳይቀር ንቀዋታል። በቡሌ መንደር ብዙ ጊዜ ሰክሮ ፈረስ ሂዶበታል። ሰክሮ ሲነጋ እራሱን እስር ቤት ውስጥ አግኝቶታል። መንገድ ዳር ባሉት በብዙ የውሃ ጉድጓዶች ሰክሮ ገብቶ የቡሌ ህዝብ አውጥቶታል። ሰክሮ ከቤት መድረስ እያቃተው ከወደቀበት መንገድ ሳይነሳ ብዙ ጊዜ በላዩ ላይ ጎርፍ ሄድበት አድሯል።

ሰዎች መልካም የሰማዕትነት ስራውን ሁሉ ርካሽ አድርገው ይቆጥሩበታል። በግብረገብ መሰረት አደረኩት ያለውን ሁሉ በስካር እንዳደረገው ያናንቁበታል።‹‹በጎ ስራውን ሁሉ በትኩስ መቃብር ውስጥ አፈር አለበሰው፤አንተ ሰው ሰውሁን፣ ሚስት አግባ፣ ልጆች ይኑርህ›› ይሉና ይዘልፉት ነበር። ይህ ሁሉ ውርደትና ርኩሰት ነው እንጅ ክብር አይደለም። በአደንዛዥ እፅ የደነዘዘ ሰው ለምንም አይሆንም። ሁሌም መጥፎ ሱስ ያለበት ሰው ከሰው በታች ነው። ሰዎች ይሸሹታል፤ ፍጹም ወዳጅነትና ዝምድናውን አይሹም።ቁም ነገር ቢኖረውም ከሰው

አይቆጠርም፡፡ እናም ኑሮው በጨለማ እንደተከበበ፣ ህይወቱ የተመሰቃቀለ፣ ኑሮው የደበዘዘ ይሆናል፡፡

ምንጭ ዘሪሁን አስፋው፣1995፣ከገፅ115-121 ተሸሎ የተወሰደ)፡፡

- ታሪኩ ተደግሞ እንዲነበብላቸው ፍላጎት እንዳላቸው ይጠይቁና ደግመው ያንብቡላቸው፡፡
- በመቀጠልም በአዳምጦ መረዳት ስር ያሉትን ጥያቄዎች በወንበር እንዲወያዩ ይግለፁላቸው፡፡ በውይይቱም ያገኙትን ሀሳብ ተማሪዎቹን በስም እየጠሩ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም የምንባቡን መልዕክት ከራሳቸው ህይዎት ጋር እያገኛኙ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- የለቱን ትምህርት ለማጠቃለል ያህል ተማሪዎቹ በሰጡት መልስ ላይ ተመርኩዘው የጥያቄዎቹን የማጠቃለያ መልስ ይግለፁላቸው፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. የማይለወጥ፣የማይሻሻል፣ከስህተቱ የማይመለስ

ለ. ከችግር ወደ ባሰ ችግር

ሐ. አጋምሸዋለሁ፣ ብዙውን ጠጥቸዋለሁ

መ. አንድ አቋምና ተመሳሳይ አላማ ያላቸው ሰዎች የሚመሰርቱት ድርጅት

ሠ. ምግባረ መልካም፣ ምግባሩ የቀና፣ እውነተኛ

ረ. በግልፅ የማይታይ፣የፈዘዘ

ሰ. ያልተስተካከለ፣የተዘበራረቀ፣ በስርዓቱ ያልተቀመጠ

ሸ. ማሾፊያ፣መቀለጃ

## ክፍል ሁለት ንባብ

- በቅድሚያ የንባቡን ርዕስ በሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፡፡ በማዳመጥ ክፍለ ጊዜ አዳምጠውት የነበረውን ታሪክ እንዲያስታውሱ በጥያቄ ያነቃቋቸው፡፡ የእለቱን ርዕስ ካዳመጡት ምንባብ ርዕስ ጋር እያዛመዱ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ያበረታቷቸው፡፡ ይህ ተግባር የተማሪዎችን ህሌና ለመሰብሰብ ይረዳል፡፡
- በማስከተል የቅድመ ንባብ ጥያቄን በቃላቸው ያሰሯቸው፡፡ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹን ከሰሩ በኋላ ተገቢውን የንበት ስልት ተጠቅመው ምንባቡን እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡ ንባባቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የሚጠይቁት አዳዲስ ቃል ካለ ይጠይቋቸው፡፡ ለጠየቁት አዲስ ቃል በራሳቸው መልሱን እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው፡፡ መመለስ ካልቻሉ ግን እርስዎ ያስረዷቸው፡፡
- ከዚም የቀረበውን የእውነት ሐሰት ጥያቄ በቃል ያሰሯቸው፡፡ በመልመጃ ሁለት ስር በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍቺ በደብተራቸው እንዲሰሩ ይግለጹላቸው፡፡ በአዛምድ መልክ የቀረቡትን ቃላት በፍቺ የሚመሳሰሉትን እንዲያዛምዱ ያድርጓቸው፡፡

ለናሙና ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### መልመጃ ሁለት

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ጉዳት
2. ያልጠነከረ ግንኙነት
3. ጥሩ ያልሆነ
4. ጦስ፣ችግር
5. መቅጠን፣መኮስመን፣ማነስ
6. ውስብስብ

## ክፍል ሶስት ቃላት

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

- በምዕራፍ አምስት ውስጥ የተማሩትን የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ በጥያቄና መልስ ይከልሱላቸው፡፡ ከዚያም በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነበር እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡
- የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ ትክክለኛ መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡ የተሳሳቱት ጥያቄ ካለ ትክክለኛ መልስ በመንገር አስተካክለው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠልም ለቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ፣ ፍቺ በትክክል መስጠት መቻላቸውን ይመዝኑ፡፡ ከዚያም በዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ጽፈው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡

## ክፍል አራት ጽሕፈት

### ማስታወሻ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

ከዚህ ስር ያለውን ማስታወሻ በደብተራቸው በማጻፍ ያስረዷቸው፡፡

አያያዥ ወይም የመሸጋገሪያ ቃላት ዓረፍተ ነገሮች እርስ በእርስ ተቀናጅተውና ተዋህደው እንዲቀርቡ የሚያግዙ ቃላትና ሀረጋት ናቸው፡፡ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር፣ አንቀፅን ከአንቀፅ በማያያዝ የምናነሳው ሀሳብ ፍሰቱን በጠበቀ መልኩ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፡፡ እያንዳንዳቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት የራሳቸው ቦታና አገልግሎት አላቸው፡፡ በመሆኑም አንዱ በገባበት ቦታ ሌላው ቢገባ አረፍተ ነገሩ ሊዛባና ሀሳቡ ሊፋለስ ይችላል፡፡

ምሳሌ፡-ስለዚህ

ነገር ግን

ሀ. በደንብ አጥንቻለሁ፤---------------ጥሩ ውጤት አመጣለሁ፡፡

ለ. ቡና ሲፈላ ደስ ይለኛል፤------------ስጠጣ አይስማማኝም፡፡

በምሳሌ ሀ ስር በቀረበው ዓረፍተ ነገር ውስጥ መግባት ያለበት አያያዥ ቃል ‹‹ስለዚህ›› ነው፡፡ በሱ ቦታ ላይ ነገር ግን የሚለውን ብናስገባ ሀሳቡ የተዛባ ይሆናል፡፡ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም አገልግሎታቸው በርካታ ነው፡፡ አያያዥ ቃላት ከሚባሉት ውስጥ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እንመልከት፡፡

| | |
|---|---|
| ምክንያቱም | በእዲህ እንዳለ |
| አለበለዚያ | በተመሳሳይ |
| በአንፃሩ | እንጂ |
| ቀጥሎም | በዚህ ሳቢያ |
| እንደገና | ያም ሆነ ይህ |
| ነገር ግንይልቅ | ስለዚህ |
| ዳሩ ግን | ምንም እንኳ |

በመጨረሻም

❖ መምህር ከቀረበው ፅሁፍ ውስጥ አያያዥ ቃላትን ለይተው በደብተራቸው እንዲጽፉ ያደርጉ፡፡ ከዚያም በቀረበው ያልተሟላ አንቀጽ ውስጥ በክፍት ቦታው ተገቢውን አያያዥ ቃል በመጠቀም እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡ እያንዳንዱን ተማሪ በስም እየጠሩ የሰሩትን እንዲያነቡ ያድርጉና በትክክል መልስ መስጠታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ በሰጡት ምላሽ ላይ ስህተት ካለ ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

❖ በዚህ ክፍል ተማሪዎቹ ያልተጠናቀቁ እንቀፆች አሟልተው እንዲጽፉ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ የቀረበውን አንቀጽ ሀሳቡን እስኪረዱት ደጋግመው እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡ ካነበቡ በኋላ አንቀጹን ሊያሟላ የሚች ሀሳብ በማስገባት አሟልተው እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ አሟልተው የጻፉትን አንቀጽ አንብበው የትኛው መረጃ ሰጪ ጽሁፍ እንደሆነ እንዲለዩ ያድርጓቸው፡፡

ለናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ተጀምረው ያልተጠናቀቁ አንቀጾች አሟልታችሁ በደብተራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ልጅቱ ልቅም ያች ቆንጆ ናት፡፡ ጫማ የላትም ነገር ግን እግሯ እንሶስላ የሞቀች ይመስላል፡፡ ፀጉሯ ሽቶና ዘይት ነክቶት አያውቅም፤ በሳሙና ለመታጠብ እንኳን እድል አላገኘም፤ሆኖም እየተዘናፈለ ወርዶ የተከበረውን ትከሻዋን አጥለቅልቆታል፡፡ መዘናፈሉም መልሰው መላልሰው ያጠፉት ይመስላል፡፡ አይኖቿ ኩል አያውቁም ነገር ግን እንደንጋት ኮከብ ያበራሉ፡፡ ጥርሶቿም ብርሃን ያስተጋባሉ፤የሚፋቁትም አልፎ አልፎ ነው፡፡ ጠፍሮቿ ቀለም አላዩም፤ሆኖም ውበታቸው እፁብ ድንቅ ነው፡፡ድህነትና ውበት በአንድ አካል ላይ እንደዚህ ያለ ፍፁም ህብረት ሲኖራቸው በፀዳል ላይ ብቻ ማየቴ ነው፡፡ *(ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፣2008 ገፅ307)*

ለ. የሾላ ወተት ፋብሪካ የሚሸጠው ወተት ህዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ብዙ ሂደቶችን ማለፍ አለበት፡፡ በመጀመሪያ ወተቱ በፋብሪካው ውስጥ ካሉ ላሞችና በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ካሉ ገበሬዎች ይገዛል፡፡ ይህ የተገዛ ወተት በትላልቅ የብረት ጋኖች ተሞልቶ በተሽከርካሪ ተጭኖ ፋብሪካው ዘንድ ይደርሳል፡፡ ፋብሪካው ተቀብሎ እየመዘነ ወደ ማፍያ ጋን ውስጥ ይገለብጣል፡፡ ጋኑ ወተቱን በ100 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ያፈላና ወደ ሁለተኛው ማሽን በትላልቅ ቱቦ ያስተላልፈዋል፡፡ ሁለተኛው ማሽን በ22 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ እንደገና ያፈላና ወተቱ ውስጥ ያለውን ክሬም ይለያል፡፡ ክሬሙም ወደ ሌላ ማሽን ሲሄድ ወተቱ ወደ መጨረሻው ማሽን ይላካል፡፡ የመጨረሻው ማሽን ወተቱን ያቀዘቅዝና በቧንቧ አማካኝነት በጠርሙስና በላስቲክ እየለካ ይሞላና ይተሸጋል፡፡ ከዚያም በጉልበት ሰራተኞች አማካኝነት በሳጥን ውስጥ እየተደረገ ተቆጥሮ መኪና ላይ ይጫናል፡፡ በመጨረሻም ለነጋዴዎች ይሰጥና ለገበያ ቀርቦ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡(ደረጀ ገብሬ፣1996 ገፅ164)

መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላት ቀጥሎ በቀረበው ባዶ ቦታ ውስጥ በማስገባት አንቀፁ የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰት እንዲኖረው አድርጉ፡፡

1. ያለምክንያት
2. እና
3. ይሆን ዘንድ
4. ነገር ግን
5. ቢሆንም
6. እርግጥ ነው
7. ስለዚህ

## ክፍል አምስት ሰዋስው

### ተውላጠ ስም

- በምዕራፍ አንድና ሁለት ስለተጸውዖ እና የወል ስም ተማሩትን እንዲያስታውሱ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠል ተውላጠ ስም ስምን ተክቶ እየገባ የሚያገለግል መሆኑን በምሳሌ በማስደገፍ ያስረዷቸው፡፡
- ግስ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊት አመልካች መሆኑን በዓረፍተ ነገር ውስጥ እያስገቡ ምሳሌ በመስጠት ይግለጹላቸው፡፡ በመቀጠል ተቀላቅለው የቀረቡትን ስምና ተውላጠ ስሞች ለይተው በሰንጠረዥ ውስጥ እንዲያሰፍሩ፣ ከዚያም በባዶ ቦታው ውስጥ ተውላጠ ስሞችን በማስገባት ዓረፍተ ነገሮችን አሟልተው እንዲጽፉ ያግዟቸው፡፡
- በመጨረሻም የቀረቡላቸውን ግሶች በዓረፍተ ነገር ውስጥ አስገብተው እንዲጠቀሙ ያድርጓቸው፡፡
- የሰጡትን መልስ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡

### በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

#### መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ስሞችንና ተውላጠ ስሞችን ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. እሱ እና እሷ

ለ. እሷ

ሐ. እሱ

መ. እነሱ

ሠ. እኔ

ረ. አንተ

ሰ. እናንተ

**መርጃ መሳሪያ**

ስምና ተውላጠ ስምን ጎን ለጎን የሚያሳይ የተዘጋጀ ቻርት

# ምዕራፍ ሰባት

## የጥላቻ ንግግር

ክፍለ ጊዜ 18

**የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች፡-**

**አዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ይመልሳሉ**

- ✓ መግባባትና አለመግባባትን የሚገልፁ ሀሳቦችን ያቀርባሉ
- ✓ ምንባቡን በማንበብ የጥላቻ ንግግር እንዴት እንደሚወገድ ይገልፃሉ
- ✓ ቅፅሎችን በመለየት ይጠቀማሉ
- ✓ የጥላቻ ንግግርን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ይገልፃሉ
- ✓ (እና)ን እና (ነገር ግን)ን ተጠቅመው ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ይመሰርታሉ፡፡

**የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች**

ማዳመጥና ማንፀባረቅ

ማንበብና ማፍለቅ

የቃላት አውዳዊ ፍች

ቀላልና ዉስብስብ አረፍተ ነገር

ቅፅሎች

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

‹‹የጥላቻ ንግግር የሚያስከትለው ጉዳት ››

የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረቡት ምንባቦች ተማሪዎቹን ከአላስፈላጊ ድርጊቶች ለመጠበቅና የሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ተረድተው ከዚህ ተግባር እንዲቆጠቡ በማሰብ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ የእርስዎ ሚና ከፍተኛ መሆኑን አይዘንጉ፡፡ ከቀረቡት ይዘቶች ባሻገር የስነ ምግባር ጉዳይ ይቃኝበታል፡፡ ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ነገር ትኩረትና ጥንቃቄ የተሞላ የህይወት ክህሎት ለራስም ሆነ ለሀገር ጠቃሚ መሆኑን ተረድተው እንዲያልፉ ጥረት ማድረግ ይጠበቃል፡፡በተጨማሪም አንዳንድ ውይይቶች ገደብ የለሽ ሆነው ያሉበትን ሰላማዊ ሁኔታ እንዳይበርዙ የውይይቱ ዳራ የተገደበ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ በተማሪውመማሪያ መጽሐፍ ላይ በቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጊዜ ይስጧቸው፡፡ የተወያዩበትን ሀሳብ ከየቡድኑ ተማሪ በመወከል እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡ በሰጡት ሀሳብ ተጨማሪ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡ ይህ ደግሞ ቀጥሎ ለሚቀርብላቸው ምንባብ ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ያነሳሳቸዋል፡፡

ተማሪዎቹ ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡና ምንባቡን በዝግታ ያንብቡላቸው፡፡ ንባቡን ገታ አድርገው በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡትን ጥያቄዎች ያንብቡላቸውና መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በዚህ እስካሁን ተማሪዎቹ ምን ያህል በትኩረት እንዳዳመጡ ይገንዘቡ፡፡ ከዚያም ንባብዎን ይቀጥሉ፡፡

ሩዋንዳ በመካከለኛው አፍሪካ እንደ ጌጥ ጣል የተደረገች ትንሽ ሀገር ነች፡፡ በጣም ማራኪ ውበት ስላላት፣ በለምለም ሸንተረሮቿ፣ ጭጋግ በሸፈናቸው

ተራሮቿ፣ በአረንጓዴ ሸለቆዎቿና በአንጸባራቂ ሐይቆቿ ተማርኮ ለምስጋና ወደ አምላክ አለማንጋጠጥ የማይታሰብ ነው፡፡ ከተራሮቿ ቁልቁል የተለያየ ዝርያ ወዳላቸው የጽድጫካዎቿ የሚወርደው ነፋሻ አየር በልዩ ልዩ አበቦች መዓዛ የተሞላ ነው፡፡

በቤታችን ዘረኝነትና ምክንያት የለሽ ጥላቻ በፍጹም አይታወቁም፡፡ እኛ እንኖር በት በነበረው የሩዋንዳ ክፍል ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ አዕምሯቸው ቅንነትና መልካምነት የሌለው ግን ደግሞ እንደበታቸው ለጥላቻ፣ ለክፋትና ለተንኮል የተፈጠሩ ሰዎችነበሩ፡፡ ሁል ጊዜ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ የጥላቻ ድምፅ እሰማለሁ፡፡ የአር.ቲ. ኤል. ኤም. ሬድዮ የጥላቻ ድምጾች በመኝታ ቤቴ መስኮት ገብተው ህልሞቼ ውስጥ እስኪደነቀሩ ሌሊቱን በሰላም ተኝቼ አሳልፋለሁ፡፡ በትምህርት ቆይታዬ አር. ቲ. ኤል. ኤም. በጽንፈኛ ሁቱዎች ዘንድ አዲሱና በጣም ታዋቂውሬድዮ ጣቢያ ለመሆን ችሏል፡፡ ጸረ- ቱትሲ መርዝን የሚረጭ የተለያየ ጥላቻ መሣሪያ ወጥቶታል፡፡ ሁሌ ‹‹ስለሁቱ የበላይነት›› የሚጮህ አካል-አልባ ክፉ ድምፅ ሆነ፡፡ የሁቱ የበላይነትም ሁቱዎችን በቱትሲ ወዳጆቻቸውና ጎረቤቶቻቸው ላይ እንዲነሱ የሚያደርግ ተናዳፊ ተርብ ለመሆን ቻለ፡፡

‹‹እነዚያ ቱትሲዎች ሊገድሉን ወጥተዋል፡፡ አትመኗቸው… እኛ ሁቱዎች ቀድመናቸው ልንነሳ ይገባናል! መንግሥታችንን ገልብጠው ሊያሳድዱን እየዶለቱብን ነው፡፡ በርዕሰ-ብሔራችን ላይ አንዳች ነገር ቢከሰት ሁሉንም ቱትሲዎች ወዲያውኑ ማውደም ግድ ይለናል! እያንዳንዱ ሁቱ ሩዋንዳን ከነዚህ ቱትሲ በረሮዎች ለማጽዳት እጅ ለእጅ መያያዝ አለበት! የሁቱ የበላይነት! የሁቱ የበላይነት!›› የሚለውን ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ዜና እንደደህና ነገር በሬዴዎ ጣቢያው ተለቆ ይደመጣል፡፡ ይህን በመሰለ አጉለኛ ሁኔታ ከእንቅልፌ እነቃለሁ፡፡ እነዚያን የልጅ ስድቦችና ልቅ ማስፈራሪያዎች ማንም ሰው ከምር ይቀበላቸዋል ብሎ ማመን አሰቸጋሪ ሲሆን መንግሥቱም የሕዝብ

ንብረት የሆነውን የአየር ሰዓት ተጠቅሞ ቱትሲዎችን ለማስፈራሪያ መፍቀዱን ማወቁ ይረብሻል፡፡ በወቅቱ ግን በሀገሪቱ በርካታ ስፍራዎች ቱትሲዎች በጽንፈኞች እየተገደሉ መሆኑን በሚገልጹ ወሬዎች ይበልጡን ተረበሽኩ፡፡ እኛም ሰማይን በድጋሚ አናይም ብለን አሰብን፡፡ የሬዲዮ ጣቢያ ስለግድያ መቀስቀሻ መሣሪያነት ለውጠዋታል፡፡ የሬድዮ ጣቢያውሰዎች በማናቸውም ስፍራ የሚገኙ ሁቱዎች ቱትሲዎችን ምንም ጥያቄ መጠየቅ ሳያስፈልጋቸው ባገኙበት አጋጣሚ መግደል ግዴታቸው እንደሆነ ያስተጋባሉ፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ታሪክ ምን ተረዳችሁ?
2. የሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ ምንጩ ምን ነበር?

አንዳንድ ገበሬዎች ሰብላቸው እየተበላሸባቸው እንደሆነ ሲያማርሩበት፤ አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን በሬድዮ አንድ ሰው ሰብሉን ለመንከባከብ ከግድያው አንድ ቀን እንኳን ቢቀር ሲሠራ ራሱን የሚከላከልበት መሣሪያ መያዝ አለበት ብሎ አሳሰበ፡፡

‹‹መዘናጋት የለባችሁም! እነዚህ እባብቱትሲዎች በየሣርና ቁጥቋጦ ውውስጥ ተደብቀዋል›› አለ፡፡

‹‹ስለሆነም እባቦቹን ከሁለት ለመቁረጥ መሳሪያችሁን ይዛችሁ መዘጋጀታችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ ከተቻ ለመሣሪያችሁን አንስታችሁ ተኩሳችሁ ግደሏቸው! ጠመንጃ ከሌላችሁ መንግሥት ይሰጣችኋል፡፡ ማሳችሁ ላይ እየሠራችሁ ሴት ቱትሲ በየጥሻው ልጇን ስታጠባ ካያችሁ ወርቃማ እድሉን እንዳታባክኑት፤ጠመንጃችሁን አንሱ ፤ ግደሏት፤ እናም ግዴታችሁን እንደተወጣችሁ አውቃችሁ ወደሥራችሁ ተመለሱ፡፡›› በማለት ምንም ሳያመንቱ በሬዲዮው መቀስቀሱን ቀጠሉበት፡፡

‹‹ ሕፃኑን መግደላችሁን ግን አትርሱ፤ የእባብ ልጅ መቼም ቢሆን እባብነው፤ ስለዚህ እርሱንም ግደሉት!››

የአካባቢው ባለስልጣናት በመንደሩ ነዳጅ ማደያ መሳሪያ ሲያድሉ ታጣቂዎቹ በበኩላቸው ከበርበር እየሄዱ ያስተባብራሉ፡፡

በሩዋንዳ ያለማናቸውም ሁቱ ጠመንጃ ያለው መስሏል፡፡ ይህ እንግዲህ በቱትሲዎች ላይ እንዲጠቀሙት ከሚያዝ መመሪያ ጋር የመጣ ነው፡፡ ማንም በዓለም ላይ ያለ ሰው ሃይአላላቸውም፡፡ ከሬድዮ ዘገባዎች በምንሰማው እርዳታ እየመጣ እንዳልሆነ አውቀነዋል፡፡ ግን ሰዎች በዘርና ጎሳ ተለይተው እንዲገደሉ በነጋ በጠባ ሳይታክቱ በጣቢያቸው ያሰራጫሉ፡፡ አንዳንዴ ቄሱ በሬድዮ ዘገባዎች ያልተካተቱትን የመንግሥትን የዘር ፍጅት እቅዶች ይነግሩናል፡፡ ‹‹ሁሉም ቱትሲዎች ሲሞቱ ጭራሽ ያልነበሩ ለማስመሰል ታቅዷል፡፡ ማንኛውንም አሻራቸውን ያጠፋሉ›› ሲሉ ምንም ሳይመስላቸው ነገሩን፡፡ ‹‹በከተማው የማውቃቸው የመንግሥት ባለስልጣናት ሁሉንም ቱትሲ ነክ መዛግብት እንዲያጠፉ ታዘዋል፡፡ አብዛኞቹን የትምህርት ቤትና የሥራ መዛግብት አቃጥለው ወደ ልደት፣ጋብቻናሞት ምስክር ወረቀቶች ተሸጋግረዋል፡፡ ያው በማንኛውም ከተማና መንደር ተመሳሳይ ነው፡፡ ትዕዛዙ አንድም የቱትሲ አሻራ በሩዋንዳ አፈር ላይ እንዳይቀር የሚልነው››፡፡

በመካለኛው አፍሪካ በምትገኘው በሩዋንዳ የተካሄደውና አንድ ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈው የዘር ማጥፋት ክስተት በንጹሐን ዜጎች ላይ ከተፈጸሙ የተደራጁና መጠነ ሰፊ ዘግናኝ ድርጊቶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ሁሉ እልቂትና ፍጅት የተከሰተው ደግሞ በአንድ የሬዲዮ ጣቢያ የጥላቻ ንግግር ወይም ቅስቀሳ ምክንያት ነው፡፡ ይህም ጸረ-ቱትሲ የጥላቻው ትወታ ሁቱዎች ቱትሲዎችን በየወቅቱ የጥቃቶቻቸው ሰለባ እንዲያደርጉ ገፋፍቷቸዋል፡ ፡የሩዋንዳው ጭፍጨፋ ተራው ሕዝብ በሰፊው የተሳተፈበትና

‹‹ቱትሲዎች መጤዎች ናቸው ›› በሚለው የቆየ የጥላቻ ቅስቀሳ ምክንያትነት በጨፍጫፊዎቹ ዓይን የነባርና የመጤ ግጭት ተደርጎ የሚታይ ነው፡፡ የሩዋንዳ የዘር ፍጅት የሰው ልጅ ጭካኔ ልክ የታየበት ነው፡፡

የጥላቻ ንግግር ሰዎች ባላቸው ማህበራዊ መሰረትና አቋም ወይም ርዕዮታለም ላይ በመመርኮዝ ሰዎችን በቡድን ወይም በተናጠል መገለልና መድሎ እንዲደርስባቸው ማድረግ ነው፡፡ ይህ አይነት መገለልና መድሎ ብሎም እልቂት በሩዋንዳ ብቻ ሳይሆን በአይሁዶች፣ጆፕሲዎችና በአወስትራሊያ ነባር ህዝቦችም ላይ ጭምር የደረሰ ነው፡፡ በተመሳሳይ ፍጅትና ጭካኔ የተፈጸመባቸው የናዚዎችና የአርመኖች እልቂቶች እንደሩዋንዳው መንስኤአቸው የዘር ጥላቻ እንዲፈጠር በተደረገ ከፍተኛ የጥላቻ ንግግር ቅስቃሳ ሳቢያ ነበር፡፡የጥላቻ ንግግር ወይም ዘመቻ መሰረተቢስ በሆነ ምክንያት ላይ ተመስርቶ በሰዎች ላይ አሉታዊ አስተሳሰብን መጫን ነው፡፡ ይህ ሁሉ እልቂትና ጥፋት የተፈጠረው እኛ በጣም ቀላል አድረገን በምናየው የሀሰት መረጃና የጥላቻ ንግግር ዘመቻ ነው፡፡ ውሸት ሀገር ያፈርሳል፣ ሰዎችን ያለስራቸው በማያውቁት ነገር ችግር ውስጥ ይጥላል፡፡ የጥላቻ ንግግር ደግሞ በመገናኛ ብዙሃን ሲታገዝ ችግሩን የበለጠ ያባብሰዋል፡፡

ምንጭ (መምህር ግርማ 2011 ሀቱቱሲ የትርጉም ስራ)

ምንባቡን ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎቹ ድጋሚ እንዲነበብላቸው ፍላጎት ካላቸው ይጠይቋቸው፡፡ ፍላጎት ካላቸው በመጠነኛ ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡ አለበለዚያ ግን ወደቀጣዩ ተግባር ይለፉ፡፡

በአዳምጦ መረዳት ስር የቀረቡትን የእውነት ሐሰት ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ሙሉ በሙሉ መመለስ ከቻሉ ጥሩ ካልሆነ ግን

ያልመለሱት ጥያቄ የሚገኝበትን አንቀጽ ያስታውሷቸውና ለመመለስ ሙከራ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ.ሐሰት | መ. ሐሰት |
| ለ. እውነት | ሠ. እውነት |
| ሐ. ሐሰት | ረ. እውነት |

ክፍል ሁለት ንባብ

- በማዳመጥ ጊዜ የቀረበውን ምንባብ ታሪክ በጥያቄና መልስ ያስታውሷቸው፡፡ የዕለቱን ምንባብ ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸውና ከማዳመጥ ምንባብ ታሪክ ጋር ሊኖረው የሚችለውን ዝምድና እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል በቅድመ ንባብ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በቃል ያሰሯቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች እየተሳተፉ መሆኑን ይከታተሉ፡፡ ጥያቄዎቹን ሰርተው ሲጨርሱ ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ምን ያህል ትክክል እንደሆነ ምንባቡን ሲያነቡ እያረጋገጡ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- ከዚያም ምንባቡን በጥሞና እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ እነሱ ሲያነቡ እርስዎ እያንዳንዱ ተማሪ እያነበበ መሆኑን ለማረጋገጥ ቅኝት ያድርጉ፡፡ ንባቡን ገታ አድርገው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በፊት የሰጡትን ግምትና ከምንባቡ ያገኙት ሀሳብ ተመሳሳይ መሆኑንና አለመሆኑን ከነምክንያቱ እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡

ምንባቡን አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ ከምንባቡ የሚጠይቁት ጥያቄ ካለ የመጠየቅ እድል ይስጧቸው፡፡ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ በራሳቸው እንዲሞክሩ ያድርጉና ከመለሱ መልካም ካልሆነ ግን እርስዎ ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡

በመቀጠል በአንብቦ መረዳት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡ በመጀመሪያ በመልመጃ ሁለት ስር የቀረቡትን የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች በምክንያት እያስደገፉ በቃላቸው እንዲናገሩ ያድርጓቸው፡፡

በመልመጃ ሶስት ስር የቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን ሲያነቡ የቃላት አገባባዊ ፍች የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ የቀረቡት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ፍች የሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች እንዲሰሩባቸው ይግለፁላቸው፡፡

በመልመጃ አራት ስር በቀረቡት ሶስት የመወያያ ጥያቄዎች ላይ ለመወያየት ያመች ዘንድ ቡድን እንዲመሰረቱ ያድርጉ፡፡ በዚያውም አወያይና ጸሀፊ መርጠው የውይይት መመሪያ ጠብቀው እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ ውይይቱ ሲካሄድ እየተዘዋወሩ ተማሪዎቹን ይመልከቷቸው፡፡ የማይሳተፉ ተማሪዎች ካሉ እንዲሳተፉ በመንገር ቡድኑን እንዲሳተፉ ይግለፁላቸው፡፡

ውይይቱን ካአጠናቀቁ በኋላ የቡድን ተጠሪዎች በተራ በተራ የውይይቱን ውጤት በንባብ እንዲቀርቡ ድርጉ፡፡ ላደረጉት ተሳትፎ በጣም ጥሩ፣ እጅግ በታም ጥሩ፣ አመሰግናሉ፣ ጎበዝ፣ ወዘተ ሚሉትን የማበረታቻ ቃል በመጠቀም ድጋፍዎትን ይግለፁላቸው፡፡ ከቡድኑ መካከል የተሻለ ሀሳብ ያቀረበ ካለም በማስጨብጨብ ያበረታቱዋቸው፡፡ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጡዋቸውና የእለቱን ትምህርት ያጠናቁ፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆኑ ‹‹ ሐሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ መልሱ፡፡

ሀ. እውነት

ለ. እውነት

ሐ. ሐሰት

መ. እውነት

ሠ. ሐሰት

ረ. ሐሰት

ሰ. ሐሰት

ሸ. እውነት

መልመጃ ሶስት

በሚከተሉት የተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ማፍረሻ

ለ. ቁርኝት

ሐ. መውጣት

መ. መጥፎ አመለካከት

ሠ. ማሳደግ ፣ ማሻሻል

ረ. ብቸኛ ማድረግ

ሰ. እገዳ ፣ ክልከላ

ሸ. ግዴለሽነት

ክፍል ሶስት ቃላት

የቃላት አገባባዊ ፍቺ

- በቃላት ትምህርት ስር ተማሪዎች ለቃላት ተመሳሳይ ተቃራኒ እና መዝገበቃላዊ ፍቺ እንዲሰጡ በተለያየ መንገድ ቀርቦላቸዋል:: ስለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ቀደም ሲል ስለተማሩ ምንም ማብራሪያ መስጠት ባያስፈልግም ስለመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ግን የተወሰነ ፍንጭ ይስጧቸው::
- በመጀመሪያ በአዛምድ መልክ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን እየፈለጉ እንዲያዛምዱ፣ ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ እየሰጡ ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ ከመዝገበ ቃላት እየፈለጉ እንዲሰጡ ያስርዷቸው:: የሰጡትን ምላሽ እንዲቀርቡ በማድረግ በትክክል መመለሳቸውን ያረጋግጡ:: ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ ማስተካከያ በመስጠት እርማት እንዲወስዱ ያበረታቷቸው::

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

በ‹‹ሀ››ስር ለቀረቡት ቃላት በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት በፍቺ ተመሳሳይ የሚሆኑትን እየመረጣችሁ አዛምዱ::

1. ሠ
2. ሐ
3. ለ
4. ሀ
5. መ

መልመጃ ሶስት

ለሚከተሉት ቃላት ከመዝገበ ቃላት ፍቻቸውን ፈልጋችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ምሳሌ፣ ፍቱን = መድሐኒት

ለ. ተንኮል

ሐ. ህልም

መ. ፊዝ፣ ምፀት

ቀ. ንጋት

ሠ. የስልጣን ብልግና

ረ. ታላቅ ደስታ

ሰ. ወፈረ

ሸ. አገናዘበ

መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እየሰጣችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ሀ. ውድቀት

ለ. የመጨረሻ

ሐ. ቀጠለ

መ. መርጋት

ሠ. መታጠፍ

ረ. ሰነፍ

ክፍል አራት ጽሕፈት

አመሳስሎ መፃፍ

- መምህር ወደ ፅህፈት ተግባር ከመግባትዎ በፊት ከስር የቀረበውን ስለ ሀቅና ስለግል አስተያት ምንነት በምሳሌ ተደገፊ ማስታወሻ ለተማሪዎቹ ያስረዷቸውና ማስተዋሻ እንዲፅፉ ያድርጉ፡፡

ማስታወሻ፡

ሀቅና የግል አስተያየት

የግል አስተያየት የተናጋሪዎችን አመለካከትና ስሜት የሚያንፀባርቅ ሲሆን ስለትክክለኛነቱ በመረጃ ሊረጋገጥ የማይችል ሀሳብ ነው፡፡በሌላ አገላለፅ የግል አስተያየት እውነት ይሁን ሀሰት ለማረጋገጥ የሚያስቸግር በአብዛኛው ሰው ተቀባይነት የሌለው ፣በሳይንስ ያልተረጋገጠ፣በይሆናል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሌላ በኩልሀቅ የሆነ አስተያየት በእውነት ላይ የተመሰረተና በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል፣ አስተያየቱ ስለ እውነትነቱ በሳይንስ ማረጋገጥ የሚቻልበት ነው፡፡

ምሳሌ፡-

- በዓለም ላይ ያሉ ቋንቋዎች ሁሉ እኩል ናቸው፡፡በሀቅ ላይ የተመሰረት አስተያየት
- ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ የሚተላለፊው በዋነኛነት ልቅ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው፡፡ በሀቅ ላይ የተመሰረተ አስተያየት
- የአማርኛ መምህሬ የሚወደኝ አይመስለኝም፡፡ በግል አስተያየት ላይ የተመሰረተ
- ሴቶችን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው፡፡ በሀቅ ላይ የተመሰረተ አስተያየት

- የጤፍ ዋጋ በሚቀጥለው ወር መቀነሱ አይቀርም፡፡ በግል አስተያየት ላይ የተመሰረተ

❖ በመቀጠልም በመልመጃ አንድ ስር ቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ሀቅና የግል አስተያየት በማለት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ የሰጡትን መልስ እንዲቀርቡ በማድረግ ትክክለኝነታቸውን ያረጋግጡ፡፡

❖ በመልመጃ ሁለት ስር አንድ አንቀፅ ፅሁፍ ቀርቧል፡፡ፅሁፉን ደጋግመው ካነበቡ በኋላ አስመስለው ሌለ ፅሑፍ ፅፈው እንዲሳዩ ይግለፁላቸው፡፡፡

❖ የፃፉትን ፅሑፍ በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ጋር ተቀያይረው እንዲገማገሙ ያድርጉና አስተያየት እንዲሰጣጡ ያድርጉ፡፡

❖ በመጨረሻም በጽሁፋቸው ላይ የእርሰዎን አስተያትና ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮችበምሳሌው መሰረት ሀቅና የግል አስተያየት በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ሀቅ

ለ. ሀቅ

ሐ. ሀቅ

መ. የግል አስተያየት

ሠ. ሀቅ

ረ. የግል አስተያየት

ሰ. ሀቅ

ሸ. የግል አስተያየት

ቀ. ሀቅ

በ. ሀቅ

**ክፍል አምስት ሰዋስው**

**ቀላልና ዉስብስብ ዐረፍተ ነገሮችን መለየት**

- በክፍል አምስት ተማሪዎቹ የ“እና“ ን እና “ነገር ግን“ አያያዥ ቃላት ተጠቅመው ዓረፍተ ነገር እንዲመሰርቱ፣ቅፅልን፣ ቀላልና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ለይተው እንዲገልፁ ይጠበቃል፡፡
- በተጨማሪም ስለ አያያዥ ቃላት ቀደም ሲል የተማሩትን በክለሳ መልክ ያስታውሷቸውና እናን እና ነገር ግን የሚሉ አያዥ ቃላት ተጠቅመው ዓረፍተ ነገሮችን አያይዘው እንዲፅፉ ይግለፁላቸው፡፡
- አያያዥ ቃላቱን ተጠቅመው የመሰረቱትን ዓረፍተ ነገሮች ይለዩላቸውና በትክክል መስራታቸውን ይፈትሹ፡፡
- በመቀጠልም ከቀረቡላቸው ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ግስ ሆኑትን ቃላት እየለዩ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- በመልመጃ አራት ስር ከቀረቡት ቃላት ቅፅል የሆኑትን ለይተው በቻርት ውስጥ ፅፈው እንዲያሳዩ ከመግለጽዎ በፊት እባክዎ መምህር ስለቅጽል ምንነትና ተግባር ከአምስተኛ ክፍል ትምህርታቸዉ እንዲያስታዉሱ ያድርጉ፡፡
- በመልመጃ አምስት ደግሞ ተዘረዘሩትን ቅፅሎች የባህሪ፣የአይነትና የመጠን እያሉ በመለየት በሰንጠረዥ እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ከዚህ በታች ስለ ቀላልና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በተመለከተ ማስታወሻ ቀርቧል፡፡ የቀረበውን ማስታወሻ ለተማሪዎች በደብተራቸው ያፅፏቸውና

ስለ ቀላል እና ውስብስብ አረፍተ ነገር ያስረዷቸው፡፡ቀላል ዓረፍተ ነገር በውስጡ አንድ ግስ ብቻ ያለው ሲሆን ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ደግሞ ሁለትና ከሁለት በላይ ግስ የሚይዝ መሆኑን ይግለፁላቸው፡፡ በመልመጃ አንድ ላይ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ቀላልና ውስብስብ ብለው እንዲለዩ ይግለፁላቸው፡፡

**ማስታወሻ፡-**

**ዓረፍተ ነገር**

**ዓረፍተ ነገር ቃላት እና ሀረጋት በስርዓት ተቀናጅተው ሙሉ ስሜት በሚሰጥ መልኩ የተደራጀ አንዱ የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡ አንድ ዓረፍተ ነገር በውስጡ ከሚይዘው ግስ ብዛት አንፃር ቀላልና ውስብስብ ብሎ መክፈል ይቻላል፡፡**

1. **ቀላል ዓረፍተ ነገር፡-**

ይህ የዓረፍተ ነገር አይነት አንድ ግስ ብቻ ያለው ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ከስማዊ ሀረግና ከግሳዊ ሀረግ የሚዋቀር ነው፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ፋጡማ የቤቱን ግቢ አፀዳች፡፡

ለ. ያሬድ ወደትምህርት ቤት በጠዋት ሄደ፡፡

ሐ. አስቴር ብርጭቆውን ወለወለች፡፡

መ. ተማሪዎች በትምህር ቤታቸው የሰላም ክበብ መሰረቱ፡፡

2. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

ይህ የዓረፍተ ነገር አይነት ሁለትና ከዚያ በላይ ግስ ያለው ሲሆን በተለያዩ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ተዋህዶ ይቀርባል። ስለሆነም ውስብስብ ዐረፍተ ነገር ዋና መለያው በውስጡ በያዘው የግስ ብዛት ነው።

ምሳሌ፦

ሀ. ናትናኤል ምሳውን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ።

ለ. ልጁ እጁን ታጥቦ ምሳውን በላ።

ሐ. ኢትዮጵያውያን ምርታቸውን ወደ አለም ገበያ ወስደው መሸጥ ጀመሩ።በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት ቀላል ወይም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በማለት ለይታችሁ አሳዩ።

ሀ. ቀላል

ለ. ውስብስብ

ሐ. ቀላል

መ. ቀላል

ሠ. ውስብስብ

ረ. ውስብስብ

ሰ. ውስብስብ

ሸ. ቀላል

ቀ. ውስብስብ

በ. ውስብስብ

መልመጃ ሁለት

ቀጥሎ በቀረቡትዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች በምሳሌው መሰረት ለዩና በደብተራችሁ ፃፉ።

ሀ. ስለመጡ ተቀበለቻቸው

ለ. ፈጥኖ ፤ በርግጎ ፤ተነሳ

ሐ. ለብሰዋል

መ. የገዙት ፤ያምራል

ሠ. ሲመለስ ፤ ቀየረ

ረ. ሲያጋጥም ፤ማጽናናት ፤ ያስፈልጋል

መልመጃ አራት

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቅፅሎች በተሰጠው ምሳሌ መሰረትየአይነት፣ የባህሪና የመጠን አመልካች እያላችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ መድቡ።

| ተ/ቁ | አይነት ገላጭ ቅፅል | ባህሪ ገላጭ ቅፅል | መጠን ገላጭ ቀፅል |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀያይ | ሰነፍ | አጭር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | ሰማያዊ | ንቁ | ደንዳና |
| 3 | አረንጓዴ | ሞኝ | ግዙፍ |
| 4 | ሮዝ | ሆዳም | ረጂም |
| 5 | | በጎ | ጠባብ |
| 6 | | | |

# ምዕራፍ ስምንት

## ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ በኢትዮጵያ ክፍለ ጊዜ 18

**የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች**

- ✓ ባለብዙ ቅጥያ ምዕላዶችን ይለያሉ
- ✓ የራሳቸውን አመለካከት ይፅፋሉ
- ✓ የፅሁፍ አላባውያንን ይገልፃሉ
- ✓ ለምዕላዶች ትርጉም ይሰጣሉ

**የምዕራፉ አጠቃላይ ይዘቶች**

- ➢ ዋና ሀሳብ ለማግኘት ማዳመጥ
- ➢ ማዳመጥና ክርክር
- ➢ ማንበብና ፅብረቃ
- ➢ የፅሁፍ ክፍሎች
- ➢ የቃላት ተቃራኒ
- ➢ ሳቢ/ተሻጋሪና ኢሳቢ/ ኢ-ተሻጋሪ ግሶች

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

‹‹ ጠርጥር በገንፎ ዉስጥ አለ ስንጥር››

**የትምህርቱ አቀራረብ**

- መምህር በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረበው ምንባብ ኤች አይ ቪ ኤድስን የተመለከተ ነው። ምንባቡ ቋንቋን ከማስተማር ባሻገር በሀገራችን ላይ ጉዳት እያደረሰ ስላለው የኤድስ በሽታ ለተማሪዎቹ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያግዛል። በዚህ አጋጣሚ ተማሪዎቹ የበሽታውን አስከፊነት ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቱት ለማድረግ የእርስዎ ጥረት በጣም አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ከቋንቋ ክሂል ትምህርት በተጨማሪ ስለበሽታው ግንዛቤ የሚያስጨብጥ አቀራረብን ቢጠቀሙ ተመራጭነት ይኖረዋል።
- በቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስር ያሉትን ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲመልሱ በማድረግ ያነቃቋቸው። እያንዳንዱን ጥያቄ ሁሉም ተማሪ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው።
- ለጥያቄዎቹ የሰጡትን መልስ በማመስገን ተቀብለው ወደዋናው የማዳመጥ ተግባር እንዲሸጋገሩ ያግዟቸው። ከዚያ በፊት ግን በመልመጃ አንድና በመልመጃ ሁለት የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲያነቡ ያስረዷቸው።
- ጥያቄዎቹን አንብበው ሲያጠናቅቁ ምንባቡ ሲነበብላቸው ጥያቄዎቹን እያሰቡ እንዲያዳምጡ ይግለጹላቸው።በመቀጠል ምንባቡን ያንብቡላቸው።

የተወለድኩት አዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡ እረዳት አልነበረኝም፡፡ በዚህ ምክንያት በአንድ ሱቅ ውስጥ በሻጭነት ተቀጠርኩ፡፡ ግማሽ ቀንእየሰራሁ ግማሽ ቀን ደግሞ ትምህርቴን እማር ነበር፡፡ በምሰራው ስራ የተሻለ ገንዘብ በማግኘቴ ገንዘብን ይበልጥ እየተላመድኩ ሄድኩና ስምንተኛ ክፍል እንደደረስኩ ትምህርቴን አቋረጥኩት፡፡ ቀስ በቀስ ስራው በፈጠረልኝ አጋጣሚ ከተለያዩ የንግድ ሰዎች ጋር ተዋወቅሁ፡፡ ለገበያ ተፈላጊ የሆኑ እቃዎችን መለየት ቻልኩ፡፡ አዳዲስ እቃዎችን እየተረከብኩኝ ለሌሎች ባለሱቆች መሸጥ ጀመርኩ፡፡ በዚህም ጠቀም ያለ ትርፍ ወደማግኘቱ ስሸጋገር የሻጭነት ስራዬን ተውኩና በድለላ ስራ ላይ ተሰማራሁ፡፡በሱቅ ውስጥ በምሰራበት ጊዜ ምንም አይነት ትርፍ ጊዜ አልነበረኝም፡፡ በአዲሱ ስራዬ ግን ትርፍ ጊዜ በማግኘቴ ለሱስ ተጋላጭ እየሆንኩ መጣሁ፡፡ጫት የሚቅሙ ጓደኞች ስላፈራሁ ሁልጊዜ ከምሳ ሰዓት በኋላ የምውለው በጫት መቃሚያ ስፍራ ሆነ፡፡ ከጫት በኋላ ደግሞ ወደመጠጥ ቤት እሄዳለሁ፡፡ ከአንድ ቤት መጠጣት እጀምርና በሞቅታ የተለያዩ መጠጥ ቤቶችን በማዳረስ ስጠጣ አመሻለሁ፡፡ በስካር መንፈስ ብዙ ሴተኛ አዳሪዎችን እየጋበዝኩና ከእነሱ ጋር እየተጫወትኩ አመሽና ከአንዷ ደንበኛዬ ጋር አድራለሁ፡፡ በዚህ ምክንያት በርካታ የቡና ቤት ሴቶች ያውቁኝ ነበር፡፡ ሁኔታዬ ያላማራቸው ብዙ ሰዎች የባህሪ ለውጥ እንዳመጣ ይመክሩኝ ጀመር፡፡ በዚህም የመጠጡን ነገር በመጠኑም ቢሆን ልቆጣጠረው ሞከርኩ፡፡ ከዚህ በፊት ከነበሩኝ የቡና ቤት ሴት ደንበኞች ጋር የነበረኝን ግንኙነት ግን ማቆም አልቻልኩም ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜያትን አሳለፍኩ፡፡ በሂደትም ብርድ ብርድ የሚልና እንደሳል ያሉ የህመም ስሜቶች ይሰሙኝ ጀመር፡፡ ስሜቶቹ ሲደጋገሙብኝ በአካባቢዬ በሚገኘው አንድ ጤና ጣቢያ ሄጄ ተመረመርኩና የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እንዳለብኝ ተነገረኝ፡፡ህክምናውን መከታተል ጀመርኩ፡፡ ጤንነቴ ለውጥ እያሳየ መጣ፡፡ ነገር ግን እንደበፊቱ ተሯሩጬ መስራት አልቻልኩም፡፡ ከሳንባ ህመሜ ባገግምም የሌሎች በሽታ

ስሜቶች ይታዩብኝ ጀመር፡፡ ሰውነቴም እየከሳ መጣ፡፡ ይህንን ያስተዋሉ የቅርብ ጓደኞቼ ምንአልባት ኤች አይ ቪ ሊሆን ይችላል በሚል የደም ምርመራ እንዳደርግ መከሩኝ፡፡ እኔም ምክራቸውን ተቀብዬ ወደ ሀኪም ቤት ሄጄ ተመረመርኩ፡፡ ከምርመራው በኂላ ኤች አይቪ በደሜ ውስጥ መኖሩ ተነገረኝ፡፡ ውጤቱን ስሰማ ያለሁበትን አላውቅም ነበር፡፡ ዶክተሩ መክረውና አረጋግተው እንደማንኛውም ሰው መኖር እንደምችል ከነገሩኝ በኂላ ቀጠሮ ሰጥተው ሸኙኝ፡፡ በልጅነት እድሜዬ ኑሮየን ለመምራት ሰርቼ ገንዘብ ማግኘት ብችልም ገንዘቤን በአግባቡ መጠቀም አልቻልኩም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ለኤች አይቪ ኤድስ ተጋላጭና ህመምተኛ ሆንኩ፡፡ አሁን የሀኪሜን ምክር እየተከታተልኩና ለኤድስ ህሙማን የሚሰጠውን መድሃኒት እየወሰድኩ ነው፡፡ ባለማወቁ በሽታውን ለበርካታ ሴቶች ማስተላለፌ ስለሚፀፅተኝ የእኔ እጣ ፈንታ በሌሎች እንዳይደርስ እየመከርኩና እያስተማርኩኝ እገኛለሁ፡፡

ምንጭ(አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሰባተኛ ክፍል

2007፣51 ተሻሽሎ የተወሰደ)

- የማዳመጥ ተግባር ሲያበቃ ቀድመው ያነበቧቸውን ጥያቄዎች ደግመው እንዲያነቡ ያድርጉና ባዳመጡት መሰረት ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- በመልመጃ ሶስት ስር በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ለመወያየት በሚያስችል መልኩ ይመድቧቸው፡፡ በራሳቸው አወያይና ፀሀፊ እንዲመርጡ ያድርጉ፡፡
- በሁሉም ጥያቄዎች ላይ ማስታወሻ እየያዙ እንዲወያዩ ያስረዷቸው፡፡ በውይይቱ ሂደት እርስዎ እየተዘዋወሩ ይከታተሉ፡፡

- ❖ የማይሳተፉ ተማሪዎች ካሉ እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡ የተወያዩበትን ሀሳብ ለማስቀረብ ለቡድኑ ጥያቄዎቹን ለቡድኑ ከፋፍለው ይስጧቸው፡፡
- ❖ የተሰጣቸውን ጥያቄ ብቻ እንዲያቀርቡ በመንገር ጥያቄው የደረሰው ቡድን ሲያቀርብ ሌሎቹ እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡
- ❖ በቀረበው ሀሳብ ላይ ተጨማሪ ሀሳብ ያለው ቡድን ካለ እንዲያቀርብ እድል ይስጡ፡፡ ለምሳሌ ጥያቄ ቁጥር አንድ የደረሰው ቡድን ሲያቀርብ ሌላው ቡድን አዳምጦ በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ ተጨማሪ ሀሳብ ያለው ካለ እንዲናገር መስጠት ማለት ነው፡፡ በቀረበው ሀሳብ እርስ በርስ አስተያየት እንዲለዋወጡ ያድርጉ፡፡
- ❖ በዚህ መልክ ሁሉም ቡድን ካቀረበ በኂላ የማጠቃለያ ሀሳብ እርስዎ ይሰጧቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. አስፈላጊ

ለ. እድል፣ድርሻ

ሐ. ስላገኘሁ

መ. መዳረግ

ሠ. መስከን፣

ረ. በጎ ሆነ - ተሻለው

ሰ. ተጨማሪ

ሽ. ማቆም - መተው

ቀ. ተግሳፅ

ክፍል ሁለት ንባብ

❖ ወደቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ከመግባትዎ በፊት ስለ ርዕሱ ጠቅለል ያለ ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡

❖ ለምሳሌ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ የምታውቁትን ግለጹ፡፡ የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡላቸው ተማሪዎቹ ስለ በሽታው ያላቸውን የቀደመ ዕውቀት ስለሚያስገነዝብዎ ለተማሪዎቹ ስለ በሽታው ከምን ተነስተው እስከ ምን ድረስ መረጃ መስጠት እንዳለብዎ ይጠቁምዎታል፡፡

❖ በመቀጠል የቅድመ ንባብ ጥያቄዎቹን በቃል እንዲመልሱ ይግለጹላቸው፡፡ ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልስ ከሰጡ በኋላ ምንባቡን ተራ በተራ ድምፃቸውን እያሰሙ እንዲያነቡ በማድረግ ሌሎቹ ደግሞ ንባቡን እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡

❖ በዚህ ጊዜ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎቹ ካሉ እገዛ ያድርጉላቸዉ፡፡

❖ ማንበባቸውን ሲያጠናቅቁ በንባብ ጊዜ ሀሳቡን ለመረዳት ያስቸገራቸው አዳዲስ ቃላት ካሉ እንዲጠይቁ እድሉን ይስጧቸው፡፡ የቀረበ ጥያቄ ካለ መልሱን ይስጧቸውና ወደተመልመጃ ሁለት ይለፉ፡፤

❖ በመልመጃ ሁለት ስር የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ተመሳሳይ ፍቺ እንዲሰጡ፣ በመልመጃ ሶስት ስር በቀረቡት ዓረፍተ

ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ሌላ ሊተካ የሚችል ቃል ፈልገው እንዲተኩ ይግለጹላቸው፡፡

- የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ ለቃላቱ በትክክል ተመሳሳይ ፍቺ መስጠታቸዉንና ለተሰመረባቸው ቃላት ሌላ አቻ ቃል መተካት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በዚህ ጊዜ ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ ማስተካከያውን ይስጧቸውና እርማት እንዲወስዱ ያበረታቷቸው፡፡
- በመጨረሻ በመልመጃ አራት ስር ያለውን ሰንጠረዥ በምንባቡ ውስጥ ካገኙት ሀሳብ ወጣ ብለው እንዲያሰላስሉ የሚያደርግ በመሆኑ በቡድን እየተወያዩ የኤች አይ ቪ ቫይረስ መተላለፊያመንገድ የሆኑትንና ያልሆኑትን ለይተው እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- ተማሪዎቹ እየተወያዩ የሚጽፉትን እየተዘዋወሩ በመመልከት የበሽታውን መተላለፊያ መንገድ የሆኑትንና ያልሆኑትን በትክክል ይግለጹላቸውና በእውነት የተደገፈ መረጃ እነዲኖራቸው ያግዟቸው፡፡
- የቀረበውን ሰንጠረዥ በሚሞሉ ጊዜ ተማሪዎቹ የማሰላሰል፣ሀሳብ የማፍለቅና የመፃፍ ክሂል ያዳብራሉ፡፡ እግረ መንገድ ደግሞ ስለበሽታው መተላለፊያ መንገድ በቂ ግንዛቤ ስለሚያገኙ አላስፈላጊ አግላይነት ተግባር እንዳይፈፅሙ ስለሚያደርግ ትኩረት በመስጠት ተማሪዎቹ እንዲተገብሩት ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

**መልመጃ ሁለት**

ለሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. መረበሽ

ለ. መለወጥ ሰ. ተጽእኖ

ሐ. መሰራጨት ቀ. ህሊና

መ. ችግር

ሠ. ድካም፣ውጣውረድ

ረ. አጋዥ፣ረዳት

**መልመጃ ሶስት**

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በፍች የሚተካቸውን ቃላትና ሀረጋት እያስገባችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. ቁጥር መ. ዕፅ

ለ. ከሚዛመትባቸው ሠ. ማእከላት

ሐ. ተጎጂ ረ. ረቂቅ

**ክፍል ሶስትቃላት**

**የቃላት ተቃራኒ ፍቺ**

- በዚህ ክፍል ተማሪዎቹ ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ በመስጠት ከተዘረዘሩት ቃላት በፍቺ ልዩ የሆነውን ማውጣትና በአረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢውን ቃል እያስገቡ ባዶ ቦታውን እንዲያሟሉ ይጠበቃል፡፡
- በመልመጃ አንድ ስር በአዛምድ የቀረበውን ተግባር በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ከ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት በፍቺ ተቃራኒ የሆኑትን እየመረጡ እንዲያዛምዱ ያስረዷቸው፡፡
- በመቀጠል ከአንድ እስከ አስር ተዘርዝረው ከቀረቡት ቃላት በፍቺ ልዩ የሆነውን ለይተው እንዲፅፉ ይግለፁላቸው፡፡
- በመጨረሻም በመልመጃ ሶስት ስር ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ባዶ ታዎች የሚያሟሉ ከላይ ከተዘረዘሩት ቃላት እየመረጡ እንዲሞሉ ይግለፁላቸው፡፡
- በትክክል መልስ መስጠታቸውን ለማወቅ ደብተራቸውን ሰብስበው ያርሙላቸው፡፡ በዚያውም የተሳሳቱት ካለ ማስተካከያ ይስጧቸው፡

መልመጃ አንድ

በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጎች በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ውስጥ ተቃራኒ የሚሆኑትን በመምረጥ አዛምዱ፡

የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

| | |
|---|---|
| 1. ሠ | 7. ሐ |
| 2. ሰ | 8. ቀ |
| 3. በ | 9. ረ |
| 4. መ | 10. ለ |
| 5. ሀ | |
| 6. ሸ | |

መልመጃ ሁለት

ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ልዩ የሆነውን ቃል እየመረጣችሁ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

1. መ
2. ሐ
3. ሀ
4. ሀ
5. መ
6. ሐ
7. ሀ
8. መ
9. ሀ
10. ለ

መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ቀጥለው በአረፍተ ነገሮች ውስጥ አስገቡ፡፡

ሀ. ምናቡ

ለ. ዘመም

ሐ. ብርድ ብርድ

መ. ቆረጥ ቆረጥ

ሠ. መቋጫው

ረ. በተረጋጋ መንፈስ

ሰ. መንገድ

ሸ. ጥንካሬ

ቀ. ጥርግርግ

በ. ጥቅልል

## ክፍል አራት ጽሕፈት

### የድርሰት ክፍሎች

- በፅህፈት ስር የቀረበውን የክርክር መመሪያ ማስታወሻ በደብተራቸው ፅፈው እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡
- ከዚም ክርክር በማካሄድ ቅድመ ዝግጅት እንደሚያስፈልገውና በክርክር ጊዜ ምን መደረግ እንደሚገባ አፅኖት ሰጥተው በጥያቄና መልስ ገለፃ ያድርጉላቸው፡፡
- ከዚያም ለክርክር የሚያስችል ቡድን እና ዳኛ በፈቃደኝነት እንዲመርጡ ያድርጉና ከቀረቡላቸው ርዕሶች አንዱን መርጠው እንዲዘጋጁ ይግለፁላቸው፡፡ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ ክርክሩን እንዲያካሂዱ ያድርጉ፡፡
- ክርክሩ ሲካሄድ ከተከራካሪና ከዳኞች ውጭ ያሉት ተማሪዎች እየተከታተሉ ማስታወሻ እንዲይዙ ያስረዷቸው፡፡ በዚህ ጊዜ እርስዎ ተከራካሪዎቹ የክርክር መመሪያን ጠብቀው መከራከራቸውን በመከታተል ማስታወሻ ይያዙ፡፡
- ክርክሩ ሲጠናቀቅ ቅድሚያ ክርክሩን ሲከታተሉ የነበሩት ተማሪዎች አስተያየታቸውን እንዲገልፁ ይጋብዟቸው፡፡
- መጨረሻውም ማጠቃለያ ክርክሩን ጠንካራ ጎንና መሻሻል የሚገባውን ነጥብ በመጥቀስ ያስረዷቸው፡፡
- ሌላው በፅህፈት ስር የቀረበው መልመጃ የፅሁፍ ክፍሎች መለየት ከዚም የቀረበውን ፅሁፍ እንዲያነቡ፤ ባነበቡት ፅሁፍ መሰረት ደግሞ መግቢያ፣ሀተታና መደምደሚ ብለው ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ያድርጉ፡፡
- በዚህ መሰረት በመምህሩ መምሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረበውን የፅሁፍ ክፍሎች ማስታወሻ በደብተራቸው ያፅፏቸው፡፡

- ❖ ከዚያም በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በምሳሌነት የቀረበውን ፅሁፍ በመጠቀም የፅሁፍ ክፍሎችን ምንነትና በፅሁፍ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ በመቀጠል በምሳሌ የቀረበውን ፅሁፍ በድጋሚ አንብበው በዚሁ መሰረት ከስር ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን መርጠው መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ ብለው ፅሁፍ እንዲፅፉ ይግለፁላቸው፡፡
- ❖ የፃፉትን ፅሁፍ ከጓደኖቻቸው ጋር እንዲለዋወጡ በማድረግ የፅሁፍ ክፍሎችን የያዘ መሆን አለመሆኑን በትክክል መግቢያ፣ሀተታና መደምደሚያ ላይ መገለፅ ያለባቸው ሀሳቦች መቅረብ መቻላቸውን እንዲፈትሹ ያስገንዝቧቸው፡፡
- ❖ ከዚያም ያገኙትን ጠንካራና መስተካከል ወይም መሻሻል የሚገባውን ነጥብ እንዲገልፁ ያድርጉ፡፡
- ❖ ለተሰጠው አስተያየት ምስጋና አቅርበው እርስዎ የያዙት ፅሁፍ ካለ ሶስቱን የፅሁፍ ክፍሎች የያዘ ፅሁፍ ለምሳሌነት በማቅረብ ትምህርቱን ያጠናክሩ፡፡
- ❖ ካልሆነ ግን ከተማሪዎቹ መካከል የተሻለ የሰራውን አስቀርበው የእለቱን ትምህርት ማጠቃለያ መስጠት ይችላሉ፡፡

ማስታወሻ፡-

የድርሰት ክፍሎች

ድርሰት ሰፋ ያለ ሀሳብ የሚቀርብበበት እንደመሆኑ መጠን በሶስት ዋና ዋና ክፍልች ሊደራጅ ይችላል፡፡

ሀ. መግቢያ፡- ወደ ዋናው ጉዳይ እያዋዛ የሚያስገባ ክፍል ነው፡፡ ይህ ስራ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰራው የድርሰቱ የመጀመሪያ አንቀፅ ነው፡፡ በዚህ አንቀፅ ላይ ዋናው ጉዳይ አይነሳም፡፡ መግቢያ አንቀፅ ወደ ዋናው መልዕክት

የሚወስደን ጥርጊያ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አንባቢያንን ወደ ቀጣዩ ክፍል ለማንደርደር መግቢያውን ማራኪና ውበት ለበስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን የምናደርገውም መግቢያውን በምሳሌያዊ ንግግሮች በአባባሎች በአጫጨር ሳቢ ጥቅሶች ወዘተ. ከሽነን በማቅረብ ነው፡፡ መግቢያ አንቀፅ የራሱ የሆነ ሀሳብ ስለማይኖረው የዋነኛ ዓረፍተነገርና የመዘርዝር ጣጣ ላይታይበት ይችላል፡፡

ለ. ሀተታ፡- ይህ ክፍል የድርሰቱ ዋና ሀሳብ የሚተላለፍበት በመሆኑ በርከት ከት ባሉ አንቀፆች ሊገነባ ይችላል፡፡ አንቀፆቹም የየራሳቸውን ሀሳብ ያራምዳሉ፡፡ ይሁንና የየአንቀፆቹ ሀሳብ ትትስር የሚታይበት ሊሆን ይገባል፡፡ ሀሳቦቹን ለማስተሳሰርም አልፎ አልፎ መሸጋገሪያ አንቀፅን በመዕከላዊ ክፍል ውስጥ እንደ ሳጋ ማስገባት የተለመደ ነው፡፡ መሸጋገሪያ አንቀፆች የራሳቸው የሆነ የተለየ አሳብ አያነሱም፡፡ የሚስፋፉ ሀሳብ ስለማይቀርብባቸውም የሚገነቡት አብዛኛውን ጊዜ በሁለት ወይም በሶስት ዓረፍተ ነገሮች ነው፡፡ ማዕከላዊ ክፍል የድርሰቱ እንብርት ነው፡፡ ዋናውን ሀሳብ ተሸካሚ በመሆኑም በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን አንቀፆች እንደምናስተላልፈው ሀሳብ ስፋትና ጥበት ሁኔታ እያየን በወጉ መመጠንና ማከናበር ያስፈልጋል፡፡

ሐ. መደምደሚያ፡- የድርሰት ሀሳብ በእንጥልጥል መቅረብ የለበትም፡፡ በማዕከላዊ ክፍል የቀረበው ዝርዝር ጉዳይ በመደምደሚያ ይቋጫል፡፡ እንደመግቢያ አንቀፅ ሁሉ አብዛኛውን ጊዜ በጥቂት ዓረፍተ ነገሮች የተገነባ አንድ አንቀፅ የድርሰት መደምደሚያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ አንቀፅ ላይ ቀደም ሲል ያልተወሳ አዲስ ሀሳብ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ይህም በመሆኑ በዋነኛ አረፍተ ነገርና ለመዘርዝር ትስስር ልንጨነቅ አይገባም፡፡ መደምደሚያ አንቀፅ በድርሰቱ ውስጥ የተነሱ አበይት ጉዳዮችን ሊያወሳ፣ ጭምቅ ሀሳብን ሊያቀርብ በአንባቢያን አዕምሮ ውስጥ ጥያቄን የሚያጭሩ ሀሳቦች ሊያስገባ ወዘተ ይችላል፡፡

ሰለሞን ሀለፎም የድርሰት አፃፃፍ ፣1997፣230-231)

ክፍል አምስት ሰዋስው

ሳቢና ኢሳቢ ግስ

በዚህ ክፍል የድርጊት ግሶችን የሚመለከት ይዘት ቀርቧል፡፡ የድርጊት ግስ ሳቢ ወይም ተሻጋሪ እና ኢሳቢ ወይም ኢተሻጋሪ ግስ ተብሎ እንደሚመደብ ከታች ያለውን ማስታወሻ በደብተራቸው ያፅፏቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎቹ የፃፉትን ማስታወሻ እንዲያነቡ ያድረጓቸው፡፡ በመጨረሻም ስለማስታወሻው ተማሪዎች ካነበቡት በተጨማሪ እርስዎ የማጠቃለያ ሀሳብ ይስጧቸው፡፡

ማስታወሻ፡-

የድርጊት ግሶች

የድርጊት ግስ አንድን ነገር በራሱ ወይም በሌላ ነገር ላይ የሚፈፀመውን ድርጊት ወይም ተግባር የሚገልፅ የግስ አይነት ነው፡፡ የድርጊት ግስ ሳቢ እና ኢሳቢ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ሀ. ሳቢ ግስ፡- ሳቢ ግስ የሚባለው ከተሳቢ ስም ጋር የሚዋቀር የግስ አይነት ነው፡፡ ሳቢ ግሶች ተሳቢ ይፈልጋሉ፡፡ ተሳቢውም ስም ወይም ተውላጠ ስም ሊሆን ይችላል፡፡ስለሆነም ግስ እና ስም(ተውላጠ ስም) ሳቢና ተሳቢ እየሆኑ ይዋቀራሉ፡፡

ምሳሌ1፡- በላ የሚለው ግስ ዳቦ ከሚለው ስም ጋር ይዋቀርና ዳቦ በላ ሰፋ ያለ መዋቅር ይፈጥራል፡፡ በዚህ መዋቅር ውስጥ በላ ሚለው ሳቢ ግስ ሲሆን ዳቦ የሚለው ስም የሱ ተሳቢ ነው፡፡ሳቢው ግስና ተሳቢው ስም ተዋቅረው የሚያስገኙት መዋቅር ሀረግ ሆኗል፡፡

ምሳሌ፡-2

ጠጣ የሚለው ግስ ወተት ከሚለው ስም ጋር ተዋቅሮ ወተት ጠጣ የሚል ሰፋ ያለ መዋቅር ፈጥሯል፡፡ በዚህ መዋቅር ውስጥ ጠጣ የሚለው ሳቢ ግስ ሲሆን ወተት የሚለው ስም ደግሞ ተሳቢ ነው፡፡፡

ለ. ኢሳቢ ግስ፡- ኢሳቢ ግስ የድርጊት ግስ ነው፡፡ ይሁን እንጅ አንደ ሳቢ ግስ ከተሳቢ ስም እና ተውላጠ ስም ጋር አይዋቀርም፡፡ በአጭሩ ተሳቢ ስአይፈልግም፡፡ በዚህ ምክንያት ብቻውን ወይም ስም ካልሆነ ሌላ ቃል ጋር ይገኛል፡፡

ለምሳሌ፡- 1

ተኛ እና ወደቀ የሚሉትን ግሶች ብንመለከት የድርጊት ግሶች ናቸው፡፡ ነገር ግን የሚስቡት ወይም የሚጎትቱት ስም የላቸውም፡፡ ሊኖራቸውም አይችልም፤ ምክንያቱም ሳቢ አደሉም፡፡ ነገር ግን ስም ካልሆኑ ሌላ ቃል ጋር ሊገናኙ ይችልሉ፡፡

ለምሳሌ፡- 2. ተራራ ላይ ወጣ፡፡

መሬት ላይ ወደቀ፡፡

በጥቅሉ ኢሳቢ ግሶች ተደራጊ አቻ የላቸውም፡፡ ስለዚህ በላ ብለን ተበላ ማላት ስንችል ወጣ፤ ብለን ተወጣ አንልም፡፡

- ❖ በማስከተል ከቀረቡላቸው ቃላት ውስጥ ሳቢ (ተሻጋሪ) ግስ እና ኢሳቢ(ኢተሻጋሪ) ግስ ሆኑትን ለይተው እንዲፅፉ ያግዟቸው፡፡ የሰሩትን እርዕስ በእርስ እርማት እንዲሰጣጡ ያድርጉና በተማሪዎች ዘንድ አከራካሪ የሆነ ነገር ከገጠማቸው በእርስዎ ዳኝነት ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ በመልመጃ ሶስት ስር ከቀረቡት ቃላት ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን ነጣጥለው እንዲያነቡ ይግለፁላቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም ተነጣጥለው ቀረቡትን ምዕላዶች አጣምረው በመጻፍ እንዲነቡ ያብራሩላቸው፡፡

በናሙናነት ለተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

ከሚከተሉት ግሶች መካከል ሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ፡፡

ሰቀለ ለካ

ሰበረ ሸጠ

በጠሰ መገበ

ቀደደለበሰ

ሰጠ

መልመጃ ሁለት

ከሚከተሉት ግሶች መካከል ኢሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ፈነዳ | ቀጠነ |
| ነደደ | አየለ |
| ደከመ | ወፈረ |
| ቀበጠ | አኮረፈ |
| ደመቀ | አለቀሰ |

መርጃ መሳሪያ

ሶስቱን የጽሁፍ ክፍሎች የያዘ የቻርት ላይ ጽሁፍ

ሳቢና ኢሳቢ ግስን በንጽጽር የያዘ የቻርት ላይ ጽሁፍ

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ባህላዊ ክንዋኔዎች

ክፍል ጊዜ 18

### የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ የተስማሙበትን ሀሳብያቀርባሉ
- ✓ አጫጭር ምንባብ አንብበው ወደ ሰንጠረዥ ይቀይራሉ
- ✓ በቃል የሚነበብላቸውን አስተካክለው ይጽፋሉ
- ✓ ከእርዕሱ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ይጽፋሉ
- ✓ ስርዓተ ነጥቦችን ጠብቀውያነባሉ

የምዕራፉ አጠቃላይ ዝርዝር ይዘቶች

- ➢ አዳምጦ መመዘን
- ➢ ማንበብና ቃላዊ ዘገባ
- ➢ የማመልከቻ ጽሁፍ
- ➢ ሀላፊ ጊዜ ግስ

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

**ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት**

**የትምርቱ አቀራረብ**

- ❖ በዚህ ምዕራፍ ስር ያሉትን መልመጃዎች ከመጀመርዎ በፊት ስለይቅርታ የተጻፈ ግጥም ወይም ተረት ያቅርቡላቸው፡፡
- ❖ ከዚያም ስላዳመጡት ግጥም ወይም ተረት ጭብጥ ወይም መልዕክት ይጠይቋቸው፡፡
- ❖ በዚህ ተግባር ተማሪዎቹን ካነቃቁ በኋላ የዕለቱን ትምህርት በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያዳመጡት ግጥም ወይም ተረት ከዕለቱ ትምህርት ርዕስ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲገምቱ በማድረግ ወደ ዋናው ትምህርት ያስገቧቸው፡፡
- ❖ ተማሪዎቹ ወደማዳመት ከመሄዳቸው በፊት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቹን በቃል ያሰሯቸው፡፡
- ❖ በአካባቢያቸው የሚያውቁት ባህላዊ የግጭት አፈታት ካለ እንዲናገሩ እድሉን ያመቻቹላቸው፡፡
- ❖ በሁለተኛ ደረጃ በመማሪያ መጽሐፋቸው ላይ የቀረበውን ምስል ተመልክተው የተረዱትን እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በዚህ ሁሉ ተግባር ለማዳመጥ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋግጠው ለማድመጥ የተዘጋጀውን ምንባብ በተገቢው ፍጥነት ያንብቡላቸው፡፡ በቅድሚያ ግን እያዳመጡ አዳዲስ ቃላትን እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

ሰዎች በጋራ ሲኖሩ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ የግጭቱ መጠን ይለያይ እንጂ፡ ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ግጭት አይቀሬ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ግጭቱን በወቅቱ በማስወገድ ሰላማዊና ጤናማ ህይወት መምራት ተገቢ ነው፡፡ በሀገራችን ለረጅም ዘመናት ሲሰራባቸው የቆዩ ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች አሉ፡፡ ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴዎች የሚባሉት ቤተሰባዊ እርቅ፣ የዘመድ ዳኝነት፣ ሽምግልና እና አፈርሳታ ናቸው፡፡

በአንድ ቤተሰብ አባላት መካከል የሚፈጠር ግጭት በአብዛኛው በቤተሰብ አማካኝነት መፍትሄ ሊያገኝ ይችላል፡፡ በልጆች፣ በልጆችና በወላጆች፣በባልና በሚስት፣ በጎረቤት መካከል አለመግባባቶች ሲከሰቱ ቤተሰባዊ እርቅ ይካሄዳል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የአስታራቂነትና የአስማሚነት ሚና የሚኖራቸው እናት፣አባት፣ ወይም በዕድሜ ከፍ ያሉ ልጆች ናቸው፡፡ ግጭቱ በባልና በሚስት መካከል ሲሆን ደግሞ በቅርብ የሚኖሩ የስጋ ዘመዶች ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ ጎረቤቶቹም የሽምግልና ስራ ይሰራሉ፡፡ በዘመድና በጎረቤት ሊፈታ ካልቻለ የዘመድ ዳኛ ወይም ሽማግሌዎች እንዲያዩት ይደረጋል፡፡

ግጭቶች በዘመድ ዳኛዎች አማካኝነት ይረግባሉ፤ መፍትሄም ያገኛሉ፡፡ የዘመድ ዳኞች ለሁሉም ወገኖች የስጋ ዝምድና ያላቸው እድሜ ጠገብ አስታራቂ ናቸው፡፡ የዘመድ ዳኛ በጠበኞቹ ስምምነት ሊመረጡ ይችላሉ፡፡ ከዚያም የሁለቱን ጠበኞች ቃል ተራ በተራ ያዳምጣሉ፡፡ ማብራሪያና ማስረጃም ይጠይቃሉ፡፡ ጉዳዩን በአግባቡ ከመረመሩ በኋላ ውሳኔ ይሰጣሉ፤ ለጉዳዩ ክብደትና እንደ ቅራኔው ክረት የዘመድ ዳኞች ሌሎች ዘመዶችን በመጨመር አብረው እንዲሸመግሉ ያደርጋሉ፡፡ ከመካከላቸውም አንድ ሰው መርጠው ጉዳዩን እንዲያስተናብር ያደርጋሉ፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ? የሽምግልና እና የአፈርሳታ የግጭት አፈታት እንዴት የሚከወን ይመስላችኋል?

ሽምግልና ሌላው የግጭት ማስወገጃ ዘዴ ነው፡፡ ሽምግልና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምትና ተቀባይነት ይሰጠዋል፡፡ የሽማግሌዎች አባላት በስነ-ምግባራቸውና በሚዛናዊነታቸው በአካባቢው ሰው ዘንድ አክብሮት ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ፡፡ ሽምግልና ብዙ ጊዜ በዕድሜ የገፉ ወይም በመካከለኛ ዕድሜ የሚገኙ ሰዎች ይወከሉበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከዕድሜ ይልቅ ማህበራዊ ተቀባይነትን፣ችሎታና ተደማጭነትን ተመራጭ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ሽምግልና ግጭቱ ከሚመለከታቸው ወገኖች ገለልተኛነትን ስለሚጠይቅ ከዘመድ ዳኛ ይለያል፡፡ አንድን ግጭት ለመዳኘት ለሽምግልና የሚላኩ ሰዎች እንደጉዳዩ ክብደትና አስቸጋሪነት ሶስትና ከዚያ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሽምግልና ሂደት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጠበኞች በአንዳቸው አሳሳቢነት ሊጀመር ይችላል፤ ወይም ከጉዳዩ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት በሌላቸው ገለልተኛ ሰዎች በሚቀርብ ጥያቄም ሊጀመር ይችላል፡፡ ሽምግልና አጥፊዎችን ይቀጣል፣ተበዳዮች እንዲካሱ ያደርጋል፤ እርቅንና ሰላምን ያመጣል፡፡

ሌላው ባህላዊ የግጭት ማስወገጃ ዘዴ አፈርሳታ ነው፡፡ አፈርሳታ ወይም አውጫጪኝ ማህበረሰብ በነቂስ ወጥቶ ወንጀለኛን የሚያውጣጣበት ሂደት ነው፡፡ አንድ ወንጀል ሲፈፀም የአካባቢው ነዋሪዎች ወንጀሉን አለመስማታቸው ወይም በሌላ ሰው ሲፈፀም አለማየታቸውን በመሀላ ያረጋግጣሉ፡፡ ዘመናዊ የወንጀል ምርመራ ባልነበረበት ወቅት ወንጀል ሲፈፀም አፈርሳታ የሚመሩ ሰዎች የአካባቢውን ኗሪዎች ይሰበስባሉ፡፡ ከተሰበሰበው ህዝብ ፈንጠር ብለውም ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያም የአካባቢው ነዋሪዎች በተናጠል እየተነሱ ወንጀል የፈፀመውን አካል በሚስጢር ይጠቁማሉ፡፡ አፈርሳታውን የሚመሩት ሰዎችም የሚሰጣቸውን መረጃና ጥቆማ ትክክለኛነት በመስቀልኛ ጥያቄዎች ያረጋግጣሉ፡፡ በመጨረሻም የጠቋሚዎችን ማንነት ሳይገልፁ ‹‹ ወንጀለኞችን

ወፍ ነገረችን፤ ወንጀሉን የፈፀሙት እነገሌ ናቸው›› በማለት በህዝብ ፊት ያጋልጣሉ።ወንጀለኞቹ ይመከራሉ፤ይቀጣሉ።

በአጠቃላይ ቤተሰባዊ እርቅ፣ የዘመድ ዳኝነት፣ሽምግልና እና አፈርሳታ ሰዎች ግጭቶችን የሚፈቱባቸው ዘዴዎች ናቸው።ዘዴዎቹም ለረጅም ዘመናት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ብዙዎቹም አሁን እያገለገሉ ይገኛሉ። የተጣሉትን ለማስታረቅ፣የተበደሉትን እንዲካሱ ለማድረግ፣ በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምና ፍቅር ለማስፈን ዘዴዎቹ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው። ስለሆነም በሳይንሳዊ መንገድ እየታገዙ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

አ.በ.ከ.መ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። 2001 ዓ.ም የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት ገፅ ከ80-82 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

- የማዳመጥ ተግባር ሲጠናቀቅ ለጻፉት አዳዲስ ቃላት ከራሳቸው መልስ እንዲሰጡ ያድርጉና መመለስ ያልቻሉትን እርስዎ ያስረዷቸው።
- በመቀጠል በመልመጃ ሁለት ስር የቀረበቡትን ጥያቄዎች በቃላቸው መልስ እንዲሰጡ በማድረግ በሰጡት መልስ ላይ ተጨማሪ ሀሳብ የሚያስፈልገው ጥያቄ ላይ እርስዎ ማብራሪያ ይስጡበት።
- ከምንባቡ ለወጡ ቃት በምንባቡ መሰረት ባላቸው ፍቺ በጽሁፍ እንዲሰጡ ይግለጹላቸው።
- የሰጡትን ፍቺ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መመለስ መቻላቸውን ያረጋግጡ። መመለስ ያልቻሉት ጥያቄ ካለ መልሱን ያስረዷቸው።
- በሚማሩበት ትምህርት ቤት የሚያጋጥሙ ችግሮችን እንዴት እንደሚፈቱ የስነ ዜጋና ስነምግባር ክበብ ተጠሪዎችን አነጋግረው ማስታወሻ በመጻፍ በክፍል እንዲያቀርቡ ይግለጹላቸው።
- ጽፈው ያመጡትን የችግር አፈታት ሂደት በክፍል እንዲያነቡ ያድርጉን ለሙከራቸው የማበረታቻ ቃል በመተቀም ያበረታቷቸው።

❖ በመጨረሻም ከዚህ ስር ተዘበራርቀው የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት አስተካክለው ዓረፍተ ነገር እንዲፅፉ ያንብቡላቸውና በትክክል መፃፍ አለመፃፋቸውን ይከታተሏቸው፡፡ ከዚያም እርስዎ ትክክለኛውን መልስ ይንገሯቸው፡፡

ሀ. ስርዓት መዳበር አለበት የዳኝነት በሀገራችን፡፡

ለ. በአግባቡ ነው የኮሮና እየተሰጠ ክትባት፡፡

ሐ. ውጤታማ ያጠና ተማሪ በአግባቡ ይሆናል፡፡

መ. ክህሎት ስልጠና ተሰጣቸው ለወጣቶች የህይወት፡፡

ሠ. ልዩ ድጋፍ ያስፈልጋል ለአካል ጉዳተኞች መስጠት፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ ሶስት

ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቺ ፃፉ፡፡

ሀ. ማስተባበር

ለ. አለመስማማት( ግጭት ውስጥ መግባት)

ሐ. ስምምነት

መ. ግጭቱ ይቀንሳል

ሠ. ውጥረት ( መባባስ)

ረ. ፍትሃዊነት

ሰ. ተሰሚነት

ሸ. ራቅ ብለው፣ነጠል ብለው

ቀ. ባህላዊ የወንጀለኛ መፈለጊያ

## ክፍል ሁለት ንባብ

- ያለፈውን ክፍለ ጊዜ ትምህርት በጥያቄና መልስ ያስታዉሷቸው፡፡
- የዕለቱን ትምህርት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው፡፡
- ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በማሰራት በቤተሰብቸው በየትኛው አጋጣሚ የድግስ መርሀ ግብር እንደሚዘጋጅ ይጠይቋቸው፡፡
- በቤተሰባቸው ወይም በአካባቢያቸው በድግስ ሰበብ ያጋጠመ ችግር ካለና ችግሩን ለማቃለል ምን ተግባር እንደተከናወነና በችግሩ ምክንያት የተከሰተውን ጉዳት ወይም ኪሳራ ምን እንደነበረ ይጠይቋቸው፡፡
- ተማሪዎቹ ካቀረቡት አጋጣሚ ምን ትምህርት እንዳገኙ እንዲናገሩ በማድረግ በማንኛውም የህይወት አጋጣሚ ልምድ ወይም ዕውቀት ማግኘት እንደሚቻል ያስገንዝቧቸው፡፡
- ስለድግስ ከማሰባቸው በፊት ምን ምን ጉዳይ ታሳቢ ማድረግ እንደሚገባ እንዲናገሩ ካደረጉ በኋላ በሶስቱም ጥያቄዎች የበለጠ ከምንባቡ ምልስ ሊያገኙ እንደሚችሉ በመጠቆም ንባቡን በለሆሳስ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- ንባባቸውን ሲያጠናቅቁ በድህረ ንባብ መልመጃ ሁለት ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል ያሰሯቸው፡፡
- በመልመጃ ሶስት ለቀረቡት ቃላት በ‹‹ ሀ›› ስር ላሉት በ‹‹ ለ ›› ከተዘረዘሩት በፍቺ የሚመሳሰሉትን እንዲያዛምዱ ይግለፁላቸው፡፡
- በመልመጃ አራት ስር የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል መልስ የሚሆነውን በመምረጥ እንዲመልሱ ያስረዷቸው፡፡
- ለጥያቄዎቹ የሰጡትን ምላሽ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ በዚህም በትክክል የመለሱትንና መመለስ ያልቻሉትን ይለዩ፡፡

- ❖ ለመለሱት ያበረታቷቸውና መመለስ ላልቻሉት ጥያቄ ምንባቡን መለስ ብለው እንዲቃኙ ያድርጉና ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ሙከራ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡፡ ካልሆ ግን እርስዎ ትክክለኛውን መልስ ያስረዷቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም ከላይ ከነበቡት ምንባብ ጋር ተያያዥነት ያለው ጽሑፍ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ የጻፉትን በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ያድርጉና ሙከራቸውን በማበረታታት ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ መሰጠት ያለበትን አስተያየት ይስጧቸው፡፡

**በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ**

**መልመጃ ሶስት**

በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት በፍቺ የሚስማሙትን ከ‹‹ለ›› ስር በመምረጥ አዛምዱ፡፡

1. መ
2. ረ
3. ለ
4. ሠ
5. ሀ
6. ሐ

**መልመጃ አራት**

በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ሐ
2. ሀ
3. መ
4. መ
5. ሐ
6. መ
7. ሀ
8. ሐ

ክፍል ሶስት ቃላት

የቃላት መጥበቅና መላላት

- በቃል ትምህርት ስር ተማሪዎቹ ለፈሊጣዊ አነጋገር ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ፣ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉና ለቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ይጠበቃል፡፡
- ፈሊጣዊ አነጋገር አንዱ ንግግርን ተደማጪነት እንዲኖረው ከሚያደርጉ ስልቶች አንዱ መሆኑን ይግለጹላቸው፡፡
- ፈሊጣዊ አነጋገር የተለያየ ፍቺ ካላቸው ሁለት ቃላት የሚፈጠር ሲሆን ቃላቱ በፊት ከነበራቸው ፍቺ ውጪ ሌላ ፍቺ እንዲሰጡ የሚደረግበት የአነጋገር ስልት መሆኑን ያስረዷቸው፡፡

  ምሳሌ፡- ‹‹ ቅቤ ጠባሽ ››የሚለውን የሁለት ቃላት ቅንጅት ብንመለከት ስለ ቅቤ መጥበስ የሚናገር ሳይሆን እወደድ ባይነት ባህሪን የሚገልጽ ነው፡፡
- በዚህ መሰረት ስለ ፈሊጣዊ ንግግር ያስረዷቸው፡፡
- ፈሊጣዊ አነጋገር ሁል ጊዜ ጥምር ቃል ሲሆን እንደማይችልም አያይዘው ይግለጹላቸው፡፡
- አንድ ቃል ፈሊጥ ሊሆን እንደሚችል ቀጥሎ ባለው ምሳሌ መሰረት ይግለጹላቸው፡፡ ምሳሌ፡- ለዋሳ የሚለው ቃል ፈሊጥ ሲሆን አቅመ ቢስ የሚል ፍቺ ይኖረዋል፡፡
- በመልመጃ አንድ ስር ባሉት ፈሊጣዊ አነጋገር ቃላት ፍቺ እንዲሰጡ ይግለጹላቸው፡፡
- አንድ ቃል ሲጠብቅ ወይም ሲላላ የተለያየ ፍቺ እንደሚሰጥ በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡

  ምሳሌ፡- ሳታልሙ የሚለው ቃል ሲጠብቅ ኢላማ ሳታስገቡ

  ሲላላ ሳታደቁ

- ❖ በመልመጃ ሁለት ስር ያሉትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ ሊኖራቸው የሚችለውን ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም በመልመጃ ሶስት ያሉትን ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ሰርተው እንዲያሳዩ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻም የሰሩትን የተማሪዎቹን ደብተር በማረም በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ❖ መመለስ ያልቻሉትን ማስተካከያ መልስ ይስጧቸውና እርማት እንዲወስዱ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች በምሳሌው መሰረት ፍቻቸውን በደብተራችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ሚስጥሩን ገልጦ አወያየ

ለ. ተረጋጋ

ሐ.ተቆጣ

መ. መሰከረ

ሠ.ሰማኝ፣ አደመጠኝ

ረ.ወላዋይ፣ በውሳኔው የማይፀና

**መልመጃ ሁለት**

**የሚከተሉትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍቺ በአረፍተ ነገር ውስጥ አሳዩ።**

ሀ. ወተት ሲጠብቅ መንከራተት

ሲላላ ከእንስሳ የሚገኝ የሚጠጣ

ለ. መዳር ሲጠብቅ ማግባት

ሲላላ ማጋባት

ሐ. መማር ሲጠብቅ ማወቅ፣ ዕውቀት ማግኘት

ሲላላ ይቅርታ ማድረግ

መ. ለጋ ሲጠብቅ መታ

ሲላላ ያልደረሰ

ሠ. ሳለ ሲጠብቅ እያለ

ሲላላ ስዕል መሳል፣ለጉንፋን መሳል

ረ. አያት ሲጠብቅ ተመለከታት

ሲላላ የአባት ወይም የእናት አባት እና እናት

## ክፍል አራት ጽሕፈት

### የሥርዐተ ነጥብ ምንነትና አይነቶች

- ❖ መምህር በጽሕፈት ስር የቀረቡትን ተግባርት ከማከናወንዎ በፊት በመምህሩ መምሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረበውን የስርዓተ ነጥብ ማስታወሻ በደብተራቸው ያጽፏቸው።
- ❖ ጽፈው ሲጨርሱ እያንዳንዱን ስርዓተ ነጥብ በምሳሌ እያስደገፉ በቂ ማብራሪያ ይስጧቸው።

  ማስታወሻ

### የስርዓተ ነጥብ ምንነትና አይነቶች

### የስርዓተ ነጥብ ምንነት

ስርዓተ ነጥብ ሀሳብን በፅሁፍ ለመግለፅ ያለው ድርሻ ከፍ ያለ ነው። በፅሁፍ ውስጥ መልዕክቱን በትክክል ለመረዳት እና የጽሁፍን አነባበብ ለመጠቆም ያገለግላል።

### የስርዓተ ነጥብ አይነቶች

በአማርኛ ቋንቋ በርካታ የስርዓተ ነጥብ አይነቶች ቢኖሩም የተወሰኑትን

እንደሚከተለው እንመልከት።

1. ነጠላ ሰረዝ(፣)፡- ነጠላ ሰረዝ ከሌሎቹ የስርዓተ ነጥብ አንፃር ሲተሳይ በርካታ አገልግሎት አለው።

ሀ. በዓረፍተ ነገር ውስጥተመሳሳ ሙያ የላቸው ድርድር ቃላት

ለያይቶ ለማስቀመጥ ያገለግላል።

- ምሳሌ፡-በገበያ ውስጥ ሙዝ፣ብርቱካን፣ፓፓዬ፣መንደሪንና አናናስ ይሸጣሉ።

ለ. በአረፍተ ነገር ውስጥ ተመሳሳይ ሙያ ወይም አቻዊነት

የሚታይባቸውን ሀረጋት ለያይቶ ለማስቀመጥ ያገለግላል፡፡

- ምሳሌ፡-አሰፋ አሮጌ ሱሪውን ታጥቆ፣በጥቁር ቀለም የተነከረ ነጠላ አጣፍቶ፣የጠፍር ጫማ ተጫምቶ፣የሰሌን ኮፍያ አድርጎ፣ሚዶውን ከፀጉሩ ላይ ሰክቶና መፋቂያውን በጥርሱ ነከስ አድርጎ ይጓዝ ነበር፡፡

ሐ. በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የንባብ ቆምታ መኖሩን

ለመጠቆም ይረዳል፡፡

- ምሳሌ፡- ቋንቋ፣የአንድ ማህበረሰብ የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡
- ባህል፣በአጭሩና በቀላሉ ሊገለፅ የሚችል ፅንስ ሀሳብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

2. ድርብ ሰረዝ(፤)፡- ድርብ ሰረዝ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑና እራሳቸውን ችለው ሊቆሙ የሚችሉ ዓረፍተ ነገሮችን አጣምሮ ለማቅረብ የሚያገለግል ስርአተ ነጥብ ነው፡፡
   - ምሳሌ፡- በርቀት እንደተቀመጠ አያት፤ እሷም አይታው ነበር፡፡
   - ቤቱ ቆርቆሮ ለብሷል፤ግርግዳው ተለስኗል፤ወለሉ ተነጥፏል፤ የቀረው ነገር አለ ማላት አይቻልም፡፡
3. ትምህርተአንክሮ (!)፡-ትምህርተ አንክሮ ብዙ ጊዜ የአግራሞት፣የቁጣ፣የትዕዛዝ ግጼታ፣የደስታ ቃና ባዘሉ ስሜቶች ሀሳብን ለመግለፅ ሲፈለግ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡፡
   - ምሳሌ፡-ደግሞ ተነሳባቸው!
   - ድህነት ቀንደኛ ጠላታችንነው!
   - ወይ ጉድ! ምን አይነት ጣጣ ነው!

4. ትምህርተ ስላቅ( ¡ ):- አንድን ሀሳብ በቀልድ፣በፌዝ፣በተሳልቆ ወይም በምፀት መግለፅ ሲያስፈልግ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
   - ምሳሌ፡- አይ ቁመና እንዲህም ቁመና የለ¡
   - የፅጉሯን ነገር አታንሳብኝ¡
5. ድርብ ትምህርተ ጥቅስ (‹‹ ››)፡- ይህ ስርዓተ ነጥብ በልቦለዳዊ ፅሁፎች ላይ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ እንግዳ ቃላትን ለመጠቆም፣ የሌሎች ሰዎችን መረጃ በጥቅስነት ሲወሰድ፣ የገፀባህሪትን ንግግር ለማስቀመጥ ያገለግላል፡፡

   ሀ. አዳዲስ ቃላትንና የተውሶ ቃላትን ለማመልከት
   - ምሳሌ፡- በሀመር ብሄረሰብ ዘንድ‹‹ኢቫንጋዲ›› የተሰኘ የወጣቶች የመዝናኛ ምሽት ዘወትር ይሄዳል፡፡

   ለ. የገፀባህሪያትን ንግግር ለማሳየት
   - ምሳሌ፡-‹‹ከቤታችን ያለው ካሴት ይሄ ብቻ ነው››
   - ‹‹ያልከውን አደረኩልህ እኮ››
   - ‹‹ሌላ ቀይርልኝ ነው እምልህ››

   ሐ. የሌላ ሰው ሀሳብን ወስደን ስንጠቀም ሀሳቡ የሌላ ሰው መሆኑን ለማሳየት፣

   ምሳሌ፡- ‹‹ከመጠምጠም መማር ይቅደም›› አሉ ምሁራን አበው፡፡
6. ነጠላ ትምህርተ ጥቅስ(‹ ›)፡- አንድ ሰው የተናገረውን ሀሳብ ሶስተኛ ወገን ሲናገረው በነጠላ ትምህረተ ጥቅስ ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡
   - ምሳሌ፡-የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር‹‹ወጣቶች!ትምህርት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው፤ሌኒን‹መማር መማር አሁንም መማር› እንዳለው ሳትዘናጉ በርትታችሁ መማር ይኖርባችኋል›› በማለት ለተማሪዎች አስገነዘቡ፡፡

- ማስታወሻውን በደንብ ከተረዱት በኋላ በተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን አንቀጽ እንዲያነቡ፣ ሲያነቡ የስርዓተ ነጥቦችን አነባበብ ጠብቀው በለሆሳስ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- አንድ ጊዜ አንብበው ሲጨርሱ በድጋሚ በተራ በተራ ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ማንበብ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ስርዓተ ነጥቡን ጠብቀው ማንበብ ካልቻሉ እርስዎ አንድ ጊዜ የአነባበብ ስልቱን ጠብቀው ያንብቡላቸው፡፡
- በድጋሚ የእርስዎን አነባበብ ስልት ተከትለው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- በዚህ መልኩ ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅመው ጽሁፍን እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው ከተለማመዱ በኋላ በመልመጃ ሁለት ስር ላለው አንቀጽ በባዶ ቦታው ውስጥ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ እንዲያስገቡ ይግለጹላቸው፡፡
- በመልመጃ ሶስት ስር የቀረበውን የአዛምድ ጥያቄ ስርዓተ ነጥቦችን ከአገልግሎታቸው ጋር እንዲያዛምዱ ያስረዷቸው፡፡
- ከዚያም የሰሩትን እንዲያቀርቡ ያድርጉና በትክክል መስራት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ማስተካከያ ለሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ይንገሯቸውና እርማት እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በመቀጠል የቀረበላቸውን ጽሁፍ ወደሰንጠረዥ እንዲቀይሩ ያስረዷቸው፡፡ ይህን መልመጃ ሲተገብሩ በዓመተ ምህረት እና በቁጥር የቀረቡትን እንዴት መፃፍ እንዳለባቸው ምሳሌ ይስጧቸው፡፡
- የጻፉትን የእያንዳንዱን ተማሪ መልመጃ ተመልክተው በትክክል መስራታቸውን ይፈትሹ፡፡
- በመጨረሻም በመምህሩ መምሪያ ላይ ያለውን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ለይ ይጻፉላቸውና እነሱ ከሰሩት ጋር እንዲያስተያዩ ያድርጉ፡፡

- ሲያስተያዩ የሰሩትን ስህተት ለይተው እንዲያወጡ ይግለጹላቸው። ስህተታቸውን ከለዩ በኂላ ማስተካከያ እንዲወስዱ ያበረታቷቸው።
- ስለ ደብዳቤ የቀረበውን ማስታወሻ በደብተራቸው ያጽፏቸውና በጥያቄና መልስ ያሰረዷቸው።

**የደብዳቤ አይነቶች**

ደብዳቤ እንደይዘቱና አላማው በርካታ ቢሆኑም የመስሪያ ቤትና የግለሰብ ደብዳቤ ተብሎ ሊከፈል ይችላል።። የግለሰብ ደብዳቤ የሚባለው ግለሰብ ለግለሰብ፣ወዳጅ ለወዳጁ፣ ጓደኛ ለጓደኛው ናፍቆታቸውን ለመግለፅ መረጃ ለመለዋወጥና ጥሪ ለማድረግ ሲባል የሚፃፍ ነው ። የመስሪያ ቤት ደብዳቤ የምንለው ደግሞ በስራ ዓለም ውስጥ ስራ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ለመፈፀምና ለማስፈፅም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና መሰሪያ ቤቶችበተጨማሪ ድርጅቶች እርእስ በእርስ ሀሳብ፣መመሪያና ትዕዛዝ የሚለዋወጡበት ነው። በዚህ የደብዳቤ አይነት መስሪያ ቤት ከመስሪያ ቤት፣ድርጅት ለድርጅት፣መስሪያ ቤት ለግለሰብ፣ እንዲሁም ግለሰብ ለመስሪያ ቤት ከላይ ወደታች ወይም ከታች ወደላይ ሊፃፍ ይችላል።

**የመስሪያ ቤት ደብዳቤና የግለሰብ ደብዳቤ አንድነትና ልዩነት**

| የመስሪያ ቤት ደብዳቤ | የግለሰብ(የወዳጅዘመድ ደብዳቤ) |
| --- | --- |
| በመደበኛ ቋንቋ አጠቃቀም መጻፍ አለበት | እንደግለሰቦቹ ቀረቤታ በኢመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ሊጻፍ ይችላል፡፡ |
| በፊደላት፤በቃላት፤በሀረጋት ግድፈት ምክንያት ችግር ወይም አለመግባባት ስለሚከሰት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል | በፊደላትና በቃላት አጠቃቀም ችግር ምክንያት የከፋ ችግር አይከሰትም፡፡ |
| ቁጥር፤ቀን፤ማህተም፤ የባለሥልጣኑ ፊርማና የሥራ ሀላፊነት መጻፍ አለበት | እንደአስፈላጊነቱ ቀንና ፊርማ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን ቁጥር፤ማህተምና የስራ ሀላፊነት ላያስፈልግ ይችላል፡፡ |
| የላኪ አድራሻ፤የተቀባይ አድራሻ፤መግቢያ ሀተታና መደምደሚያ አይቀሬ ናቸዉ | የላኪ፤የተቀባይ አድራሻ፤መግቢያ፤ሀተታና መደምደሚያ እንደአስፈላጊነቱ ሊገባ ይችላል |
| እንደሁኔታዉ ደብዳቤዉ በፖስታ ቤት አሊያም በሰዉ ሊላክ ይችላል፡፡ | በግለሰብ ወይም በፖስታ ሊላክ ይችላል |
| ህጋዊነቱን ለማረጋገጥ ቴምብር፤የራስጌ ማህተም፤ግልባጭ ይኖረዋል፡፡ | ግልባጭ፤ቴምብርም ሆነ ማህተም አያስፈልግም፤ነገር ግን በፖስታ ቤት በኩል የሚላክ ከሆነ ቴምብር ያስፈልጋል |

- ስለደብዳቤ የቀረበውን ማስታወሻ መረዳት መቻላቸውን በቃል ጥያቄ በመጠየቅ ያረጋግጡ፡፡
- በተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የማመልከቻ ደብዳቤ ምሳሌ በደንብ አንብበው እንዲረዱት ይግለጹላቸው፡፡

- በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ስለሚያጋጥሙ ችግሮችና ችግሩን ለማቃለል ወይም ለማስቀረት የተደረገውን ጥረት ከስነ ዜጋና ስነ ምግባር ክበብ ተጠሪዎች ጠይቀው ማስታወሻ በመጻፍ በክፍል ውስጥ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡ያለባቸውን አስተያየት ይስጧቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ ሶስት

ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ በትክልል በማንበብ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በባዶ ቦታው ውስጥ አስገብታችሁ ፃፉ፡፡

1. አራት ነጥብ
2. ነጠላ ሰርዝ
3. ነጠላ ሰረዝ
4. ነጠላ ሰረዝ
5. አራት ነጥብ
6. አራት ነትብ
7. ቅንፍ
8. አራት ነጥብ
9. አራት ነጥብ
10. ትዕምርተ ጥቅስ

መልመጃ አራት

በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘተሩት የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ጋር የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

1. ሐ
2. ሠ
3. ለ
4. ረ
5. መ
6. ሀ

መልመጃ አምስት

ከዚህ በታች ያለውን ምንባብ በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ወደ ሰንጠረዥ ቀይራችሁ ፃፉ፡፡

| የደን ስርጭት በኢትዮጵያ በስኩየር ኪሎ ሜትር 1973 -1990ዓ.ም | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የደን አይነቶች | ከ1973 — 1976 | | 1986 — 1990 | |
| | ስፋት ስ.ኪ.ሜ | የደን ስፋት በመቶኛ | ስፋት ስ.ኪ.ሜ. | የደን ሽፋን በመቶኛ |
| ጥቅጥቅ ደን | 30243 | 2.64 | 2346 | 0.2 |
| በመጠኑ የተመናመነ ደን | 14158 | 1.24 | 7466 | 0.65 |
| በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነ ደን | 10009 | 0.87 | 35243 | 3.08 |
| ጠቅላላ | 54410 | 4.75 | 45055 | 3.93 |

ክፍል አምስት ሰዋስው

የሃላፊ ጊዜ

- ❖ ከዚህ በፊት ስለሀላፊ ጊዜ የተማሩትን በጥያቄና መልስ ክልሳ ያድርጉላቸው፡፡ በመልመጃ አንድ ላይ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በሀላፊ ጊዜ የተጻፉትን ለይተው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ❖ በመቀጠልም በመልመጃ ሁለት ስር በቀረቡት የሀላፊ ጊዜ ግሶች ዓረፍተ ነገር እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ❖ በመጨረሻ የሰሩትን እንዲያቀርቡ በማድረግ በትክክል የሀላፊ ጊዜ ድርጊትን ከአሁን እና ከወደፊት ጊዜ መለየት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ❖ ማስተካከያ መስጠት የሚያስፈልገው ካለ ያስረዷቸውና አስተካክለው እነዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

መልመጃ አንድ

ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በሃላፊ ጊዜ የተመሰረቱትን ለይተችሁ አውጡ፡፡

ሀ. ልጁ የተዋሰውን መጽሐፍ ባለፈው ሳምንት መለሰ፡፡

መ. ባለፈው ዓመት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ተቆፍሮ ነበር፡፡

ሠ. እንግዳው ትናንት ማታ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

ሰ. ባለፈው ዓመት ውድድሩን ያሸነፈው የኔ ፈረስ ነበር፡፡

# ምዕራፍ አስር

## ሴቶችን ማብቃት

የክፍል ጊዜ ርዝማኔ፡-18

❖ የምዕራፉ አጠቃላይ አላማዎች

- ✓ የተሰማቸውን ምክንያታዊ ሆነው ይገልፃሉ
- ✓ ምንባቦችን አስተካክለው ያነባሉ
- ✓ የሰው ህይወት ታሪክ ይጽፋሉ
- ✓ ስርዓተ ነጥቦች ያላቸውን አገልግሎት ተረድተው ያነባሉ
- ✓ ርዕቱና ኢርቱዕ ዓረፍተ ነገሮችን ይጠቀማሉ

❖ አጠቃላይ ይዘቶች

- ➢ ማዳመጥና ፅብረቃ
- ➢ የህይወት ታሪክ ማንበብና መፃፍ
- ➢ ቅጥያዎችን ማጣመር
- ➢ ርቱዕና ኢርቱዕ

## ❖ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ‹‹ህልመኛዋ ወጣት››

**የትምህርቱ አቀራረብ**

- እባክዎ መምህር በዕለቱ የሚደመጠውን ምንባብ ርዕስ በጠመኔ ሰሌዳዉ ላይ ይጻፉላቸው፡፡ ከዚያም በቅድመ ማዳመጥ ስር ያሉትን ጥያቄዎች በቃላቸው እንዲሰሩ ይግለጹላቸው፡፡
- በመጀመሪያ እጃቸውን እያወጡ የሚመልሱ ካሉ እድሉን ይስጧቸውና እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ በተጨማሪም እጃቸውን ያላወጡ ተማሪዎችን በስም እየጠሩ ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ጥያቄ ‹‹ሀ››ን ሲሰሩ ስዕሉ ስለምን እንደሚገልጽ እንዲገምቱ ይጠይቋቸውና ለሚሰጡት የተለያየ መልስ ምክንያት እንዲሰጡ ይጠይቋቸው፡፡
- ወደጥያቄ ‹‹ ለ ›› ሲሄዱ ርዕሱንና ምስሉን እያነፃፀሩ ያላቸውን ግንኙነት እንዲገምቱና የተረዱትን እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡
- ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያለው ታሪክ በአካባቢያቸው ወይም በቤተሰባቸው የሚያውቋቸው ስኬታማ ሴቶች ካሉ የስኬታማነታቸው ምስጢር ምን እንደሆነ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያድርጉና ለሰጡት ምላሽ አመስግነው ወደምንባቡ ያምሩ፡፡
- በማዳመጥ ጊዜ የሚያዳምጡትን ታሪክ የድርጊት ቅደም ተከተል እየለዩ በማዳመጥ በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ባዶ ቦታ እንዲሞሉ ያስረዷቸው፡፡
- ለማዳመጥ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡና ለማድመጥ የቀረበውን ምንባብ ያንብቡላቸው፡፡

- መሀል ላይ ንባብዎትን ገታ ያድርጉና የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎችን እስካሁን ካዳመጡት ታሪክ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡
- በመቀጠል ባለታሪኳ በመጨረሻ ምን ደረጃ ላይ እንደምትደርስ እንዲገምቱ ያበረታቷቸው፡፡

ወርቅነሽ ትባላለች፤ ተወልዳ ያደገችው በሀገራችን ካሉት የገጠር መንደሮች መካከል በአንዱ ውስጥ ነው፡፡ ባደገችበት ማህበርሰብ ዘንድ ሴትን ልጅ ማስተማር የማይታሰብ ስለነበር እሷም የዚሁ እጣ ፈንታ ተቋዳሽ ነበረች፡፡ ሰባት ልጆችን ለወለዱት ቤተሰቦቿ ሶስተኛ ልጅ ስትሆን የቤቱን ስራ በመስራት የሴትነት ግዴታዋን ትወጣለች፡፡ሁለቱ ታላላቆቿ ወንዶች በመሆናቸው ሁሉንም የቤት ስራ ጠቅልላ ስለምተሰራ ከፍተኛ የስራ ጫና ነበረባት፡፡ ወንድሞቿ እህታቸውን የሚወዷት ቢሆኑም የቤቱን ስራ እንዳያግዟት ባህላቸው አይፈቅድላቸውም ነበር፡፡

ወርቅነሽ እንደወትሮዋ ቤተሰቦቿንም ሆነ እህት ወንድሞቿን ዘወትር ታደርገው እንደነበረው ከማገልገል ይልቅ ለብቻዋ ሆና ማሰብ ጀመረች፡፡ ሁኔታዋ ያላማራቸው ቤተሰቦቿ ምን እንደሆነች በተራ ጠየቋት፡፡ እሷ ግን ታስብ የነበረው ከወር በፊት የእናቷ ታናሽ እህት ዘመድ ጥየቃ መጥታ ስለመከረቻት ነገር ስለነበር ምን እያሏት እንደነበር እንኳ አላዳመጠቻቸውም ነበር፡፡ የት ሄድሽ ልጄ! ሲላት አባቷ እንደመባነን ብላ ወደ አክስቴ መሄድ እፈልጋለሁ፡፡ ዘመናዊ ትምህርት አስተምርሻለሁ ብላኛለች፤እናንተ የማትፈቅዱልኝ ከሆነ ግን ጠፍቼ መሄዴ አይቀርም አለቻቸው፡፡ ቤተሰቦቿም በሰሙት ነገር ቢደነግጡም ጥያቄዋን ግን ወደ ጎን ማላት አልፈለጉም፡፡ እናቷም ከእህቷ ጋር በስልክ ከተነጋገረች በኋላ ወደ አዲስ አበባ ከሚመጣ ሰው ጋር ላከቻት፡፡

ወርቅነሽ አዲስ አበባ ከአክስቷ ቤት እንደደረሰች ከተማውን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትመለከተው በቀላሉ የምትለምደው ስላልመሰላት ፍራት ፍራት ብሏት ነበር፡፡ አክስቷም ሁሉንም ነገር ስታሳያት ሰንብታ ትምህርት ቤት ሲከፈት አንደኛ ክፍል አስመዘገበቻት፡፡ ዕድሜዋ ተላልፏት ስለነበር በክፍል ካሉት ተማሪዎች ትልቋ እሷ ብቻ ነበረች፡፡ ትምህርት እንደተጀመረ አካባቢ አርፍዳ ወደ ክፍል ስትገባ የክፍሏ ተማሪዎች አስተማሪ እየመሰለቻቸው ከመቀመጫቸው ይነሱላት ነበር፡፡ እንደነሱ ተማሪ መሆኗን ሲያውቁ ይስቁባት ነበር፡፡ እሷ ግን በማን እንደሚስቁ ስለማትረዳቸው ዝም ትላቸዋለች፡፡

ወርቅነሽ የተለያዩ መሰናክሎች ቢያጋጥሟትም ሁሉንም ነግር እንዳመጣጣቸው ተቋቁማ በጥሩ ውጤት እየታጀበች አስረኛ ክፍል ደረሰች፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በምትከታተልበት ወቅት ሁሌም አንደኛ ስለምትወጣ ሁሉንም ሰው ታስደስት ነበር፡፡ በሚኒሚዲያ ክበብ አማካኝነት ድራማ፣ ጭውውት፣ ግጥምና መነባንብ በማቅረብ ምርጥ ብቃቷን ማስመስከር ችላለች፡፡ በተለይ ያደገችበትን ማህበረሰብ አለባበስና አነጋገር በመወከል ድራማ ስታቀርብ ሁሉም ተማሪዎች በአድናቆት ይከታተሏት ነበር፡፡ በዚህም በአስተማሪዎቿ ዘንድ የምትወደድ ልጅ ነበረች፡፡ በጥንካሪዋ፣በውጤቷና በስነምግባሯ ለሌሎች ሴት እህቶቿ እንደምሳሌ የምትጠቀስ ነበረች፡፡ ወደፊት ትምህርቷን ስትጨርስ ምን መሆን እንዳለባት የወሰነቻቸውም ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያላች ነበር፡፡ ያደገችበትም ማህበረሰብ እንዴት መርዳት እንደምትችል ዕቅድ አውጥታ ነበር፡፡

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ፅሁፍ ምን ተረዳችሁ?
2. ወርቅነሽ ወደፊት ትምህርቷን ስትጨርስ ምን የምትሆን ይመስላችኋል?

ወርቅነሽ የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናዋን ወስዳ በትምህርት ቤቱ ከሁሉም የተሻለ ውጤት አስመዘገበች፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ስለደረሳት በጣም ተደሰተች፡፡ ዩንቨርሲቲ እንደገባች የተመኘችውን የጋዘጠኝነት ትምህርት በማጥናቷ በራስ መተማመኗን ጨመረላት፡፡ ከሁለት ወር በኋላ በእሷ አስተባባሪነት በዩንቨርሲቲው ውስጥ ሳምንታዊ የስነ-ፅሁፍ ምሽት እንዲመሰረት አደረገች፡፡ በተቋቋመው ክብብም በርካታ ሴቶችና ወንዶች እውቀታቸውን ማዳበር ጀመሩ፡፡ የምታቀርባቸው ግጥሞች መነባንቦች፣ ወጎችና ስለሴቶች ብቃት ታቀርብ ስለነበር በርካታ ሴቶች የእሷን መንገድ መከተል መጀመራቸው የበለጠ እንድትሰራ ያደርጋት ነበር፡፡ ወርቅነሽ በግቢ ቆይታዋ በትምህርቷ ከሁሉም ተማሪዎች ጋር እየተወዳደረች በጥሩ ውጤት በዋንጫ ተመራቂ ሆነች፡፡ ያሳደገቻት አክስቷም ኮራችባት፡፡

በመጨረሻም ሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ስመጥር የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በአንደኛው ተወዳድራ አልፋ የጋዜጠኝነት ስራዋን ጀመረች፡፡ በአጭር ጊዜ በስራዋ እውቅናን እያገኘች መጣች፡፡ ያገኘችውን እውቅና በመጠቀም መንግስትንና ባለሀብቶችን አቀናጅታ ተወልዳ ባደገችብት አካባቢ ደረጃውን የጠበቀ አንድ ትምህርት ቤት ማስገንባት ቻለች፡፡ የእሷ እኩያዎች ያጡትን የትምህርት እድል ታናናሾቿ እንዲያገኙ ማድረግ ቻለች፡፡ ሌሎች ተጨማሪ ትምህርት ቤቶችን ለማስገንባት እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች፡፡

- የማዳመጥ ጊዜ ሲጠናቀቅ እያዳመጡ የሞሉትን ጥያቄ ምን ያህሉ ተማሪ አጠናቆ እንደሞላ፣ምንያህሉ ደግሞ በከፊል ወይም ደግሞ እንዳልሞላ እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

- እንደተማሪዎቹ ሁኔታ ምንባቡ በድጋሚ መነበብ እንዳለበትና እንደሌለበት እርስዎ ይወስኑ፡፡
- ማለትም አብላጫው ተማሪ ባዶ ቦታውን መሙላት ከቻለ በድጋሚ ሳያነቡ በባዶ ቦታው የሚገቡትን ቃላትና ሐረጋት ከመምህሩ መምሪያ መጽሐፍ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ያላሟሉት ተማሪዎች እየመረጡ እንዲያሟሉ፣ አሟልተው የጻፉት ደግሞ የሰሩትን እንደገና ተመልሰው እንዲያዩት በማድረግ ሁሉንም ተማሪዎች በሚያሳትፍ መልኩ ተግባሩን ያከናውኑ፡፡
- አብዛኛው ተማሪ ባዶ ቦታውን አሟልቶ ካልጻፈ ግን ምንባቡን በድገጋሜ ማንበቡ የተሻለ ሊሆን ይችላል፡፡
- በመልመጃ ሶስት ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች በቅድሚያ እንዲወያዩባቸው ጊዜ ይስጧቸው፡፡
- በመቀጠል የተወያዩበትን ሀሳብ እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡
- በመጨረሻም ከቀረበላቸው ምንባብ ምን ቁም ነገር እንዳገኙ ተወያይተው በክፍል ውስጥ በተራ በተራ ንግግር እንዲያደርጉ ያስረዷቸው፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ፡፡

መምህራችሁ‹‹ህልመኛዋ ወጣት›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ የድርጊት ቅደም ተከተሉን በጥሞና በማዳመጥ ባዶ ቦታውን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. የሴትነት ግዴታዋን

ለ. እንደወትሮዋ

ሐ. እንደመባነን

መ. ተላልፏት

ሠ. መሰናክል

ረ. አቀናጅታ

## ❖ክፍል ሁለት፡- ንባብ

- በክፍል ሁለት ንባብ ክሂልን ለማስተማር የቀረበውን ምንባብ ከማንበባቸው በፊት በርዕሱ ስር ያሉትን ፎቶግራፎች ተመልክተው በስዕሉ የቀረቡት ሴቶች በምን ተግባር እንደሚታወቁ ይጠይቋቸው፡፡
- የተማሪዎቹን ግምት መነሻ በማድረግ ሎሬት የትነበርሽ ንጉሴ የህግ ባለሙያ እና የአካል ጉዳተኛ መብቶች ተሟጋች እንደሆነች፣ እ.ኤ.አ. 2017የአካል ጉዳተኞች መብቶች እና ማካተቶችን በማስተዋወቅ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የአእምሮ ውቅርን መለወጥ በሚያበረታታ ስራዋ ‹‹ራይት ላይቭሊሁድ አዋርድን›› ሽልማት ያገኘች አይነስውር ጀግና ሴት መሆኗን፣
- ዶ/ር እሌኒ ገብረ መድህን በስራ ፈጣሪነትዋ ወይም ለስራ ፈጣሪዎች ዕድል በመስጠቷ፣አልያም ደግሞ የኢትዮጵያን የምርት ገበያ በማስጀመሯ፣ በተጨማሪም የእራሷን ጥቅም ትታ ሀገሬን አገለግላለሁ በሚል ከአሜሪካን ሀገር በመምጣት የኢትዮጵያን ህዝብ እያገለገለች ያለች ታላቅ ሴት መሆኗን፣
- ክብርት ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት ፕሬዝዳንት እና ለሀገራቸው ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ስራ የሰሩ እንደሆኑ፣
- ፓይለት አምሳለ ጓሉ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት አውሮፕላን አብራሪ መሆናቸውን ያብራሩላቸው፡፡
- በመቀጠልም በሀገራችን ስኬታማ የሆኑ ሴቶች ቁጥር አናሳ የሆነበትን ምክንያት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- በመልመጃ ሁለት ስር የቀረቡትን ቃላት አጣምረውና ነጥለው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡

- በመነጠልና በማጣመር አንብበው ሲያጠናቅቁ ምንባቡን ጥንድ ጥንድ ሆነው ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- ሲያነቡ ዋናና ዝርዝር ሀሳቡን እየለዩ እንዲያነቡ ያስረዷቸው፡፡
- የማንበብ ተግባሩን ሲያጠናቅቁ በተግባር ሶስት ስር የቀረበውን የእውነት ሐሰት ጥያቄ መልስ እንዲሰጡና ለመልሳቸው ምክንያት እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡
- በመልመጃ አራት ስር ለቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ያስረዷቸው፡፡
- የሰጡትን መልስ በተራ እየወጡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉ ያድርጉና እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያበረታተዋቻ፡፡
- በመጨረሻም ማስተካከያ መልስ የሚያስፈልገውጥያቄ ካለ እርስዎ ያስረዷቸውና የተሰጣቸውን እርማት እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

### መልመጃ አራት

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቻቸውን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. እንዲረጋገጥ

ለ. ሰነዶች

ሐ. ቁርኝት

መ. አስተዋጽዖ

ሠ. ምሳሌ

ረ. ማበልፀግ

ሰ. ተቋማት

# ❖ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል

- ከዚህ በፊት የቃላት ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍቺ መማራቸውን ያስታውሷቸው፡፡
- ምን ያህል እንደሚያስታውሱ በጥያቄ ይፈትሹና በተግባር አንድ ስር ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እንዲሰጡ ያስረዷቸው፡፡
- የሰጡትን ምላሽ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠት መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ማስተካከያ የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ መልስ ይንገሯቸውና ትክክለኛ መልስ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በመልመጃ ሁለት ጥምር ቃል ለመመስረት የቀረቡትን ተጠቅመው ጥምር ቃል እንዲመሰርቱ ከማድረግዎ በፊት ስለ ጥምር ቃል ምንነት ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡
- ጥምር ቃል የተለያየ ፍቺ ካላቸው ሁለት ቃላት የሚመሰረት ሲሆን ጥምር ቃሉ ከተመሰረተ በኋላ የሚኖረው ፍቺ ሁለቱ ቃላት ቀድሞ ከነበራቸው ፍቺ ውጪ እንደሆነ ያስረዷቸው፡፡
- ጥምር ቃል ቀደም ብሎ ከተማሩት ከፈሊጣዊ ንግግር ጋር ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ይንገሯቸው፡፡ ጥምር ቃል የሚኖረው ፍቺ ፊት ለፊት ሲሆን የፈሊጣዊ አነጋገር ቃል ፍቺ ግን ከፊት ለፊት ፍቺ ያለፈ እንደሚሆን፣
- ጥምር ቃል ሁል ጊዜ የሁለት ቃል ውጤት ሲሆን ፈሊጥ ግን ጥምር ቃል ብቻ እንዳልሆነ፣ በቃል ደረጃ ሊገኝ እንደሚችል ባለፈው ስለፈሊጣዊ አነጋገር የተማሩትን እንዲያስታውሱ ያድርጓቸው፡፡

- ስለጥምር ቃል ከተረዱ በኋላ በተግባር ሁለት በቀረበው ጥምር ቃል እንዲመሰርቱ፣ ለመሰረቱት ጥምር ቃል ፍቺ እንዲሰጡ ይግለጹላቸው፡፡
- የመሰረቱትን ጥምር ቃልና የሰጡትን ፍቺ እየወጡ በጠመኔ ሰሌዳዉ እንዲጽፉ ያድርጉና እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ ያግዟቸው፡፡
- በመጨረሻም ማስተካከያ የሚያስፈልገውን ይለዩና ትክክለኛ መልስ ይስጧቸውና እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡
- ለተሰመረባቸው ቃላት ትክክለኛ ፍቺ የያዘውን ፊደል እየመረጡ መልስ እንዲሰጡ ያስረዷቸው፡፡
- በመልመጃዎቹ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጡትን መልስ እንዲናገሩ በማድረግ በትክክል መልስ መስጠታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በትክክል ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ ትክክለኛውን መልስ ይጻፉላቸውና አስተካክለው እንደገና እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡
- በተግባር አራት ስር የቀረቡትን ቃላት ከዚህ በፊት በተማሩት መሰረት ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተው እንዲጽፉ ያስረዷቸው፡፡
- የሰሩትን በተራ በተራ እየወጡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲጽፉ በማድረግ እርስ በርስ እንዲተራረሙ ያግዟቸው፡፡
- በመጨረሻም በተማሪዎች ያልተመለሰ ጥያቄ ካለ እርስዎ ያስረዷቸውና እንዲያስተካክሉ ያበረታቷቸው፡፡

## በናሙናነት የተመረጡ ጥያቄዎች መልስ

## መልመጃ አንድ

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. ሚዛናዊ

ለ. ምናብ

ሐ. መቃረን

መ. ጉስቁልና

ሠ. ውርደት

ረ. አደባባይ

ሰ. ብዙ፣ በርካታ

## መልመጃ ሶስት

የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደድል ምረጡ፡፡

1. ሀ
2. ሐ
3. ሐ
4. መ
5. ሀ

5. ሀ.
6. መ

# ❖ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

## የህይወት ታሪክ

- በዚህ ትምህርት ክፍል ስር በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ በደብተራቸው እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡
- ጽፈው ሲያጠናቅቁ በጥያቄና መልስ ያስረዷቸው፡፡ ያልገባቸው ካለ እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፡፡ ላቀረቡት ጥያቄ በቂ ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡
- በተማሪዉ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የጳውሎስ ኞኞ የህይወት ታሪክ ሲያነቡ ደቂቃ ይያዙላቸው፣
- ሲያነቡ የስርዓተ ነጥቦችን አነባበብ ስልት ጠብቀው እንዲያነቡ ይግለጹላቸው፡፡
- አንብበው ሲያጠናቅቁ የቀረበውን ምንባብ በተያዘላቸው ደቂቃ አንብበው ማጠናቀቃቸውን ይፈትሹ፡፡
- በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ስርዓተ ነጥቦች ተከትለው በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ለመፈተሽ በድጋሜ በተራ በተራ ድምጻቸውን እያሰሙ እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡
- በዚህም ስርዓተ ነጥቦቹን በትክክል ማንበብ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- ተማሪዎቹ በትክክል ማንበብ ከቻሉ ጥሩ ካልሆነ ግን እርስዎ በአርአያነት ያንብቡላቸውና የእርስዎን ስልት ተከትለው ማንበብ እንዲለማመዱ ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል በቡድን ይመድቧቸውና በቡድናቸው ከላይ ያነበቡትን የህይወት ታሪክ አወንታዊና አሉታዊ ጎን ላይእንዲወያዩ ይግለጹላቸው፡፡

- ተወያይተው ያገኙትን አወንታዊና አሉታዊ ጎን እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፡፡
- ባቀረቡት ሀሳብ ላይ በመነሳት ተማሪዎቹ የጽሑፉን አወንታዊና አሉታዊ ጎን መለየት መቻላቸውን ይፈትሹ፡፡
- ላቀረቡት ሀሳብ ማበረታቻ ቃል በመጠቀም ያበረታቷቸውና ተጨማሪ ወይም መስተካከል ያለበት ሀሳብ ካለ በአስተያየት መልክ ያብራሩላቸው፡፡
- እስካሁን በተማሩት የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ መሰረት የግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በቢጋር መልክ እንዲያዘጋጁ ያስረዷቸው፡፡
- ያዘጋጁትን ቢጋር በክፍል ውስጥ አንዲያነቡ ያድርጉና ማስተካከል ያለባቸውን ነጥብ እንዲያስተካክሉ ያግዟቸው፡፡
- ባዘጋጁት ቢጋር አንድ ሰው የህይወት ታሪክ መጻፍ እንዲለማመዱ ይግለጹላቸው፡፡
- በመለማመጃነት የጻፉትን የህይወት ታሪክ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያድርጉና ለሙከራቸው ማበረታቻ ቃል በጠቀም ያበረታቷቸው፡፡
- በመቀጠል ማስተካከል ያለባቸውን አስተያየት ይስጧቸው፡፡
- በቀጣይ የሚውቁትን አንድ ሰው የህይወት ታሪክ ጽፈው እንዲመጡ ይግለጹላቸው፡፡
- የጻፉትን የህይወት ታሪክ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተማሪዎቹ የህይወት ታሪክ መጻፍ መቻላቸውን ያረጋግጡ፡፡
- በጻፉት የህይወት ታሪክ ያሳዩትን ጠንካራ ጎን እና መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች ያስረዷቸው፡፡
- መምህር ተማሪዎቹ የህይወት ታሪክ አፃፃፍልምምዳቸውን አጠናክረው እንዲሄዱ በድጋሜ የራሳቸውን የህወት ታሪክ እንዲጽፉ ይግለጹላቸው፡፡

# ❖ ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## ርቱዕና ኢርቱዕ

- በዚህ ስር ተማሪዎች ርቱዕና ኢርቱዕ ግስን እንዲለዩ ይጠበቃል፡፡ስለዚህ በመልመጃ አንድ ስር ከተዘረዘሩት ግሶች ውስጥ ርቱዕና ኢርቱዕ በማለት ለይተው በሰንጠረዥ ውስጥ እንዲጽፉ በምሳሌ ያስረዷቸው፡፡
- የጥያቄውን መልስ በጠመኔ ሰሌዳዉ ላይ በመጻፍ እነሱ ከሰሩት ጋር አነፃፅረው ስህተታቸውን እንዲለዩ ያግዟቸው፡፡
- ለፈጸሙት ስህተት ማስተካከያ እንዲወስዱ ያድርጉ፡፡
- በርቱዕ የቀረቡትን ግሶች ወደኢርቱዕ እንዲለውጡ ይግለጹላቸው፡፡
- በመልመጃ ሶስት በቀረቡት ግሶች ርቱዕና ኢርቱዕ ተግባርን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች እንዲሰሩ ያስረዷቸው፡፡
- የተማሪዎቹን ደብተር በመሰብሰብ ያርሙና በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጡ፡፡
- እርማት የሚያስፈልገው ጥያቄ ካለ እርማት ይስጧቸውና አስተካክለው እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

## መልመጃ አንድ

➢ የሚከተሉትን ተቀላቅለው የቀረቡትን ቃላት ርቱዕ ወይም ኢርቱዕ በማትለይታችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ ፃፉ፡

| ተ/ቁ | ርቱዕ | ኢርቱዕ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ላጠ | ተመታ |
| | ፈላ | ተሰበረ |
| 1 | በላ | ተሰራ |
| 2 | ሳለ | ተደበደበ |
| 3 | መታ | ተለወጠ |
| 4 | ሰበረ | ተሰወረ |
| 5 | ሸለመ | ተቀየረ |
| 6 | ፃፈ | ተሰነጠቀ |
| 7 | ጠጣ | ተወዳደረ |

## መረጃ መሳሪያ

ርቱዕና ኢርቱዕ ግሶችን በንጽጽር የሚያሳይ ቻርት

# ዋቢ መፃሕፍት

ሀዲስ አለማየሁ። (1996 ዓ.ም) ።ፍቅር እስከ መቃብር። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ሔኖክ ያሬድ። (2005 ዓ.ም) ።በአበበ ቢቂላ የተወለደው መቼ ነው።ሪፖርተር ጋዜጣ

መዘመር ግርማ። (2011ዓ.ም) ።ሁቱትሲ የወጣቷ ልብ አንጠልጣ ትውስታዎች የትርጉም ስራ።

ማርታ እሸቱና ነፃነት ጌትነት። (2004 ዓ.ም) ። የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ 10ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣በት.መ.ማ.ማ.ድ።

ሜሪ ጄን ግሌይና ሳባ ገ/መድህን ። (2007ዓ.ም) ።ተምሳሌት። ፅሀይ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራዊ ቅንጅት አሳታሚ ድርጅት።

ሰለሞን ሐለፎም። (1997 ዓ.ም) ። የድርሰት አፃፃፍ።አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድጅት።

ሳሙኤል አየለና ታሪኳ መላኩ። (1997ዓ.ም) ።የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ሳባ ያማርኛ መዝገበ ቃላት። (2005 ዓ.ም) ። አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስትቲትዩት። (1995 ዓ.ም) ። የኤች አይ ቪ ኤድስ ትምህርት።አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ሪፖርተር ጋዜጣ። (2009 ዓ.ም) ። ኪንና ባህል፣ታትሞ ከወጣው ለማስተማሪያነት ተሸሽሎ የተወሰደ።

ባየ ይማም፡፡ (2010 ዓ.ም) ፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ታለጌታ ይመር፡፡ (2007 ዓ.ም)፡፡ ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ ማሪያ አጋዥ መፅሀፍ፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፣ሴቭ ዘ ችልድረን እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በጋራ ትብብር፡፡ (2008 ዓ.ም) ፡፡ለምግብነት የሚውሉ የጓሮ አትክልቶች በሚል የተዘጋጀ አጋዥ መፅሀፍ፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (1999 ዓ.ም) ፡፡ ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ ከ7-10ኛ ክፍል፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

አለቃ ደስታ ተ/ክለወልድ፡፡ (1962ዓ.ም) ፡፡ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣በአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አምሳለ አክሊሉ፡፡ (1981 ዓ.ም) ፡፡ በአለም የታወቁ አጫጨር ልቦለዶች፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፤

ዘሪሁን አስፋው ፡፡ (2004 ዓ.ም)፡፡ የስነ-ፅሁፍ መሰረታውያን፡፡ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት፡፡ ባህርዳር፣(ያልታተመ)፡፡

የአዲስ አበባ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (2007 ዓ.ም) ፡፡ ባህል ቱሪዝም፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ፡፡ (2007ዓ.ም)፡፡ የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል፡ ፡አዲስ አበባ፣በሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፡፡ (2012 ዓ.ም) ፡፡ የጥላቻ ንግርርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፡፡ሀያ ስድተኛ አመት ቁጥር 26 ገፅ 12339፡፡ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም መተሚያ ድርጅት፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡ (1996 ዓ.ም) ፡፡ተግባራዊ የፅህፈት መማሪያ፡፡አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያድርጅት፡፡

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፡፡ (2008 ዓ.ም) ፡፡ኮሜት አጋዥ መፅሃፍ ከ9-10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴት ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ (2009 ዓ.ም) ፡፡ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ፋንታሁን እንግዳ፡፡ (2000 ዓ.ም) ፡፡ታሪካዊ መዝገበ ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ፡፡ አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

## የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | |